# የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

## ማዕከላዊ ነጋሪት ጋዜጣ

## MAEKELAWI NEGARIT GAZETA

## OF THE CENTRAL ETHIOPIA REGIONAL STATE

ወልቂጤ 2ኛ ዓመት ቁጥር

የካቲት 20 ቀን 2'*፲6 ዓ.ም

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

ጠባቂነት የወጣ

Woliqite 2nd Year No

February 28 /2024


### አዋጅ ቁጥር 8/2016 ዓ.ም

### የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ

### መግቢያ

የታክስ አስተዳደሩ ይበልጥ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተገማችነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ የክልሉ ታክሶች የሚመሩበት ራሱን የቻለ የታክስ አስተዳደር አዋጅ እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ፣

የታክስ ሕጐች አተረጓጐም ስርዓት ወጥነት ያለው እንዲሆን በማድረግ ታክስ ከፋዩ እንግልት እንዳይገጥመው የሚያስችል የአተረጓጐም ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ የሚያስፈልግ በመሆኑ፤

ታክስ ከፋዮች በታክስ ውሳኔ ረገድ የሚኖራቸውን ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉበት ተደራሽነት ያለው፣ በሚገባ የተደራጀ እና የተቀላጠፈ ውሳኔ መስጠት የሚያስችል የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሥራ ላይ ያለው የታክስ አስተዳደር አዋጅ ከክልሉ ህገ-መንግስት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን

### Proclamation No. 8/2024

### The Central Ethiopia Regional State Tax Administration Proclamation

### Preamble

WHEREAS, it is necessary to enact a separate tax administration proclamation governing the administration of regional taxes with a view to render the tax administration system more efficient, effective and measurable ;

WHEREAS, it is believed that introducing the system of advance tax ruling helps to address the problem of prolonged pendency of taxpayers cases resulting from divergent interpretations of tax laws within the tax administration;

WHEREAS, it is necessary to establish a system for review of taxpayers' complaints on tax decisions which is accessible, well organized and capable of efficient disposition of cases;

WHEREAS, it has become necessary that the effective proclamation of the tax administration to

በአዲስ አዋጅ መታወጅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሕገ-መንግስት አንቀፅ 55 ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 8/" 2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጉም

ይህንን አዋጅ ጨምሮ ለታክስ ሕጎች አፈፃፀም የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1. "የተሻሻለ የግብር ውሳኔ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 መሠረት ቢሮው የሚሰጠው የተሻሻለ የግብር ውሳኔ ነው፡፡
2. "ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ውሳኔ" ማለት
   ሀ) በቅሬታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ፣
   ለ) የሚከተሉትን ሳይጨምር ቢሮው የሚሰጠው ሌላ ማንኛውም ውሳኔ፣
      1) የታክስ ውሳኔ፣
      2) የታክስ ውሳኔ በመስጠት ሂደት ቢሮው የሚሰጠው ውሳኔ፤
3. "የጸደቀ ቅጽ" በዚህ አዋጅ አንቀጽ 79 የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡
4. "ቢሮ" ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ገቢዎች ቢሮ እና እንደ አግባብነቱ

be declared by a new proclamation to be compatible with the Region Constitution;

NOW, THEREFORE, in accordance with sub Article 3 of Article 55 of the Constitution of the Central Ethiopia Region State, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "the Central Ethiopia Region State Tax Administration Proclamation No…8…. /2024."

### 2. Definition

In the tax laws (including this Proclamation), unless the context otherwise requires:-

1. "Amended assessment" means an amended assessment made by the Bureau under Article 28 of this Proclamation;
2. "Appealable decision" means:
   a) an objection decision;
   b) any other decision of the Bureau made other than:
      1) a tax decision;
      2) a decision made by the Bureau in the course of making a tax decision;
3. "Approved form" has the meaning in Article 79 of this Proclamation;
4. "Bureau" means Central Ethiopia Regional Revenue Bureau and includes the relevant

በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ መምሪያዎች፤ ጽህፈት ቤቶች እና የታክስ ማዕከላትን ይጨምራል፡፡

5. “ድርጅት” ማለት ኩባንያ፤ የሽርክና ማህበር፣ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የመንግሥት የፋይናንስ ድርጅት ወይም ሌላ በኢትዮጵያ ወይም በውጭ ሀገር የተመሠረተ ድርጅት ነው፡፡

6. “ኮሚሽን” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 86 መሠረት የሚቋቋመው የግብር ይግባኝ ኮሚሽን ነው፡፡

7. “ኩባንያ” ማለት የራሱ ሕጋዊ ሰውነት ያለው በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ለመሥራት የተቋቋመ ድርጅት ሲሆን፣ በሌላ ሀገር ሕግ መሠረት የተመሠረተን ተመሳሳይ የንግድ ድርጅት ይጨምራል፡፡

8. “ወሳኝ ድምፅ ያለው አባል” ማለት ኩባንያን በሚመለከት፣ ለራሱ ጥቅም ሲል ብቻውን ወይም ግንኙነት ካለው ሰው ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ፡-

   ሀ) በኩባንያው ካለው ጥቅም ጋር ተያይዞ 50% ወይም ከዚያ በላይ ድምፅ የመስጠት መብት ያለው፤
   ለ) በኩባንያው ካለው ጥቅም ጋር ተያይዞ 50% ወይም ከዚያ በላይ የትርፍ ድርሻ የሚያገኝ፤ ወይም
   ሐ) በኩባንያው ካለው ጥቅም ጋር ተያይዞ 50% ወይም ከዚያ በላይ

departments, offices, and tax centers at each administrative level.

5. “Body” means a company, partnership, public enterprise or public financial agency, or other body of persons whether formed in Ethiopia or elsewhere;

6. “Commission” means the Tax Appeal Commission established under Article 86 of this Proclamation;

7. “Company” means a commercial business organisation established by the Commercial Code of Ethiopia and having legal personality, and includes any equivalent entity incorporated or formed under a foreign law;

8. “Controlling member”, in relation to a company, means a member who beneficially holds, directly or indirectly, either alone or together with a related person or persons:

   a) 50% or more of the voting rights attaching to membership interests in the company;
   b) 50% or more of the rights to dividends attaching to membership interests in the company; or
   c) 50% or more of the rights to capital attaching to membership interests in

የካፒታል ድርሻ ያለው አባል ነው፡፡

9. “ሰነድ” የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡
   ሀ) የሂሳብ መዝገብ፣ ሪከርድ፣ የመመዝገቢያ ሰነድ፣ የባንክ መግለጫ፣ ደረሰኝ፣ ኢንቮይስ፣ ቫውቸር፣ ውል ወይም ስምምነት፣ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን፤
   ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 መሠረት ፈቃድ በተሰጠው የታክስ ወኪል የተሰጠ የምስክር ወረቀት ወይም መግለጫ፤ ወይም
   ሐ) በኤሌክትሮኒክ የመረጃ ማከማቻ መሳሪያ ውስጥ የተከማቸ ወይም የተያዘ ማንኛውም መረጃ ወይም ዳታ፣
10. “በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት” ማለት ቢሮው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 26 መሠረት በግምት የሚያከናውነው የታክስ ስሌት ነው፡፡
11. “የበጀት ዓመት” ማለት ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ቀን ያለው ጊዜ ነው፡፡
12. “የስጋት የታክስ ስሌት” ማለት ቢሮው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 መሠረት ከስጋት በመነሳት የሚያከናውነው የታክስ ስሌት ነው፡፡
13. “የገንዘብ ክፍያ ትእዛዝ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 43 መሠረት በቢሮው የሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትእዛዝ ነው፡፡
14. "ዓለም አቀፍ ሰምምነት" ማለት በኢትዮጵያ መንግሥትና በሌላ ሀገር መንግሥት ወይም መንግሥታት ወይም

the company;

9. “Document” includes:
   a) a book of account, record, register, bank statement, receipt, invoice, voucher, contract or agreement, or Customs entry;
   b) a certificate or statement provided by a licensed tax agent under Article 22 of this Proclamation; or;
   c) any information or data stored on an electronic data storage device;
10. “Estimated assessment” means an estimated assessment made by the Bureau under Article 26 of this Proclamation;
11. “Fiscal year” means the budgetary year of the Ethiopian Government;
12. “Jeopardy assessment” means a jeopardy assessment made by the Bureau under Article 27 of this Proclamation;
13. “Garnishee order” means a garnishee order issued by the Bureau under Article 43 of this Proclamation;
14. “International agreement” means an agreement between the Government of Ethiopia and a foreign government or governments, or an international

ዓለም አቀፍ ድርጅት መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው፡፡

15. "ዓለም አቀፍ ድርጅት" ማለት ሉዓላዊ ሥልጣን ያላቸው ሀገራት ወይም የእነዚህ ሀገራት መንግሥታት አባል የሆኑበት ድርጅት ነው፡፡

16. “ክፍያ ለዘገየበት የሚከፈል ወለድ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 37 መሠረት የታክስ ክፍያ በመዘግየቱ ምክንያት የሚከፈል ወለድ ነው፡፡

17. “የታክስ ወኪል” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 91 ወይም 92 መሠረት ፈቃድ የተሰጠው የታክስ ወኪል ነው፡፡

18. “ፈቃድ ሰጪ አካል” ማለት ፈቃድ፣ የምስክር ወረቀት፣ ስምምነት፣ ወይም ሌላ መብት ለመስጠት በማንኛውም ሕግ የተሾመ ሰው ነው፡፡

19. “ሥራ አስኪያጅ” ማለት

ሀ) ለሽርክና ማህበር ሲሆን ሽሪኩ ወይም የሽርክና ማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይም በዚህ ደረጃ የሚሠራ ወይም ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውን ሰው፤

ለ) ለኩባንያ ሲሆን፣ የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ወይም በኩባንያው ውስጥ ተመሳሳይ ሥልጣን ያለው ወይም በዚህ ደረጃ የሚሠራ ወይም ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውን ሰው፤

ሐ) ለሌላ ለማንኛውም ድርጅት፣ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይም በኩባንያው

organisation;

15. “International organisation” means an organisation the members of which are sovereign states or governments of sovereign states;

16. “Late payment interest” means late payment interest imposed under Article 37;

17. “Licensed tax agent” means a tax agent licensed under Article 91 or 92 of this Proclamation;

18. “Licensing Bureau” means any organ authorized under any law to issue a licence, certificate, concession, or other authorisation;

19. “Manager” means:

a) for a partnership, a partner or general manager of the partnership, or a person acting or purporting to act in that capacity;

b) for a company, the chief executive officer, a director, general manager, or other similar officer of the company, or a person acting or purporting to act in that capacity; or

c) for any other body, the general manager or other similar officer of the body, or a person acting or

ውስጥ ተመሳሳይ ሥልጣን ያለው ሰው ወይም በዚህ ችሎታ የሚሠራ ወይም ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውን ሰው ነው፡፡

purporting to act in that capacity.

20. “አባል” ማለት ኩባንያን በሚመለከት ማንኛውም ባለአክሲዮን ወይም በኩባንያው ውስጥ ሌላ ማንኛውም የአባልነት ጥቅም ያለው ሰው ነው፡፡

20. “Member” in relation to a body, means a person with membership interest in the body including a shareholder in a company or a partner in a partnership;

21. “የአባልነት ጥቅም” ማለት ኩባንያን በሚመለከት የአክሲዮን ወይም ሌላ የባለቤትነት ጥቅም ነው፡፡

21. “Membership interest”, in relation to a body, means an ownership interest in the body including a share in a company or an interest in a partnership;

22. “የሽርክና ማህበር” ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት የተቋቋመ የሽርክና ማህበር ሲሆን በውጭ ሀገር ሕግ መሠረት የተቋቋመን ተመሳሳይ አካልም ይጨምራል፡፡

22. “Partnership” means a partnership formed under the Commercial Code of Ethiopia and includes an equivalent entity formed under foreign law;

23. “ቅጣት” ማለት የታክስ ሕግ በመጣሱ ምክንያት በዚህ አዋጅ ክፍል አስራ አምስት ምዕራፍ ሁለት ወይም በሌላ የታክስ ሕግ የሚጣል አስተዳደራዊ ቅጣት ነው፡፡

23. “Penalty” means an administrative penalty for breach of a tax law imposed under Chapter Two of Part Fifteen of this Proclamation or under another tax law;

24. “የገንዘብ ቅጣት ውሳኔ” ማለት ቢሮው በዚህ አዋጅ ክፍል አስራ አምስት ምዕራፍ ሁለት መሠረት የሚወስነው የገንዘብ ቅጣት ነው፡፡

24. “Penalty assessment” means an assessment of penalty made by the Bureau under Chapter Two of Part Fifteen of this Proclamation;

25. “ሰው” ማለት ግለሰብ፣ ድርጅት፣ መንግሥት ወይም የአንድ መንግሥት ንዑስ የፖለቲካ አካል ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት ነው፡፡

25. “Person” means an individual, body, government, local government, or international organisation;

26. “በሁለተኛ ደረጃ የሚመጣ ኃላፊነት” ማለት አንድ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16(4)፣ 40(3(ሐ)፣ 41(12)፣ 42(8)፣ 43(10)፣ 46(1)፣ 47(1) ወይም 48(1) ያለበትን ኃላፊነት (“የመጀመሪያ ኃላፊነት ተብሎ የሚጠቀስ”) በመወጣት ረገድ ሌላ ሰው ያለበት ኃላፊነት ነው፡፡

27. “በታክስ ከፋዩ የተከናወነ ስሌት” ማለት ታክሱን የማስላት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 መሠረት ያከናወነው የታክስ ስሌት ነው፡፡

28. “የታክስ ስሌት ማስታወቂያ” ማለት፡-

ሀ) በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት የሚቀርብ የግብር ማስታወቂያ፣

ለ) ወደ ሀገር ውስጥ በገባው ዕቃ ላይ የሚከፈለውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ የሚያሳይ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን፣

ሐ) በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ፣

መ) በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ፣

ሠ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 መሠረት የሚቀርብ በቅድሚያ የሚከፈል ታክስ ማስታወቂያ፤ ወይም

ረ) በታክስ ሕግ መሠረት የታክስ ማስታወቂያ ተብሎ የሚጠቀስ በታክስ ከፋዩ የሚዘጋጅ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ፣

26. “Secondary liability” means a liability of a person (referred to as the “primary liability”) that another person is personally liable for under Article 16(4), 40(3)(c), 41(12), 42(8), 43(10), 46(1), 47(1), or 48(1) of this Proclamation;

27. “Self-assessment” means an assessment treated as having been made by a self-assessment taxpayer under Article 25 of this Proclamation;

28. “Self-assessment declaration” means:

a) a tax declaration under the Income Tax Proclamation;

b) a Customs entry to the extent that it specifies the value added tax or excise tax payable in respect of an import of goods;

c) an excise tax declaration under the Excise Tax Proclamation;

d) a turnover tax declaration under the Turnover Tax Proclamation;

e) an advance tax declaration under Article 23 of this Proclamation; or

f) a tax declaration specified as a self-assessment declaration under a tax law;

29. “ታክሱን የማስላት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ” ማለት ራሱ ያከናወነውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ማቅረብ የሚገደድ ሰው ነው፡፡

30. “ታክስ” ማለት በታክስ ሕጎች መሠረት የሚጣል ታክስ ሲሆን፣ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ) በከፋዩ ተቀንሶ የሚቀር ታክስ፣

ለ) በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት አስቀድሞ የሚከፈል ወይም በየጊዜው የሚከፈል ታክስ

ሐ) ቅጣት

መ) ክፍያ በመዘግየቱ ምክንያት የሚከፈል ወለድ ነው፣

31. “የታክስ ስሌት” ማለት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ፣ በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት፣ የስጋት የታክስ ስሌት፣ የታስክ ስሌት ማሻሻያ፣ አስተዳደራዊ የታክስ ቅጣት ወይም ወለድ ስሌት፣ ወይም በታክስ ሕግ መሠረት የሚደረግ ሌላ ማንኛውም ስሌት ነው፡፡

32. “ከታክስ የመሸሽ ድንጋጌ” ማለት በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ የተመለከቱት ከታክስ የመሸሽ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

33. “የታክስ ውሳኔ” ማለት

ሀ) በታክስ ከፋዩ የተከናወነውን የታክስ ስሌት የማይጨምር የታክስ ስሌት፣

ለ) ታክሱን የማስላት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ በሚያቀርበው ማመልከቻ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 መሠረት የሚሰጥ ውሳኔ፤

29. “Self-assessment taxpayer” means a taxpayer required to file a self-assessment declaration;

30. “Tax” means a tax levied under a tax law and includes the following:

a) withholding tax;
b) advance payments of tax and instalments of tax payable under the Income Tax Proclamation;
c) penalty;
d) late payment interest;

31. “Tax assessment” means a self-assessment, estimated assessment, jeopardy assessment, amended assessment, penalty or interest assessment, or any other assessment made under a tax law;

32. “Tax avoidance provision” means the tax avoidance provisions of the Regional Income Tax Proclamation; and

33. “Tax decision” means:

a) a tax assessment, other than a self-assessment;
b) a decision on an application by a self-assessment taxpayer under Article 29 of this Proclamation;

ሐ) በታክስ ከፋዩ እንዲከፈል ወይም ለወደፊት እንዲከፈል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40/2/ መሠረት የተሰጠ ውሳኔ፤

መ) በሁለተኛ ደረጃነት የሚመጣን ኃላፊነት ወይም ታክስን ለማስከፈል የሚወጣን ወጭ ማስመለስን በሚመለከት የሚሰጥ ውሳኔ፤

ሠ) ክፍያ በመዘግየቱ ምክንያት የሚጣልን ወለድ በተመለከተ የተሰጠ ውሳኔ፤

ረ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 49 ወይም 50 መሰረት በቀረበ የታክስ ተመላሽ ማመልከቻ ላይ የሚሰጥ የእምቢታ ውሳኔ፤

ሰ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 49 መሠረት ሊካካስ ከሚችለው በላይ የሆነን የታክስ ተመላሽ መጠን፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 50 መሠረት የሚቀርብን የተመላሽ ጥያቄ መጠን ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 50 መሠረት እንደገና መከፈል የሚኖርበትን የተመላሽ መጠን አስመልክቶ የሚሰጥ ውሳኔ፤ ወይም

ሸ/ ለቢሮው ያልተከፈለ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የቀረን ታክስ በሚመለከት በክልሉ ገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 88(3) መሠረት የሚሰጥ ውሳኔ፤

34. “የታክስ ማስታወቂያ” ማለት የሚከተሉት ናቸው::

ሀ) በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት መቅረብ የሚኖርበት የታክስ ማስታወቂያ፤

ለ) በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት በከፋዩ

c) a determination under Article 40(2) of this Proclamation of the amount of tax payable or that will become payable by a taxpayer;

d) a determination of a secondary liability or the amount of tax recovery costs payable;

e) a determination of late payment interest payable;

f) a decision to refuse an application for a refund under Article 49 or 50;

g) a determination of the amount of an excess credit under Article 49 of this Proclamation, the amount of a refund under Article 50 of this Proclamation, or the amount of a refund required to be repaid under Article 50 of this Proclamation; or

h) a determination of the amount of unpaid withholding tax under Article 88(3) of the Regional Income Tax Proclamation;

34. “Tax declaration” means the following:

a) a tax declaration required to be filed under the Income Tax Proclamation;

b) a withholding tax declaration

ተቀንሶ የሚያዝን ታክስ በሚመለከት የሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያ፤

ሐ) በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ ታክስ ማስታወቂያ፤

መ) በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያ፤

ሠ) በዚህ አዋጅ መሠረት በታክስ ከፋዩ መቅረብ የሚኖርበት የታክስ ማስታወቂያ፤

35. “የታክስ ሕግ” ማለት

ሀ) ይህ አዋጅ፤

ለ) የገቢ ግብር አዋጅ፣

መ) የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፤

ሠ) የቴምብር ቀረጥ አዋጅ፤

ረ) የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ

ሰ) ቢሮው ታክሱን፣ ቀረጡን ወይም ክፍያውን የማስተዳደር ኃላፊነት የተሰጠው እስከሆነ ድረስ ማንኛውም ይህንን ታክስ፣ ቀረጥ፣ወይም ክፍያ የሚጥል ሌላ ሕግ፤

ሸ) ከዚህ በላይ ባሉት ንዑስ አንቀጾች ሥር በተጠቀሰው ሕግ መሠረት የሚወጣ ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ ነው፡፡

36. “የታክስ ሠራተኛ” ማለት

ሀ) የቢሮው ዋና ሀላፊ፤

ለ) የቢሮው ምክትል ሀላፊዎች፤

ሐ) የክልሉን የታክስ ሕግ የማስተዳደርና

required to be filed under the Income Tax Proclamation;

c) a declaration required to be filed under the Excise Tax Proclamation;

d) a turnover tax return required to be filed under the Turnover Tax Declaration;

e) a tax declaration required to be filed by a taxpayer under this Proclamation;

35. “Tax law” means:

a) this Proclamation;

b) the Income Tax Proclamation;

c) the Excise Tax Proclamation;

d) the Stamp Duty Proclamation;

e) the Turnover Tax Proclamation;

f) any other legislation (other than legislation relating to Customs) under which a tax, duty, or levy is imposed if the Bureau has responsibility for the administration of the tax, duty, or levy;

g) any regulation or directives made under a law referred to in the above sub Articles;

36. “Tax officer” means:

a) the Head of the Bureau;

b) the Deputy Head of the Bureau;

c) officers or employees of the tax

የማስፈፀም ኃላፊነት የተጣለባቸው ሌሎች የቢሮው ኃላፊዎች ወይም ተቀጣሪዎች፤

መ) ቢሮውን ወክለው ሲሰሩ፡-

1. የክልሉ ፖሊስ አባል፤
2. ሌሎች በቢሮው ተወክለው የሚሰሩ የመንግስት መስሪያ ቤት ኃላፊዎችና ሠራተኞች፤

37. "የታክስ ጊዜ" ማለት ከታክስ ጋር በተያያዘ ለቢሮው ማስታወቂያ የሚቀርብበት ታክስ የሚሸፍነው ጊዜ ነው፡፡

38. "ታክስ ለማስከፈል የወጡ ወጪዎች" ማለት፡-

ሀ) ቢሮው ያልተከፈለን ታክስ ለማስከፈል የሚያወጣቸው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30( 3) የተዘረዘሩ ወጪዎች፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 41 (9) (ሀ) የተዘረዘሩት ቢሮው ታክስ ለማስከፈል የሚያስችልን ሀብት ሲይዝ የሚያወጣቸው ወጪዎች ናቸው፡፡

39. "የታክስ እንደራሴ" ማለት ታክስ ከፋዩን በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውንም ገንዘብ ለመቀበል ወይም ለመክፈል ኃላፊነት ያለበት ግለሰብ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡

ሀ) የሽርክናን ማህበር በተመለከተ የሽርክና ማህበሩ ሸሪክ ወይም ሥራ አስኪያጅ፣

ለ) ኩባንያን በተመለከተ የኩባንያው ዳይሬክተር፤

ሐ) ችሎታ የሌለውን ግለሰብ በተመለከተ ችሎታ የሌለውን ግለሰብ በመወከል

authorities responsible to administer and implement the regional tax law;

d) when performing functions on behalf of the Bureau:

1) a member of the Regional police;
2) Other governmental offices' heads and staff represented by the bureau.

37. "Tax period", in relation to a tax, means the period for which the tax is reported to the Bureau;

38. "Tax recovery costs" means:

a) the costs of the Bureau referred to in Article 30(3) of this Proclamation incurred in recovering unpaid tax;

b) the costs of the Bureau referred to in Article 41 (9) (a) of this Proclamation incurred in undertaking seizure proceedings;

39. "Tax representative", in relation to a taxpayer, means an individual responsible for accounting for the receipt or payment of moneys or funds in Ethiopia on behalf of the taxpayer and includes the following:

a) for a partnership, a partner in the partnership or a manager of the partnership,

b) for a company, a director of the company;

c) for an incapable individual, the legal representative of the individual

ወይም ለዚህ ግለሰብ ጥቅም ገቢ የሚቀበል ህጋዊ ወኪል፣

responsible for receiving income on behalf or, or for the benefit of, the individual;

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40 የተጠቀሰውን ታክስ ከፋይ በተመለከተ በተጠቀሰው አንቀጽ መሠረት የታክስ ከፋዩ ባለአደራ፣

d) for a taxpayer referred to in Article 40 of this Proclamation, the receiver in relation to the taxpayer under that Article;

ሠ) ማንኛውንም ታክስ ከፋይ በተመለከተ ለታክስ ሕጎች ዓላማ ሲባል ቢሮው በጽሁፍ በተሰጠ ማስታወቂያ የታክስ ከፋዩ የታክስ እንደራሴ እንደሆነ ያስታወቀው ግለሰብ ነው፡፡

e) for any taxpayer, an individual that the Bureau has, by notice in writing to the individual, declared to be a tax representative of the taxpayer for the purposes of the tax laws;

40. "ታክስ ከፋይ" ማለት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ሲሆን የሚከተሉትንም ይጨምራል፡-

ሀ) የገቢ ግብርን በተመለከተ በሠንጠረዥ "ለ" ወይም "ሐ" መሠረት በግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ የሌለው በግብር እፎይታ ላይ ያለ ወይም ኪሳራ ያጋጠመው ሰው፤

ለ) የተርን ኦቨር ታክስን በተመለከተ የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ ሰው፤

40. "Taxpayer" means a person liable for tax and includes the following:

a) for the income tax, a person who has zero taxable income or privilege of tax holiday or loss under Schedule 'B' or 'C' for a tax year;

b) for the Turn Over Tax, Turn Over taxpayer;

41. "ያልተከፈለ ታክስ" ማለት በመክፈያ ቀን ወይም ቢሮው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 የተመለከተውን የታክስ መክፈያ ቀን ያራዘመ ከሆነ በተራዘመው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ ታክስ ነው፡፡

41. "Unpaid tax" means tax that has not been paid by the due date or, if the Bureau has extended the due date under Article 32 of this Proclamation, by the extended due date;

42. "ታክስ ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው" ማለት በክልሉ ገቢ ግብር አዋጅ ክፍል አስር መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ

42. "Withholding agent" means a person required to withhold tax from a payment under Part Ten of the Regional Income Tax

ላይ ታክስ ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ የተጣለበት ሰው ነው፡፡

43. “ተቀንሶ የሚያዝ ታክስ” ማለት በክልሉ ገቢ ግብር አዋጅ ክፍል አስር መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ መያዝ ያለበት ታክስ ነው፡፡

44. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸ ሀሳብ የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

### 3. ትክክለኛ የገበያ ዋጋ

1. የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 77 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለታክስ ሕጎች ዓላማ በአንድ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ የአንድ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ ዋጋ ነው የሚባለው የዕቃው፣ የንብረቱ፣ የአገልግሎቱ ወይም የጥቅሙ የወቅቱ እና የቦታው መደበኛ የገበያ ዋጋ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት በአንድ የተወሰነ ጊዜ እና ቦታ የአንድን ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ ዋጋውን ለመወሰን ባልተቻለው ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም እና ማንኛውም ሌላ ተመሳሳይ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም በሚያስገኘው ትክክለኛ ዋጋ መካከል ላለው ልዩነት ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ የሚገኘው ዋጋ ዋጋውን ለመወሰን ያልተቻለው ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ሆኖ ይወሰዳል፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈጻፀም፣

Proclamation;

43. “Withholding tax” means tax that is required to be withheld from a payment under Part Ten of the Regional Income Tax Proclamation;

44. Any expression in the masculine shall also include the feminine.

### 3. Fair Market Value

1. For the purposes of the tax laws and subject to Article 77 of the Income Tax Proclamation, the fair market value of goods, an asset, service, or benefit at a particular time and place is the ordinary open market value of the goods, asset, service, or benefit at that time and place.
2. If it is not possible to determine the fair market value of goods, an asset, service, or benefit under sub-article (1) of this Article, the fair market value is the consideration any similar goods, asset, service, or benefit would ordinarily fetch in the open market at that time and place, adjusted to take account of the differences between the similar goods, asset, service, or benefit and the actual goods, asset, service, or benefit.
3. For the purposes of sub-article (2) of this

አንድ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ከሌላ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ጋር ተመሳሳይ ነው የሚባለው ከሌላው ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ጋር በባህሪይ፣ በጥራት፣ በብዛት በሚሰጠው አገልግሎት በሚይዛቸው ቁሶችና በመልካም ስም ተመሳሳይ ወይም በሚቀራረብ ሁኔታ ተመሳሳይ የሆነ እንደሆነ ነው።

Article, goods, an asset, service, or benefit is similar to other goods, asset, service, or benefit, as the case may be, if it is the same as, or closely resembles, the other goods, asset, service, or benefit in character, quality, quantity, functionality, materials, and reputation.

4. የአንድን ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ ዋጋ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ ከዋጋ አገማመት ጠቅላላ መርሆዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ ትክክለኛው የገበያ ዋጋ በቢሮው የሚወሰን ይሆናል።

4. If the fair market value of goods, an asset, service, or benefit cannot be determined under the preceding sub-articles of this Article, the fair market value shall be the amount determined by the Bureau provided it is consistent with generally accepted principles of valuation.

5. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ለዕቃ፣ ለንብረት፣ ለአገልግሎት ወይም ለጥቅም የተከፈለ ዋጋ ከዕቃው፣ ከንብረቱ፣ ከአገልግሎቱ ወይም ከጥቅሙ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ የበለጠ ወይም ያነሰ ሊሆን ይችላል።

5. For the purpose of this Article, the fair market value of goods, an asset, service, or benefit may be greater or lesser than the actual price charged for the goods, asset, service, or benefit.

6. ቢሮው የአንድን ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

6. The Bureau may issue a Directive for the purposes of determining the fair market value of any goods, asset, service, or benefit.

### 4. ግንኙነት ያላቸው ሰዎች

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለታክስ ሕጎች አፈፃፀም ሁለት ሰዎች ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ናቸው የሚባለው ከሁለቱ አንዱ ሰው በሌላኛው ሰው ትዕዛዝ፣ ጥያቄ፣ አስተያየት ወይም ፍላጎት መሠረት ይንቀሳቀሳል ተብሎ ሲገመት ወይም ሁለቱም

### 4. Related Persons

1. For the purposes of the tax laws and subject to sub-article (2) of this Article, two persons are related persons when the relationship between the two persons is such that one person may reasonably be expected to act in accordance with the directions, requests, suggestions, or

ሰዎች በሌላ ሦስተኛ ወገን ትዕዛዝ፣ ጥያቄ፣ ሃሣብ ወይም ፍላጎት መሠረት ይንቀሳቀሳሉ ተብሎ ሲታመን ነው፡፡

2. አንድ ሰው የሌላ ሰው ተቀጣሪ ወይም ደምበኛ ስለሆነ ብቻ ወይም ደግሞ ሁለቱም ሰዎች የሦስተኛ ወገን ተቀጣሪዎች ወይም ደንበኞች በመሆናቸው ብቻ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ናቸው ሊባሉ አይችሉም፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሚከተሉት ሰዎች ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡

   ሀ) ቢሮው ከሁለቱ አንዱ በሌላኛው ትዕዛዝ፣ ጥያቄ፣ አስተያየት ወይም ፍላጎት መሠረት አይንቀሳቀስም ብሎ ካላመነ በስተቀር፣ አንድ ግለሰብና የዚህ ግለሰብ ዘመድ፤

   ለ) አንድ ድርጅት ወይም የዚህ አንቀጽ ሌሎች ድንጋጌዎች ተፈፃሚ በሚሆንበት ሁኔታ የዚህ ድርጅት አባል በራሱ ወይም ግንኙነት ካላቸው ሰዎች ጋር በመሆን በቀጥታ ወይም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑና በተሳሰሩ ድርጅቶች አማካይነት የድርጅቱን 25% (ሃያ አምስት በመቶ) ወይም ከዚያ በላይ የመምረጥ፣ የትርፍ ድርሻ ወይም የካፒታል ደርሻ መብት የሚቆጣጠር ሲሆን ድርጅቱና የድርጅቱ አባል ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡

   ሐ) ሁለት ድርጅቶች ግንኙነት ያላቸው ናቸው

wishes of the other person, or both persons may reasonably be expected to act in accordance with the directions, requests, suggestions, or wishes of a third person.

2. Two persons are not related persons solely because of the fact that one person is an employee or client of the other, or both persons are employees or clients of a third person.

3. Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the following are related persons:

   a) an individual and a relative of the individual unless the Bureau is satisfied that neither person may reasonably be expected to act in accordance with the directions, requests, suggestions, or wishes of the other;

   b) a body and a member of the body when the member, either alone or together with a related person or persons under another application of this Article, controls either directly or through one or more interposed bodies 25% or more of the rights to vote, dividends, or capital in the body;

   c) two bodies, if a person, either alone or

የሚባሉት አንድ ሰው ብቻውን ወይም የዚህ አንቀጽ ሌሎች ድንጋጌዎች ተፈፃሚ በሚሆኑበት ሁኔታግንኙነት ካለው ሰው ጋር በመሆን የሁለቱን ድርጅቶች የትርፍ ድርሻ ወይም ካፒታል በቀጥታ ወይም በሌሎች በተሳሰሩ ድርጅቶች አማካይነት 25% (ሃያ አምስት በመቶ) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የመምረጥ መብት፣ የተቆጣጠረ እንደሆነ ነው።

4. የአንድ ግለሰብ ዘመዶች ናቸው የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፤
   ሀ) የትዳር ጓደኛ፤
   ለ) ቅድመ አያት፣ አያት፣ አባት፣ እናት፣ ወደታች የሚቆጠር ዘመድ፣ ወንድም፣ እህት፣ የወንድም ልጅ፣ የእህት ልጅ፣ አጎት፣ አክስት፣ የአጎት ልጅ፣ የአክስት ልጅ፣ የእንጀራ እናት፣ የእንጀራ አባት፣ የጉዲፈቻ ልጅ፤
   ሐ) የጉዲፈቻ ልጅ ወላጅ፣ ወይም የእርሱ ወይም የእርሷ ባል ወይም ሚስት፤
   መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ (ለ) የተገለጹት ግለሰቦች ባል ወይም ሚስት፤

5. የአንድ ግለሰብ የትዳር ጓደኛ የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡
   ሀ) ግለሰቡ ወይም ግለሰቧ በህጋዊ መንገድ ያገባው ወይም ያገባችው፣
   ለ) ጋብቻ ሳይኖር ከግለሰቡ ወይም ግለሰቧ ጋር እንደባልና ሚስት አብሮ ወይም አብራ የሚኖር ወይም የምትኖር፤

together with a related person or persons under another application of this Article, controls, either directly or through one or more interposed bodies, 25% or more of the rights to vote, dividends, or capital in both bodies.

4. The following are a relative of an individual:
   a) the spouse of the individual;
   b) an ancestor, lineal descendant, brother, sister, uncle, aunt, nephew, niece, stepfather, stepmother, or adopted child of the individual;
   c) a parent of the adoptive child of the individual or spouse of the individual;
   d) a spouse of any person referred to in paragraph (b) of this sub-article.

5. The following are a spouse of an individual:-
   a) an individual who is legally married to the first-mentioned individual;
   b) an individual who lives in an irregular union with the first-mentioned individual;

6. አንድ የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አድራጊዎች የአንደኛ ደረጃ ዘመዶች ጋር ዝምድና እንዳለው ይቆጠራል፡፡

6. An adopted child is treated as related to their adoptive parent in the first degree of consanguinity.

## ክፍል ሁለት

## የታክስ ሕጎችን ስለማስተዳደር

## PART TWO

## ADMINISTRATION OF THE TAX LAWS

### 5. የቢሮው ኃላፊነት

የታክስ ሕጎችን ሥራ ላይ የማዋልና የማስፈፀም ኃላፊነት የቢሮው ነው፡፡

### 5. Duty of the Bureau

The implementation and enforcement of the tax laws shall be the duty of the Bureau.

### 6. የታክስ ሠራተኞች ግዴታዎችና ኃላፊነቶች

1. የታክስ ሠራተኛ ለቢሮው በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባርን መወሰኛ አዋጅ እና በሌሎች ህጎች ለታክስ ሕጐች አፈፃፀም ሲባል የተሰጠውን ማንኛውንም ሥልጣኑን ሊሠራበት ወይም ማንኛውንም ተግባርና ኃላፊነቱን መወጣት አለበት፡፡
2. የታክስ ሠራተኛ በታክስ ሕጐች በተሰጠው ማንኛውም ሥልጣኑ የሚሠራው ወይም ማንኛውንም ተግባርና ኃላፊነቱን የሚወጣው ታማኝነትና ፍትሐዊነትን በተላበሰ መንገድ ሲሆን ታክስ ከፋዩንም በአክብሮት የማስተናገድ ኃላፊነት አለበት፡፡
3. የታክስ ሠራተኛ ከሚከተሉት ጋር በተያያዘ በታክስ ሕጐች የተሰጠውን ሥልጣን ሊሠራበት ወይም ኃላፊነቱን ወይም ተግባሩን ሊያከናውን አይችልም፡፡
   ሀ) የቀረበለት ጉዳይ ከሠራተኛው የግል፣ የቤተሰብ፣ የንግድ፣ የሙያ፣ የቅጥር ወይም የፋይናንስ ግንኙነት ካለው ሰው ጋር የተገናኘ ከሆነ፣
   ለ) በሌላ መልኩ የጥቅም ግጭት

### 6. Obligations and Responsibilities of Tax Officers

1. A tax officer shall exercise any power, or perform any duty or function, assigned to the officer for the purposes of the tax laws in accordance with the proclamation issued to determine the powers and duties of the Execitive organs of the Central Ethiopia Region State.
2. A tax officer shall be honest and fair in the exercise of any power, or performance of any duty or function, under a tax law, and shall treat each taxpayer with courtesy and respect.
3. A tax officer shall not exercise a power, or perform a duty or function, under a tax law that:
   a) relates to a person in respect of which the tax officer has or had a personal, family, business, professional, employment, or financial relationship;
   b) Otherwise involves a conflict of

የሚያስከትል ከሆነ፣

4. የታክስ ሠራተኛ ወይም ሥራው በቀጥታ የሚመለከተው የፋይናንስ ቢሮ ሠራተኛ የታክስ ሂሣብ ሠራተኛ ወይም አማካሪ ወይም የታክስ ማስታወቂያ ለሚያዘጋጅ ወይም ታክስን አስመልክቶ ምክር ለሚሰጥ ሰው የሂሳብ ሠራተኛ ወይም አማካሪ በመሆን ሊያገለግል ወይም የዚህ ሰው ተቀጣሪ እንዲሆን የቀረበለትን ሀሳብ ሊቀበል አይችልም፡፡

interest.

4. A tax officer or any officer of the Bureau who is directly involved in tax matters shall not act as a tax accountant or consultant, or accept employment from any person preparing tax declarations or giving tax advice.

## 7. የመተባበር ግዴታ

በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ የክልሉ የመንግስት ተቋማት፣ ማህበራት፣ ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ግለሰቦች እና የሚመለከታቸው አካላት የታክስ ሕጎችን በማስፈፀም ረገድ ከቢሮው ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 7. Duty to Co-operate

All local government administrations, institutions, associations, non-government organisations, individuals, and concerned bodies shall have the duty to co-operate with the Bureau in the enforcement of the tax laws.

## 8. የታክስ መረጃ በምስጢር የሚያዝ ስለመሆኑ

1. የታክሰ ሠራተኛ በሥራው አጋጣሚ ያገኛቸውን የማንኛውም መረጃዎችና እና ሰነዶች ሚስጢራዊነት መጠበቅ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ የታክስ ሠራተኛ ለሚከተሉት ሰዎች አንድን ሰነድ ወይም መረጃ ከመግለጽ አይከለክለውም፡፡

   ሀ) ኃላፊነቱን ይወጣበት ዘንድ ለቢሮው ሌላ ሠራተኛ፤

   ለ) በታክስ ሕግ የተደነገገን የታክስ ወንጀል የፈፀመን ሰው ለመክሰስ እንዲሁም ሌላ ማናቸውም ሕግ የተደነገገን የታክስ ወንጀል የፈፀመን

## 8. Confidentiality of Tax Information

1. Any tax officer shall maintain the secrecy of all documents and information received in his official capacity.
2. The provision of sub-article (1) of this Article shall not prevent a tax officer from disclosing a document or information to the following:

   a) another tax officer for the purpose of carrying out official duties;

   b) a law enforcement agency for the purpose of the prosecution of a person for an offence under a tax law or the prosecution of a person for an offence

ሰው ለመክሰስ ይቻል ዘንድ ለሕግ አስፈጻሚ አካል፤

ሐ) ለኮሚሽኑ ወይም ክርክርን በማየት ላይ ላለ ፍርድ ቤት የአንድን ሰው የታክስ ኃላፊነት ለማረጋገጥ ወይም የቅጣት ኃላፊነትን ወይም ታክስ በመዘግየቱ ምክንያት የሚከፈል ወለድን ወይም ለወንጀል ጉዳይ የሚያስፈልግ መረጃ፤

መ) የመረጃ ልውውጥን የሚመለከት በፌዴራል መንግስት የተደረገ ስምምነት ሲኖር ለውጭ ጉዳይ ሚኒስተር የሚሰጥ መረጃ፤

ሠ) ለክልሉ ዋናው ኦዲተር ሥራውን ለማከናወን በሚያስፈልገው መጠን የሚሰጥ መረጃ፤

ረ) ለፌዴራል ፍትህ ሚኒስቴር ሆነ ለክልል ፍትህ ቢሮ ሥራውን ለማከናወን በሚያስፈልገው መጠን የሚሰጥ መረጃ፤

ሰ) ለቢሮው በሚያስፈልጋቸው መጠን የሚሰጥ መረጃ፤

ሸ) የሚሰጠው መረጃ አንድን ግለሰብ ለይቶ የማያሳውቅ ሲሆን፣ የመንግሥትን ገቢ የመሰብሰብ አገልግሎት ለሚሰጥ ወይም ለስታትስቲክስ መስሪያ ቤት ሥራውን ለማከናወን በሚያስፈልገው

relating to a tax law under any other law;

c) the Commission or a court in proceedings to establish a person's tax liability, or liability for penalty or late payment interest, or in a criminal case;

d) supplying to a foreign ministry as Federal Government has entered an agreement providing for the exchange of information, to the extent permitted under that agreement;

e) the Auditor-General when the disclosure is necessary to the performance of official duties by the Auditor-General;

f) the Federal Attorney General as well as Regional justice Bureau when the disclosure is necessary to the performance of its official duties;

g) the Regional Bureau when the disclosure is necessary to the performance of its Official duties;

h) a person in the service of the Government in a revenue or statistical department or conducting research when the disclosure is necessary to the performance of official duties by the person and provided the disclosure does not identify a specific person;

መጠን የሚሰጥ መረጃ፤

ቀ) መረጃ የሚመለከተው ሰው በጽሁፍ ፈቃዱን ከገለጸ ለሌላ ለማንኛውም ሰው፤

በ) በሌላ ማናቸውም ህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ማንኛውንም መረጃ የሚቀበል ሰው፡

ሀ) መረጃው የተገለፀበትን ዓላማ ለማሳካት ካልሆነ በስተቀር የመረጃውን ሚስጢራዊነት መጠበቅ፤

ለ) መረጃውን የያዙትን ማንኛውንም ሰነዶች ለቢሮው የመመለስ፣ ግዴታ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ "የታክስ ሠራተኛ" የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ) የቢሮው አማካሪ ቦርድ አባል የሆነ ወይም የነበረ፣

ለ) ሥራ ተቋራጭን ጨምሮ በማንኛውም ደረጃ በቢሮው የተቀጠረ ወይም በቢሮው በአንድ ሥራ ላይ እንዲሠማሩ የተደረገ ማንኛውም ሰው፤

ሐ) የቢሮው የቀድሞ ሠራተኛ፣ ተቀጣሪ ወይም ሥራ ተቋራጭ፤

## ክፍል ሦስት
## ታክስ ከፋዮች

### ምዕራፍ አንድ
### ስለምዝገባ

i) any other person with the written consent of the person to whom the information relates;

j) an organ authorized by any law.

3. A person receiving any information under sub-article (2) of this Article shall:

a) maintain the secrecy of the information except to the minimum extent necessary to achieve the object for which the disclosure was permitted;

b) return any documents reflecting the information to the Bureau.

4. In this Article, "Tax officer" includes:

a) a member or former member of the Advisory Board of the Bureau;

b) a person employed or engaged by the Bureau in any capacity including as contractor;

c) a former officer, employee, or contractor of the Bureau.

## PART THREE
## TAXPAYERS

### CHAPTER ONE
### REGISTRATION

## 9. ታክስ ከፋዮችን ስለመመዝገብ

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) እንደተጠበቁ ሆነው፣ አስቀድሞ የተመዘገበ ካልሆነ በስተቀር በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሰው በቢሮው ዘንድ ለመመዝገብ ማመልከት አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ፣

   ሀ) በኢትዮጵያ የሚያገኘው ገቢ ብቻ በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 49 እና 51 መሠረት ግብር የሚከፈልበት በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው፣

   ለ) በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 62 (2) መሠረት ግብር የሚከፈልበት ገቢ ብቻ ያለው ግለሰብ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡
3. ተቀጣሪው አስቀድሞ የተመዘገበ ካልሆነ በስተቀር፣ ከቀጣሪው ጋር ውል የገባ ተቀጣሪ ይመዘገብ ዘንድ ቀጣሪው የማመልከት ግደታ አለበት፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ፣ ቀጣሪው እንዲመዘገብ ያላደረገው ተቀጣሪ በንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ካለበት የመመዝገብ ግዴታ ነጻ ሊያወጣው አይችልም፡፡
5. ለምዝገባ የሚቀርበው ማመልከቻ፣

   ሀ) ቢሮው ባጸደቀው ቅጽ መሠረት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

   ለ) የመስተዳደር ምክር ቤት

## 9. Registration of Taxpayers

1. Subject to sub-articles (2) and (3) of this Article, a person who becomes liable for tax under a tax law shall apply to the Bureau for registration unless the person is already registered.
2. Sub-article (2) of this Article shall not apply to:

   a) a non-resident if the only Ethiopian source income derived by the person is subject to Articles 49 and 51 of the Income Tax Proclamation; or

   b) an individual whose only income is subject to Article 62(2) of the Income Tax Proclamation.
3. An employer shall apply for registration of an employee entering into employment with the employer unless the employee is already registered.
4. Sub-article (3) of this Article shall not relieve the employee of the obligation to apply for registration under sub-article (1) of this Article should the employer fail to make the application for the employee.
5. An application for registration shall be:

   a) made in the approved form by the Bureau;

   b) accompanied by documentary evidence of the person's identity,

በሚያወጣው ደንብ በሚወሰነው መሠረት የጣት አሻራ መለያን ጨምሮ የግለሰቡን ማንነት ከሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤

ሐ) ታክስ ከፋዩ ለታክስ የመመዝገብ ግዴታ ካለበት ቀን አንስቶ በ21 ቀናት ውስጥ ወይም ቢሮው በፈቀደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 መሠረት ቀጣሪው ለተቀጣሪው የሚያመለክት በሚሆንበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5(ለ) መሠረት የሚጠየቀው የማንነት መለያ በተቀጣሪው መቅረብ ይኖርበታል፡፡
7. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ያለበት ለምዝገባ የማመልከት ግዴታ ይኸው ሰው በሌላ ታክስ ሕግ ለአንድ ለተለየ ታክስ ካለበት የመመዝገብ ግዴታ ወይም ካለው አማራጭ በተጨማሪ ነው፡፡
8. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት ለመመዝገብ ያመለከተው ሰው በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ሲያምንበት ይመዘግበዋል፤ ለዚህ ሰውም በፀደቀው ቅጽ መሠረት የምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ ይሰጠዋል፡፡

including biometric identifier, as may be specified in the Regulations;

c) made within 21 days of becoming liable to apply for registration or within such further period as the Bureau may allow.

6. In the case of an application made by an employer for an employee under sub-article (3) of this Article, the biometric identifier required under sub-article (5)(b) of this Article shall be provided by the employee.
7. Subject to sub-article (10) of this Article, the obligation of a person to apply for registration under sub-article (1) of this Article shall be in addition to an obligation or option of the person to apply for registration for the purposes of a particular tax under another tax law.
8. The Bureau shall register a person who has applied for registration under sub-article (1) of this Article if satisfied that the person is liable for tax under a tax law and issue the person with a registration certificate in the approved form.

9. ቢሮው ለመመዝገብ ማመልከቻ ያቀረበውን ሰው ጥያቄ ያልተቀበለው ከሆነ የምዝገባውን ጥያቄ የማይቀበለው መሆኑን ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 14 ቀናት ውስጥ ለምዝገባ ላመለከተው ሰው በጽሁፍ ያሳውቀዋል።

10. አንድ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለመመዝገብ ሲያመለክት ያቀረበውን ማስረጃ ይህ ሰው ተጨማሪ የምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ ማቅረብ ሳያስፈልገው ቢሮው ማስረጃውን ይህ ሰው በሌላ የታክስ ሕግ ለአንድ የተለየ ታክስ እንዲመዘገብ ያለበትን ግዴታ ወይም ለመመዝገብ የተሰጠውን ፈቃድ ለማሟላት ሊጠቀምበት ይችላል።

11. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10) ቢኖርም፤ ቢሮው የአንድን ሰው ተጨማሪ ምዝገባ በተሟላ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስፈልገውን ማንኛውንም ሌላ ተጨማሪ መረጃ ያቀርብ ዘንድ ይህንን ሰው ሊጠይቀው ይችላል።

12. በዚህ አንቀጽ መሠረት መመዝገብ ሲኖርበት ያልተመዘገበን ሰው ቢሮው በፀደቀው ቅጽ መሠረት መዝግቦ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሊሰጠው ይችላል።

13. በዚህ አንቀጽ መሠረት የአንድ ሰው ምዝገባ ተፈፃሚ የሚሆነው የዚህን ሰው ምዝገባ በሚያረጋግጠው የምስክር ወረቀት ላይ ከተመለከተው ቀን ጀምሮ ነው።

9. If the Bureau refuses to register a person who has applied for registration, the Bureau shall serve the person with written notice of the refusal within 14 days of the person filing the application for registration.

10. When a person has applied for registration under sub-article (1) of this Article, the Bureau shall use the information provided for the registration for the purposes of any other registration of that person required or permitted under a tax law for the purposes of a particular tax without the person being required to file any additional registration forms.

11. Despite sub-article (10) of this Article, the Bureau may request a person to provide any further information necessary to complete an additional registration of the person.

12. The Bureau may register a person who has failed to apply for registration as required under this Article and shall issue the person with a registration certificate in the approved form.

13. The registration of a person under this Article shall take effect from the date specified on the person's registration certificate.

**10.ለውጦችን ስለማሳወቅ**

1. ማንኛውም የተመዘገበ ሰው ከሚከተሉት ወስጥ ማንኛውንም ጉዳይ በተመለከተ ለውጥ ሲከሰት ለውጡ በተከሰተ በ30 (በሠላሳ) ቀናት ውስጥ ለቢሮው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤
   ሀ) ስሙ፣ ቋሚ አድራሻው ወይም የፖስታ አድራሻው፣ የተቋቋመበት መተዳደሪያ ደንብ ወይም ዋንኛ የሥራ እንቅስቃሴው ወይም እንቅስቃሴዎቹ፤
   ለ) ከቢሮው ጋር ግንኙነት የሚያደርግበት የባንክ አድራሻ፤
   ሐ) ከቢሮው ጋር ግንኙነት የሚያደርግበት የኤሌክትሮኒክ አድራሻ፣
   መ) ቢሮው በመመሪያ የሚወሰናቸው ሌሎች ዝርዝሮች፤
2. የተመዘገበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የለውጥ ማስታወቂያ ሲያቀርብ ይህ ሰው በሌላ የታክስ ሕግ ለአንድ ለተለየ ታክስ ካደረገው ምዝገባ ጋር በተያያዘ ተመሳሳይ ለውጦችን ማስታወቅን በተመለከተ የተጣለበትን የማስታወቅ ግዴታ እንደተወጣ ይቆጠራል፡፡

**11.ምዝገባን ስለመሰረዝ**

1. የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ለሁሉም የታክስ ሕጎች የተጣለበት የመመዝገብ ግዴታ ሲቋረጥ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ለቢሮው ማመልከት አለበት፣
2. ምዝገባን ለማሰረዝ የሚቀርበው ማመልከቻ

**10.Notification of Changes**

1. A registered person shall notify the Bureau, in writing, of a change in any of the following within 30 days of the change occurring:
   a) the person's name, physical or postal address, constitution, or principal activity, or activities;
   b) the person's banking details used for transactions with the Bureau;
   c) the person's electronic address used for communication with the Bureau;
   d) such other details as may be specified in a Directive issued by the Bureau.
2. The notification of changes under sub-article (1) of this Article by a registered person shall be treated as satisfying any obligation to notify the same changes in relation to a registration of the person for the purposes of a particular tax under another tax law.

**11.Cancellation of Registration**

1. A person who ceases to be required to be registered for the purposes of all the tax laws shall apply to the Bureau for cancellation of the person's registration.
2. An application for cancellation of registration shall be made:

ሀ) በፀደቀው ቅጽ መሠረት፣ እና

ለ) የተመዘገበው ሰው በሁሉም የታክስ ሕጐች የተጣለበት የመመዝገብ ግዴታ ከተቋረጠበት ቀን አንስቶ ባሉት 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ወይም ቢሮው በሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

3. አንድ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ ካቀረበ በሌላ የታክስ ሕግ ለአንድ የተለየ ታክስ የተደረገው ምዝገባ እንዲሰረዝለት ጭምር እንዳመለከተ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

4. አንድ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ ሲያቀርብ ቢሮው ይህ ሰው ሥራውን ያቆመ መሆኑንና በሁሉም የታክስ ሕጎች የመመዝገብ ግዴታ የሌለበት መሆኑን ካረጋገጠ በኂላ ለዚህ ሰው የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ምዝገባውን ይሰርዘዋል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተው ምዝገባ የተሠረዘ መሆኑን የሚገልፀው ማስታወቂያ ማመልከቻው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት 30 (ሰላሳ) ቀናት ለአመልካቹ መሰጠት የሚኖርበት ሲሆን፣ ቢሮውም የምዝገባ ይሰረዝልኝ ማመልከቻው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት 90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ የታክስ ከፋዩን የታክስ ጉዳዮች በተመለከተ የመጨረሻ ኦዲት ሊያደርግ ይችላል፡፡

a) in the approved form; and

b) Within 30 days of the person ceasing to be required to be registered for the purposes of all the tax laws or within such further time as the Bureau may allow.

3. An application by a person under sub-article (1) of this Article shall be treated as satisfying any obligation of the person to apply for cancellation of the person's registration for the purposes of a particular tax under another tax law.

4. The Bureau shall, by notice in writing, cancel the registration of a person who has applied under sub-article (1) of this Article when satisfied that the person has ceased all operations and is no longer required to be registered for the purposes of all the tax laws.

5. A notice of cancellation of registration under sub-article (4) of this Article shall be served on the applicant within 30 days of receipt of the application and the Bureau may conduct a final audit of the person's tax affairs within 90 days of service of the notice of cancellation of registration.

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት አንድ ሰው ምዝገባ እንዲሰረዝለት ጥያቄ ያላቀረበ እንደሆነ ቢሮው ይህ ሰው ሥራውን ሙሉ በሙሉ ማቆሙን እና ለታክስ ሕጐች ዓላማ የመመዝገብ ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንዲሁም የተፈጥሮ ሰው ከሆነ መሞቱን፣ ኩባንያ ከሆነም መፍረሱን፣ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ሕልውናው የተቋረጠ መሆኑን ሲያምንበት ለታክስ ከፋዩ ወይም ለታክስ እንደራሴው የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ምዝገባውን ይሰርዛል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) መሠረት የሚደረግ የአንድ ሰው ምዝገባ መሰረዝ በሌላ ታክስ ሕግ ለአንድ የተለየ ታክስ ዓላማ ሲባል የተደረገ ምዝገባ መሰረዝንም ይጨምራል፡፡

8. የአንድ ሰው የምዝገባ መሰረዝ ተፈጻሚ የሚሆነው ቢሮው በሰጠው የስረዛ ማስታወቂያ ላይ ከተጻፈው ቀን ጀምሮ ነው፡፡

9. የአንድ ሰው የምዝገባ መሰረዝ በሌላ ታክስ ሕግ አንድን የተለየ ታክስ የሚመለከት ሲሆን፣ በዚያ የታክስ ሕግ ምዝገባ መሰረዝን በሚመለከት የሠፈሩትን ግዴታዎች ማሟላት ግዴታ ይሆናል፡፡

6. If a person has failed to apply for cancellation of the person's registration as required under sub-article (1) of this Article, the Bureau shall, by notice in writing to the person or the person's tax representative, cancel the registration of the person when satisfied that the person has ceased all operations and is no longer required to be registered for the purposes of all the tax laws, including when the person is a natural person who has died, a company that has been liquidated, or any other person that has ceased to exist.

7. The cancellation of a person's registration under sub-article (4) or (5) of this Article shall include cancellation of any registration of the person for the purposes of a particular tax under another tax law.

8. The cancellation of a person's registration shall take effect from the date specified in the notice of cancellation served on the person by the Bureau.

9. When the cancellation of the registration of a person involves cancellation of the person's registration for the purposes of a particular tax under another tax law, the person shall comply with any requirements relating to cancellation of that registration as specified under that other tax law.

## ምዕራፍ ሁለት

## የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሮች

### 12. ታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር

ታክስ ከፋዮችን ለመለየት እንዲቻል ቢሮው በዚህ ምዕራፍ በተደነገገው መሠረት ለታክስ ሕጎች ዓላማ ሲባል ለተመዘገበ ሰው "የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር" በሚል የሚታወቅ ይሰጣል፣ ታክስ ከፋዩም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን የታክስ ሕጎች በሚያዙት መሠረት መጠቀም አለበት፡፡

### 13. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ስለመስጠት

1. ቢሮው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት ለታክስ ሕጎች ዓላማ ሲባል ለተመዘገቡ ሰዎች የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አዘጋጅቶ ይሰጣል፡፡
2. ለሁሉም የታክስ ሕጎች አንድ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሚሰጥ ሲሆን አንድ ታክስ ከፋይ በማንኛውም ጊዜ አንድ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ብቻ ይኖረዋል፡፡
3. ቢሮው ለታክስ ከፋዩ የታክስ መለያ ቁጥር የሚሰጠው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ማስታወቂያ በመላክ ይሆናል፡፡

### 14. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አጠቃቀም

1. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጠው ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን በማንኛውም የታክስ ማስታወቂያ፣ ማስታወቂያ ወይም ለታክስ ሕግ ዓላማ ሲባል በሚቀርብ ወይም ጥቅም ላይ በሚውል ሰነድ ወይም በታክስ ሕግ መሠረት በሚዘጋጅ ሰነድ ላይ መግለጽ ይኖርበታል፤ እንዲሁም ታክስ ከፋዩ ታክስ

## CHAPTER TWO

## TAXPAYER IDENTIFICATION NUMBER

### 12. Taxpayer Identification Number

For the purposes of identification, the Bureau shall issue a number, to be known as a taxpayer identification number ("TIN"), in accordance with this Chapter to a taxpayer registered for the purposes of the tax laws and the taxpayer shall use the TIN as required under the tax laws.

### 13. Issue of a TIN

1. The Bureau shall issue a TIN to a taxpayer registered for the purposes of the tax laws under Article 9 of this Proclamation.
2. A TIN shall be issued for the purposes of all tax laws and a tax payer shall have only one TIN at any time.
3. The Bureau issues a TIN to a taxpayer by serving the taxpayer with written notice of the TIN.

### 14. Use of a TIN

1. A taxpayer who has been issued with a TIN shall state the TIN on any tax declaration, notice, or other document filed or used for the purposes of a tax law, or as otherwise required under a tax law, including supplying the TIN to a withholding agent in respect of payments made by the agent to the taxpayer.

ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ላለበት ሰው ክፍያዎች በሚፈጽምበት ጊዜ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን መስጠት አለበት፡፡

2. የንግድ ሥራ ለመሥራት ፈቃድ ይሰጠው ዘንድ ማመልከቻ የሚያቀርብ ታክስ ከፋይ ፈቃድ ለሚሰጠው ቢሮ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን መስጠት አለበት፡፡
3. ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንኡስ 2 በተመለከተው መሠረት ፈቃዱን በሚያድስበት ጊዜ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ማቅረብ የሚጠበቅበት የመጀመሪያው የፈቃድ ማመልከቻ ከቀረበ ወዲህ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ የተቀየረ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
4. የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሚሰጥ የመንግሥት አካል ወይም ተቋም ታክስ ከፋዩ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ሳያቀርብ ፈቃድ መስጠት አይችልም፡፡
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ለተሰጠው ሰው ብቻ የሚያገለግል ስለሆነ በሌላ ሰው ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፡፡
6. የታክስ ወኪል የአንድን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ሊጠቀምበት የሚችለው፡-

    ሀ) የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ ባለቤት የሆነው ሰው የታክስ ወኪል የታክስ መለያ ቁጥሩን ለመጠቀም እንዲችል በጽሑፍ ሲፈቅድለት፣ እና
    ለ) የታክስ ወኪሉ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ለታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ ባለቤት የታክስ ጉዳዮች ብቻ

2. A tax payer applying for a licence to carry on a business or occupation shall be required to supply the taxpayer's TIN to the licensing Bureau.
3. A taxpayer shall supply the taxpayer's TIN on a renewal of a licence referred to in sub-article (2) of this Article only if the taxpayer's TIN has changed since the original application of the licence.
4. A licensing Bureau issuing a licence to carrying on a business or occupation shall not issue a licence to a taxpayer unless the taxpayer has supplied his TIN.
5. A TIN is personal to the taxpayer to whom it has been issued and, subject to sub-article (6) of this Article, shall not be used by another person.
6. The TIN of a taxpayer may be used by a licensed tax agent when:

    a) the tax payer has given written permission to the licensed tax agent to use the TIN; and
    b) the licensed tax agent uses the TIN only in respect of the tax affairs of the taxpayer.

ሲጠቀምበት ነው፡፡

15. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥርን ስለመሰረዝ

1. ቢሮው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የአንድን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ለመሠረዝ ይችላል፡-
   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 መሠረት የታክስ ከፋዩ ምዝገባ ሲሰረዝ፤
   ለ) የታክስ ከፋዩ እውነተኛ ማንነት ባልሆነ ማንነት የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ የተሰጠ እንደሆነ፤
   ሐ) ታክስ ከፋዩ ጥቅም ላይ ያለ ሌላ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ያለው እንደሆነ፤
2. ቢሮው በማንኛውም ጊዜ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የአንድን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር በመሰረዝ አዲስ የታክስ መለያ ቁጥር ሊሰጠው ይችላል፡፡

ምዕራፍ ሶስት

የታክስ እንደራሴዎች

16.የታክስ እንደራሴዎች ግዴታዎች

1. አንድ የታክስ እንደራሴ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብንና ታክስ መክፈልንም ጨምሮ የታክስ ሕግ በታክስ ከፋዩ ላይ የሚጥለውን ማንኛውም ግዴታ የመወጣት ኃላፊነት አለበት፡፡
2. አንድ ታክስ ከፋይ ሁለትና ከሁለት በላይ የታክስ እንደራሴዎች ያሉት እንደሆነ እያንዳንዱ የታክስ እንደራሴ በዚህ አንቀጽ ለተመለከቱት ግዴታዎች የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት አለበት፤ ሆኖም ግን ከታክስ

15. **Cancellation of a TIN**

1. The Bureau shall, by notice in writing, cancel the TIN of a taxpayer when satisfied that:-
   a) the tax payer's registration has been cancelled under Article 11 of this Proclamation;
   b) a TIN has been issued to the taxpayer under an identity that is not the taxpayer's true identity;
   c) The taxpayer had been previously issued with a TIN that is still in force;
2. The Bureau may, at any time, by notice in writing, cancel the TIN issued to a taxpayer and issue the taxpayer with a new TIN.

**CHAPTER THREE**

**TAX REPRESENTATIVES**

16. **Obligations of Tax Representatives**

1. A tax representative of a taxpayer shall be responsible for performing any obligation imposed by a tax law on the taxpayer, including the filing of tax declarations and payment of tax.
2. When there are two or more tax representatives of a taxpayer, each tax representative shall be jointly and severally liable for any obligations referred to in this Article but the obligations may be discharged

እንደራሴዎቹ መካከል አንዱ የታክስ ወኪል ግዴታዎችን መወጣት ይችላል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በታክስ ሕግ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በታክስ እንደራሴ መከፈል የሚኖርበት ታክስ በታክስ እንደራሴው ይዞታ ወይም ቁጥጥር ሥር ባለው ገንዘብ ወይም ሀብት መጠን ከታክስ እንደራሴው መሰብሰብ አለበት፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በታክስ እንደራሴው መከፈል የነበረበት ታክስ ሳይከፈል ሲቀር የታክስ እንደራሴው በታክስ እንደራሴነቱ ታክሱን ለመክፈል የግል ኃላፊነት የሚኖርበት የታክስ እንደራሴው፡-
   ሀ) የተቀበለውን ወይም ሊቀበለው የሚችለውንና ታክስ የሚከፈልበትን ገንዘብ ያጠፋ፣ ለሌላ ዓላማ ያዋለ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ፣
   ለ) የታክስ ከፋዩ ሀብት የሆኑ እና በታክስ እንደራሴው ይዞታ ሥር የነበሩ ወይም ታክስ መከፈል ከነበረበት ጊዜ በኋላ በይዞታው ሥር የሆኑ እና ለታክሱ ክፍያ ሊውሉ የሚችሉ ንብረቶችን ወይም ገንዘብ ያስተላለፈ ወይም በከፊል ለሌላ የሰጠ እንደሆነ ነው፡፡

5. የታክስ እንደራሴው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ለታክስ ክፍያ የግል ኃላፊነት የማይኖርበት፡

by any of them.

3. Except as provided otherwise under a tax law and subject to sub-article (4) of this Article, any tax that, by virtue of sub-article (1) of this Article, is payable by the tax representative of a taxpayer shall be recoverable from the tax representative only to the extent of the monies or assets of the taxpayer that are in the possession or under the control of the tax representative.

4. Subject to sub-article (5) of this Article, a tax representative shall be personally liable for the payment of any tax due by the tax representative in that capacity when, while the amount remains unpaid, the tax representative:
   a) alienates, charges, or disposes of any moneys received or accrued in respect of which the tax is payable; or
   b) disposes of or parts with any moneys or funds belonging to the taxpayer that are in the possession of the tax representative or which come to the tax representative after the tax is payable, when such tax could legally have been paid from or out of such moneys or funds.

5. A tax representative shall not be personally liable for tax under sub-article (4) of this Article if:

ሀ) በታክስ እንደራሴው የተከፈለው ገንዘብ የዋለው ለታክስ ከፋዩ ጥቅም ሲሆንና የተከፈለው ገንዘብ በሕግ ከታክስ ከፋዩ ታክስ የመክፈል ግዴታ ቅድሚያ ሲኖረው፤ ወይም

ለ) ገንዘቡ በተከፈለበት ጊዜ የታክስ እንደራሴው ታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳ ያለበት መሆኑን ካላወቀ ወይም ሊያውቅ የማይችል ከሆነ ነው።

6. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው የታክስ እንደራሴው በታክስ ከፋዩ ላይ በታክስ ሕግ የተጣለውን ማንኛውንም ግዴታ ሳይወጣ ቢቀር ታክስ ከፋዩ ካለበት ማንኛውም ግዴታ ነፃ ሊያደርገው አይችልም።

**ክፍል አራት**

**ስለሰነዶች**

**17. መዝገብ የመያዝ ግዴታዎች**

1. ለታክስ ሕግ ዓላማ ሲባል አንድ ታክስ ከፋይ በታክስ ሕግ መያዝ ያለባቸውን ሰነዶች በኤሌክትሮኒክ መልክ ጨምሮ የመያዝ ግዴታ ያለበት ሲሆን እነዚህም ሰነዶች የሚያዙት፡
   ሀ) በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ፣
   ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ፤ እና
   ሐ) የታክስ ከፋዩን የታክስ ግዴታ በግልጽ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ፣
   መሆን አለበት።

2. በታክስ ሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ታክስ ከፋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)

a) the monies were paid by the tax representative on behalf of a taxpayer and the amount paid has a legal priority over the tax payable by the taxpayer; or

b) at the time the monies were paid, the tax representative had no knowledge, and could not reasonably be expected to know, of the taxpayer's tax liability.

6. Nothing in this Article relieves a taxpayer from performing any obligation imposed on the taxpayer under a tax law that the tax representative of the taxpayer has failed to perform.

**PART FOUR**

**DOCUMENTS**

**17. Record-keeping Obligations**

1. A taxpayer shall, for the purposes of a tax law, maintain such documents (including in electronic format) as may be required under the tax law and the documents shall be maintained:
   a) in Amharic or English;
   b) in Ethiopia; and
   c) in a manner so as to enable the taxpayer's tax liability under the tax law to be readily ascertained.

2. Subject to sub-article (3) of this Article or a tax law providing otherwise, a taxpayer shall retain the documents referred to in sub-article (1) of this Article for the longer of:

የተመለከቱትን ሰነዶች ከሚከተሉት ረጅም ለሆነው ጊዜ ይዞ የማቆየት ግዴታ አለበት፡-

ሀ) በንግድ ህግ ለተወሰነው የሰነድ መያዣ የጊዜ ርዝማኔ፣ ወይም

ለ) ሰነዶቹ አግባብነት በሚኖራቸው የታክስ ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ለቢሮው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ለአምስት ዓመታት፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኂላ በአዋጁ መሠረት ለሚደረግ ክርክር ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ( 2) ከተመለከተው ጊዜ በፊት ተግባራዊ በሆነ ሕግ መሠረት ለሚደረግ ክርክር ሰነዱ የሚያስፈልግ ሲሆን ታክስ ከፋዩ ሁሉም ክርክሮች እስከሚጠናቀቁ ጊዜ ድረስ ሰነዱን ይዞ የማቆየት ግዴታ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ሰነድ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ካልቀረበ በቢሮው በጹሁፍ በሚሰጥ ማስታወቂያ በሚወሰነው ጊዜ ውስጥ ሰነዱ በቢሮው ተቀባይነት ባለው ተርጓሚ በታክስ ከፋዩ ወጪ ወደ አማርኛ ወይም ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉሞ እንዲቀርብ ቢሮው ታክስ ከፋዩን ሊያዘው ይችላል፡፡

5. ይህ አንቀጽ ቢኖርም፣ የፋይናንስ ቢሮ ባወጣው የዋጋ ማሸጋገሪያ መመሪያ ሰነድ አያያዝን በተመለከተ የተደነገጉት ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

a) the record-keeping period specified in the Commercial Code; or

b) 5 years from the date that the tax declaration for the tax period to which they relate was filed with the Bureau;

3. When, at the end of the period referred to in sub-article 2 of this Article, a document is necessary for a proceeding under the Proclamation or any other law commenced before the end of the period referred to under sub-article 2, the tax payer shall retain the document until the proceeding and any related proceedings have been completed.

4. When a document referred to sub-article (1) of this Article is not in Amharic or English, the Bureau may, by notice in writing, require the taxpayer to provide, at the taxpayer's expense, a translation into Amharic or English by a translator approved by the Bureau by the date specified in the notice.

5. Notwithstanding the provisions of this Article, the Transfer Pricing Directive to be issued by the Finance Bureau shall be applicable.

18. ሰነዶችን ስለመመርመር

በታክስ ሕግ መሰረት ሰነዶችን እንዲይዝ የሚገደድ ታክስ ከፋይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 በተመለከተው በማንኛውም ምክንያታዊ ጊዜ ውስጥ ሰነዶቹን ለቢሮው ምርመራ ዝግጁ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

19. ደረሰኞች

1. የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ደረሰኞች ከማሳተሙ በፊት የእነዚህን ደረሰኞች ዓይነትና ብዛት በቢሮው ማስፈቀድና ማስመዝገብ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የህትመት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ደረሰኞችን ለማሳተም ከታክስ ከፋዩ ጥያቄ ሲቀርብለት ደረሰኞቹን ከማተሙ በፊት የእነዚህ ደረሰኞች ዓይነትና መጠን በቢሮው የተፈቀደና የተመዘገቡ መሆናቸውን ማረጋግጥ አለበት፡፡
3. ማንኛውም የሂሣብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ለሚያከናውነው ግብይት ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
4. ቢሮው ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የሚያግዙ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

20.የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች

1. የመስተዳደር ምክር ቤት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪዎችን የሚመለከት ደንብ ያወጣል፡፡
2. ደንቡ የሚከተሉትን ጉዳዮች ሊደነግግ ይችላል፡-
   ሀ) ታክስ ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ

18. **Inspection of Documents**

A taxpayer required to maintain documents under a tax law shall make the documents available for inspection at all reasonable times by the Bureau during the period specified under Article 17 of this Proclamation.

19. **Receipts**

1. A taxpayer that has the obligation to maintain books of account shall register with the Bureau the type and quantity of receipts before having such receipts printed.
2. Any person operating a printing press engaged by a taxpayer to print receipts shall ensure that the type and quantity of receipts are registered with the Bureau before printing the receipts.
3. Any taxpayer that has an obligation to maintain books of account shall issue a receipt for any transaction.
4. The Bureau shall issue directives for the implementation of this Article.

20. **Sales Register Machines**

1. The Administrative Council shall issue Regulations on Sales Register Machines.
2. The Regulations may provide for the following:
   a) the obligatory use by taxpayers of sales register machines;

እንዳለባቸው፤

ለ) ታክስ ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የሚጠቀሙበትን ሁኔታዎች፤

ሐ) በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ታትሞ የሚወጣው ደረሰኝ ሊይዛቸው ስለሚገባ መረጃዎች፤

መ) የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው ተፈላጊ ባህሪያት፤

ሠ) የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አቅራቢዎች የሚያቀርቧቸው መሣሪያዎች እውቅና እንዲያገኙ መከተል ስለሚገባቸው ስነ-ሥርዓት እና አቅራቢዎቹ ስላለባቸው ግዴታ፤

ረ) ለታክስ ከፋይ የተሸጠን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ስለሚመዘገብበት ሁኔታ።

3. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፡-

ሀ) “የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሳሪያ” ማለት በሽያጭ መደበኛ ደረሰኝ ፋንታ የዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ሽያጭ የሚመዘግብና ለማንበብ ብቻ የሚቻል ማስታወሻን የሚያከማች በኤልክትሮኒክስ ዘዴ ፕሮግራም የሚደረግ ቺፕ የተገጠመበት በሰርኪዩት የተጋገረ ፕሮግራም የሚጠቀም መሣሪያ ነው።

ለ) “የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ” ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያን የሚተካ ኮምፒዩተራይዝድ የሆነ መሣሪያ ሲሆን፣ የደንበኞችን ትዕዛዝ፣ የትዕዛዙን አፈጻጸምና ሂደትና የዴቢትና ክሬዲት ካርድ ሂሳብን

b) the conditions for the use by taxpayers of sales register machines;

c) the information required to be included on a receipt produced by a sales register machine;

d) the required features of sales register machines;

e) the process for suppliers to apply for accreditation of sales register machines and the reporting obligations of such suppliers;

f) the registration of a sales register machine sold to a taxpayer.

3. For the purpose of this Article:

   a) “Cash register machine” means a machine that uses a firmware that is installed in an electronic programmable read only memory chip and can record the sale of goods or services in lieu of a regular sales receipt;

   b) “Point of sale machine” means a machine that is a computerised replacement for a cash register machine and having additional capability to record and track customers’ orders and debit and credit

የመመዝገብና የመከታተል፣ በክምችት ያለን ዕቃ የመቆጣጠርና የመሳሰሉትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል ተጨማሪ አቅም ያለው መሣሪያ ነው፡፡

ሐ) "የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ" ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ ነው፡፡

## ክፍል አምስት

## የታክስ ማስታወቂያዎች

### 21.የታክስ ማስታወቂያዎችን ስለማቅረብ

1. በታክስ ሕግ የታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታ የተጣለበት ሰው ማስታወቂያውን በፀደቀው ቅጽ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ በተመለከተው አኳኋን ማቅረብ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ቢሮው በሚሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ፡-
   ሀ) አስቀድሞ ለቢሮው ያቀረበውን የታክስ ማስታወቂያ የሚያሟላ የታክስ ማስታወቂያ፤ ወይም
   ለ) ቢሮው በሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ የተመለከቱ መረጃዎችን የያዘ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት፡፡
3. ቀደም ሲል የቀረበው የታክስ ማስታወቂያ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) ድንጋጌ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡
4. ቢሮው በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ከፋዩ

card accounts, manage inventory, and perform similar functions;

c) "Sales register machine" means a cash register machine and a point of sale machine.

## PART FIVE

## TAX DECLARATIONS

### 21.Filing of Tax Declarations

1. A taxpayer required to file a tax declaration under a tax law shall file the declaration in the approved form and in the manner provided for in the Regulation to be issued under this Proclamation.
2. Subject to sub-article (3) of this Article, the Bureau may, by notice in writing, require a taxpayer to file by the due date set out in the notice:
   a) a fuller declaration in relation to a tax declaration already filed to the Bureau; or
   b) such other tax declaration as the Bureau specifies in the notice.
3. Sub-article (2) (a) of this Article shall not apply when the tax declaration already filed is a self-assessment declaration.
4. The Bureau shall not be bound by a tax

ስም በቀረበ የታክስ ማስታወቂያ አይገደድም፡፡ ስለሆነም ቢሮው ባገኘው ማንኛውም አስተማማኝ እና ሊረጋገጥ የሚችል መረጃ ላይ በመመሥረት ታክስ ከፋዩ መክፈል ያለበትን የታክስ መጠን ሊወስን ይችላል፡፡

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 እና የዚህ አዋጅ አንቀጽ 82 እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ታክስ ከፋይ በሚያቀርበው የታክስ ማስታወቂያ ላይ መፈረም የሚኖርበት ሲሆን የታክስ ማስታወቂያውም ማስታወቂያው እና ተያያዥ ሰነዶችም የተሟሉና ትክክለኛ መሆናቸውን ታክስ ከፋዩ የሚያረጋግጥበትን መግለጫ መያዝ አለበት፡፡

6. ታክስ ከፋዩ፡-
   ሀ) ግለሰብ ካልሆነ፣
   ለ) ችሎታ የሌለው ግለሰብ ከሆነ፣ ወይም
   ሐ) የታክስ ማስታወቂያውን በሌላ ምክንያት ለመፈረም የማይችል ግለሰብ ሲሆንና ለታክስ ወኪሉ ወይም ለታክስ እንደራሴው በጽሑፍ የውክልና ሥልጣን የሰጠው ከሆነ፣ የታክስ ከፋዩ የታክስ ወኪል ወይም የታክስ እንደራሴው የታክስ ማስታወቂያውን ሊፈርም እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት የማረጋገጫ መግለጫ ሊሰጥ ይችላል፡፡

7. የታክስ ማስታወቂያው በታክስ ከፋዩ የታክስ ወኪል ወይም በታክስ እንደራሴው የተፈረመ ሲሆን ታክስ ከፋዩ የማስታወቂያውን ይዘት እንደሚያውቅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) እንደተመለከተው ስለማስታወቂያው

declaration or information provided by, or on behalf of, a taxpayer. The Bureau may determine a taxpayer's tax liability based on any reliable and verifiable sources of information available.

5. Subject to sub-article (6) of this Article and Article 82 of this Proclamation, a taxpayer shall sign a tax declaration filed by him and the tax declaration shall contain a representation by the taxpayer that the declaration, including any attached material, is complete and accurate.

6. when the taxpayer is:
   a) not an individual;
   b) an incapable individual; or
   c) an individual who is otherwise unable to sign the declaration provided the taxpayer has provided the representative or tax agent with Bureau in writing to sign the declaration, a taxpayer's tax representative or licensed tax agent shall sign the taxpayer's tax declaration and make the representation referred to in sub-article (5) of this Article

7. When a tax declaration is signed by the taxpayer's tax representative or licensed tax agent, the taxpayer shall be deemed to know the contents of the declaration and shall be treated as having made the representation as to completeness and accuracy referred to in sub-

የተሟላ እና ትክክለኛ ስለመሆኑ ማረጋገጫ እንደሰጠ ይቆጠራል፡፡

article (5) of this Article.

**22. የታክስ ወኪል ስለሚሰጠው የታክስ ማስታወቂያ ማረጋገጫ**

1. የታክስ ከፋይን የታክስ ማስታወቂያ የሚያዘጋጅ ወይም በታክስ ማስታወቂያ ዝግጅት ድጋፍ የሚያደርግ የታክስ ወኪል የታክስ ከፋዩን ሰነዶች መመርመሩን እና እስከሚያውቀው ድረስ የታክስ ማስታወቂያውና ተያያዥ ሰነዶች የታክስ ማታወቂያው የሚመለከታቸውን መረጃዎች እና ግብይቶች በትክክል የሚያሳዩ መሆኑን የሚያረጋግጥ በፀደቀው ቅጽ መሠረት የተዘጋጀ የምስክር ወረቀት ለታክስ ከፋዩ መስጠት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን የምስክር ወረቀት ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ የታክስ ወኪል የምስክር ወረቀቱን መስጠት ያልፈለገበትን ምክንያት የያዘ የጽሁፍ መግለጫ ለታክስ ከፋዩ መስጠት አለበት፡፡
3. የታክስ ከፋይን የታክስ ማስታወቂያ የሚያዘጋጅ ወይም በታክስ ማስታወቂያ ዝግጅት ድጋፍ የሚያደርግ የታክስ ወኪል ከታክስ ማስታወቂያው ጋር በተገናኘ ለታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የምስክር ወረቀት የሰጠ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት መግለጫ የሰጠ መሆኑን በታክስ ማስታወቂያው ላይ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

**22. Licensed Tax Agent Certification of Tax Declaration**

1. A licensed tax agent who prepares or assists in the preparation of a tax declaration of a taxpayer shall provide the taxpayer with a certificate, in the approved form, certifying that the tax agent has examined the documents of the taxpayer and that, to the best of his knowledge, the declaration together with any accompanying documentation, correctly reflects the data and transactions to which it relates.
2. A licensed tax agent who refuses to provide a certificate referred to in sub-article (1) of this Article shall provide the taxpayer with a statement in writing of the reasons for such refusal.
3. A licensed tax agent who prepares or assists in the preparation of a tax declaration of a taxpayer shall specify in the declaration whether a certificate under sub-article (1) of this Article or a statement under sub-article (2) of this Article has been provided to the taxpayer in relation to the declaration.

4. የታክስ ወኪል በዚህ አንቀጽ መሠረት የሰጠውን የምስክር ወረቀት ወይም መግለጫ ቅጂ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 (2) ለተወሰነው ጊዜ ይዞ ማቆየት ያለበት ሲሆን ቢሮው በጽሑፍ ሲጠይቀው ቅጂውን ለቢሮው ማቅረብ አለበት፡፡

4. A licensed tax agent shall keep a copy of certificates or statements provided to taxpayers under this Article for the period specified in Article 17 (2) of this Proclamation and shall, when required to do so by notice in writing from the Bureau, produce the copy to the Bureau.

## 23. የታክስ ማስታወቂያዎችን አስቀድሞ ስለማቅረብ

1. ሥራውን ያቋረጠ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ሥራውን ያቋረጠ መሆኑን ሥራውን ካቆመበት ቀን ጀምሮ በ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ለቢሮው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚመለከተው ታክስ ከፋይ ሥራውን ባቆመ በ60 (ስልሳ) ቀናት ውስጥ ወይም ቢሮው ለታክስ ከፋዩ በሚሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ በሚወስነው ከዚያ ባነሰ ጊዜ ውሰጥ፡-

ሀ) ታክስ ከፋዩ ሥራውን ላቆመበት የታክስ ጊዜ ወይም የታክስ ማስታወቂያ ጊዜው ላልደረሰ ከዚያ በፊት ለነበረ የታክስ ጊዜ የቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ፣ እና

ለ) በቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያው መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ታክስ መክፈል፣ አለበት፡፡

3. ማንኛውም ታክስ ከፋይ ከኢትዮጵያ ሊወጣ ከሆነና የታክስ ከፋዩ ከኢትዮጵያ መውጣት በጊዜያዊነት አለመሆኑ የሚገመት ከሆነ ታክስ ከፋዩ ከኢትዮጵያ ከመውጣቱ በፊት፡

ሀ) የወቅቱን የታክስ ማስታወቂያ እና

## 23. Advance Tax Declarations

1. A taxpayer who ceases to carry on any activity shall notify the Bureau, in writing, of the cessation within 30 days of the date that the taxpayer ceased to carry on the activity.
2. A taxpayer to whom sub-article (1) of this Article applies shall, within 60 days after the date that the taxpayer ceased to carry on the activity or within such lesser period as the Bureau may require by notice in writing to the taxpayer:

a) file an advance tax declaration for the tax period in which the taxpayer ceased to carry on the activity and for any prior tax period for which the due date for filing has not arisen; and

b) Pay the tax due under the advance tax declaration at the time of filing the declaration.

3. If a taxpayer is about to leave Ethiopia during a tax period and the taxpayer's absence is unlikely to be temporary, the taxpayer shall, before leaving:

a) file an advance tax declaration for

ከኢትዮጵያ በሚወጣበት ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ የማቅረቢያ ጊዜው ላልደረሰው ከዚያ በፊት ለነበረው የታክስ ጊዜ የቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ፣ እና

ለ) በቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያው መሠረት መከፈል የሚገባውን ታክስ መክፈል ወይም ታክሱ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለቢሮው አጥጋቢ በሆነ አኳኋን ማመቻቸት፣ አለበት።

4. በማንኛውም የታክስ ጊዜ ታክስ ከፋዩ የታክስ ጊዜውን የታክስ ማስታወቂያ ማቅርብ በሚገባው ጊዜ አያቀርብም ብሎ ማመን የሚያስችል ምክንያት ሲኖረው ቢሮው ለታክስ ከፋዩ የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት፡-

ሀ) ታክስ ከፋዩ ወይም የታክስ እንደራሴው የታክስ ጊዜው የታክስ ማስታወቂያ ማቅረቢያ ጊዜ ባይደርስም ቢሮው በሰጠው ማስታወቂያ በተመለከተው ጊዜ የቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያ እንዲያቀርብ፣ እና

ለ) በቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያው የተመለከተውን ታክስ ቢሮው በሰጠው ማስታወቂያ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል ሊያዝ ይችላል።

5. ታክስ ከፋዩ ከአንድ የታክስ ዓይነት በላይ የሚመለከተው ከሆነ ይህ አንቀጽ ለእያንዳንዱ ታክስ በተናጠል ተፈጻሚ ይሆናል።

the tax period and for any prior tax period for which the due date for filing has not arisen by the time the taxpayer leaves; and

b) pay the tax due under the advance tax declaration at the time of filing the declaration or make an arrangement satisfactory to the Bureau for the payment of the tax due.

4. If, during a tax period, the Bureau has reason to believe that a taxpayer will not file a tax declaration for the period by the due date, the Bureau may, by notice in writing and at any time during the tax period, require:

a) the taxpayer or the taxpayer's tax representative to file an advance tax declaration for the tax period by the date specified in the notice being a date that may be before the date that the tax declaration for the tax period would otherwise be due; and

b) Pay any tax payable under the advance tax declaration by the due date specified in the notice by the Bureau.

5. If a taxpayer is subject to more than one tax, this Article shall apply separately for each tax.

6. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ “ሥራ” ማለት ንግድ ወይም ማንኛውም በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ የሚከፈልበትን ገቢ የሚያስገኝ ሌላ ሥራ ሲሆን የመጨረሻ ታክስ ሆኖ ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ለቢሮው የሚተላለፍ ታክስ የሚከፈልበትን ገቢ የሚያስገኝ ሥራን አይጨምርም፡፡

### 24. በአግባቡ የቀረበ የታክስ ማስታወቂያ

ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ከፋዩ ስም ቀርቧል የተባለ የታክስ ማስታወቂያ በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ከፋዩ ፈቃድ እንደቀረበ ይቆጠራል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የታክስ ስሌቶች

### 25. በታክስ ከፋዩ ስለሚዘጋጅ የታክስ ስሌት

1. በፀደቀው ቅጽ መሠረት ለአንድ የታክስ ጊዜ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ያቀረበ የራሱን ታክስ ስሌት የሚያዘጋጅ ታክስ ከፋይ በታክስ ስሌት ማስታወቂያው የገለፀው መጠን ለማንኛውም የዚህ አዋጅ ዓላማዎች የታክስ ማስታወቂያው ተፈጻሚ ለሚሆንበት የታክስ ጊዜ ዜሮን ጨምሮ ሊከፈል የሚገባውን የታክስ መጠን ስሌት እንዳቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡
2. በፀደቀው ቅጽ መሠረት ለአንድ የታክስ ጊዜ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ያቀረበ የራሱን የታክስ ስሌት የሚያዘጋጅ በገቢ ግብር አዋጅ ሠንጠረዥ “ለ” ወይም “ሐ” መሠረት ታክስ የሚከፈልበትን ገቢ የሚያገኝ ታክስ ከፋይ በዚሁ የታክስ ጊዜ

6. In this Article, “activity” means a business or any other activity-giving rise to income subject to tax under a tax law, other than an activity-giving rise to income subject to withholding tax as a final tax.

### 24. Tax Declaration Duly Filed

A tax declaration that is purported to be filed by or on behalf of a taxpayer shall be treated as having been filed by the taxpayer or with the taxpayer’s consent unless the contrary is proved.

## PART SIX

## TAX ASSESSMENTS

### 25. Self-assessments

1. A self-assessment taxpayer who has filed a self-assessment declaration in the approved form for a tax period shall be treated, for all purposes of this Proclamation, as having made an assessment of the amount of tax payable (including a nil amount) for the tax period to which the declaration relates being that amount as set out in the declaration.
2. When a self-assessment taxpayer liable for income tax under Schedule ‘B’ or ‘C’ of the Income Tax Proclamation has filed a self-assessment declaration in the approved form for a tax period and the taxpayer has a loss for the year, the taxpayer shall be treated, for all

ኪሣራ የገጠመው እንደሆነ በታክስ ስሌት ማስታወቂያው የገለፀው የኪሣራ መጠን ለማንኛውም የዚህ አዋጅ ዓላማዎች የታክስ ማስታወቂያው ተፈጻሚ ለሚሆንበት የታክስ ጊዜ ያጋጠመውን የኪሣራ ስሌት እንዳቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

3. በፀደቀው ቅጽ መሠረት ለአንድ የታክስ ጊዜ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ያቀረበ የራሱን የታክስ ስሌት የሚያዘጋጅ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ታክስ ከፋይ፣ በዚሁ የታክስ ጊዜ በግብዓት ላይ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቅላላ መጠን የተጨማሪ እሴት ታክስ ከሚከፈልበት ሽያጭ ላይ ከሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቅላላ መጠን የበለጠ እንደሆነ፣ በታክስ ስሌት ማስታወቂያው የገለፀው የታክስ መጠን ለማንኛውም የዚህ አዋጅ ዓላማዎች የታክስ ማስታወቂያው ተፈጻሚ ለሚሆንበት የታክስ ጊዜ ታክስ ከሚከፈልበት ሽያጭ ላይ ከሰበሰበው ታክስ በላይ የግብዓት ታክስ መክፈሉን የሚገልጽ የስሌት ማስታወቂያ እንዳቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

4. የታክስ ማስታወቂያ፡-
   ሀ) ቅጹ በቢሮው አስቀድሞ የተሞላ መረጃ የያዘ ቢሆንም፣
   ለ) ሊከፈል የሚገባው ታክስ መረጃ በቅጹ ውስጥ እየተሞላ ሳለ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የተሰላ ቢሆንም፣ በፀደቀው ቅጽ መሠረት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ተሞልቶ በታክስ ከፋይ

purposes of this Proclamation, as having made an assessment of the amount of the loss being that amount as set out in the declaration.

3. When a self-assessment taxpayer has filed a Value Added Tax return in the approved form for a tax period and the taxpayer's total input tax for the period exceeds the taxpayer's total output tax for the period, the taxpayer shall be treated, for all purposes of this Proclamation, as having made an assessment of the amount of the excess input tax for the period being that amount as set out in the declaration.

4. A tax declaration despite the following:
   a) the form included pre-filled information provided by the Bureau;
   b) the tax payable is computed electronically as information is inserted into the form, in the approved form completed and filed electronically by a

የቀረበ የታክስ ማስታወቂያ የራሱን የታክስ ስሌት በሚያዘጋጅ ታክስ ከፋይ እንደቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

taxpayer is a self-assessment return.

## 26. በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት

1. ማንኛውም ታክስ ከፋይ በታክስ ሕግ መሠረት በማንኛውም የታክስ ጊዜ ማቅረብ የሚገባውን የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ እንደሆነ ቢሮው በማንኛውም ጊዜ የሚያገኘውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ለታክስ ጊዜው ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ በግምት ("የግምት ስሌት" ተብሎ የሚጠራ) ማስላት የሚችል ሲሆን የግምት ስሌቱ የሚከተሉትን ይመለከታል፡-
   ሀ) የገቢ ግብር አዋጅ ሠንጠረዥ "ለ" ና "ሐ" ኪሳራን በሚመለከት የታክስ ጊዜውን የኪሳራ መጠን፣
   ለ) በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሠረት በግብዓት ላይ በብልጫ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስን በሚመለከት ለታክስ ጊዜው በግብዓት ላይ በብልጫ የተከፈለውን የታክስ መጠን፣
   ሐ) በሌላ ማንኛውም ሁኔታ ዜሮ መጠንን ጨምሮ በታክስ ጊዜው ሊከፈል የሚገባውን የታክስ መጠን፡፡
2. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ታክሱ በግምት ለተሰላው ታክስ ከፋይ የሚከተሉትን ዝርዝር ነጥቦች ያካተተ የታክስ ግምት ስሌት ማስታወቂያ መስጠት አለበት፡-
   ሀ) እንደሁኔታው የተሰላውን የታክስ

## 26. Estimated Assessments

1. When a taxpayer has failed to file a tax declaration for a tax period as required under a tax law, the Bureau may, based on such evidence as may be available and at any time, make an assessment (referred to as a "estimated assessment") of:
   a) in the case of a loss under Schedule 'B' or 'C' of the Income Tax Proclamation, the amount of the loss for the tax period;
   b) in the case of an excess amount of input tax under the Value Added Tax Proclamation, the amount of the excess input tax for the tax period; or
   c) in any other case, the amount of tax payable (including a nil amount) for the tax period.
2. The Bureau shall serve a taxpayer assessed under sub-article (1) of this Article with notice, in writing, of an estimated assessment specifying the following:
   a) the amount of tax assessed, or loss or

መጠን፣ ወደፊት የሚሸጋገር የኪሣራ ወይም በብልጫ የተከፈለን የግብዓት ታክስ መጠን፣

ለ) በተሰላው ታክስ ላይ ሊከፈል የሚገባ የቅጣት መጠን ካለ፣

ሐ) በተሰላው የታክስ መጠን ላይ ሊከፈል የሚገባ የዘገየ ክፍያ ወለድ መጠን ካለ፣

መ) የታክስ ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ጊዜ፤

ሠ) ማስታወቂያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ታክሱ፣ ቅጣቱ እና ወለዱ የሚከፈልበትን ቀን፤

ረ) ቅሬታ ማቅረብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ጨምሮ በታክስ ግምት ስሌቱ ላይ ቅሬታውን የሚያቀርብበትን አኳሃን፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚሰጠው የታክስ ግምት ስሌት ማስታወቂያ ታክሱን በሚጥለው የታክስ ሕግ መሠረት በተዘጋጀው የታክስ ግምት ስሌት ሊከፈል የሚገባው ታክስ የሚከፈልበትን ጊዜ ("የመጀመሪያው የታክስ መክፈያ ጊዜ" ተብሎ የሚጠቀስ) ሊለውጥ የማይችል ሲሆን፣ የታክስ ክፍያው በመዘግየቱ ምክንያት የሚጣል ቅጣትና ወለድ መታሰብ የሚጀምሩት ከመጀመሪያው የመክፈያ ጊዜ አንስቶ ይሆናል።

4. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ የሚሆነው በታክስ ስሌት ለሚሰበሰብ ታክስ ብቻ ነው።

5. ይህ አንቀጽ በቢሮው የተዘጋጀ የታክስ ግምት ስሌት የደረሰው ማንኛውም ታክስ ከፋይ

excess input tax carried forward, as the case may be;

b) the amount assessed as penalty (if any) payable in respect of the tax assessed;

c) the amount of late payment interest (if any) payable in respect of the tax assessed;

d) the tax period to which the assessment relates;

e) the due date for payment of the tax, penalty, and interest being a date that is within 30 days from the date of service of the notice;

f) the manner of objecting to the assessment, including the time limit for lodging an objection to the assessment.

3. The service of a notice of an estimated assessment under sub-article (2) of this Article shall not change the due date (referred to as the "original due date") for payment of the tax payable under the assessment as determined under the tax law imposing the tax, and late payment penalty and late payment interest remain payable based on the original due date.

4. This Article shall apply only for the purposes of a tax that is collected by assessment.

5. Nothing in this Article relieves a taxpayer from being required to file the

የግምት ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታውን አያስቀርም፡፡

6. በቢሮው የተዘጋጀ የታክስ ግምት ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከደረሰው በኋላ ለዚያ የታክስ ጊዜ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የታክስ ማስታወቂያ ለታክስ ጊዜው እንደቀረበ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ሆኖ አይቆጠርም፡፡
7. ቢሮው በማንኛውም ጊዜ በግምት ላይ የተመሠረተ የታክስ ስሌት ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡
8. ቢሮው ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የሚያግዙ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 27. የስጋት የታክስ ስሌት

1. ቢሮው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 ወይም 42 በተመለከቱት ሁኔታዎች በአንድ የታክስ ጊዜ ማንኛውም ታክስ ከፋይ መክፈል ለሚገባው ታክስ በሚያገኘው ማስረጃ ላይ በመመሥረት የስጋት ታክስ ስሌት ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው፡-
   ሀ) ታክስ ከፋዩ ለታክስ ጊዜው የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ እንደሆነ፣ እና
   ለ) ታክሱ በታክስ ስሌት የሚሰበሰብ ሲሆን ብቻ ነው፡፡
3. የስጋት ታክስ ስሌት: -
   ሀ) ታክስ ከፋዩ ለታክስ ጊዜው የታክስ ማስታወቂያ የሚያቀርብበት ቀን ከመድረሱ በፊት ሊዘጋጅ ይችላል፣ እንዲሁም
   ለ) በሚዘጋጅበት ጊዜ ፀንቶ ባለ ሕግ መሠረት መዘጋጀት አለበት፡፡

tax declaration to which an estimated assessment served under this Article relates.

6. A tax declaration filed by a taxpayer for a tax period after notice of an estimated assessment has been served on the taxpayer prepared by the Bureau for the period is not a self-assessment declaration.
7. The Bureau may make an estimated assessment at any time.
8. The Bureau may issue directives for the implementation of this Article.

### 27. Jeopardy Assessments

1. The Bureau may, based on such evidence as may be available, make a “jeopardy assessment” of the tax payable by a taxpayer in the circumstances specified in Article 23 or 42 of this Proclamation for a tax period.
2. Sub-article (1) of this Article applies only when:
   a) the taxpayer has not filed a tax declaration for the tax period; and
   b) the tax is collected by assessment.
3. A jeopardy assessment:
   a) may be made before the date on which the taxpayer’s tax declaration for the period is due; and
   b) shall be made in accordance with the law in force at the date the jeopardy assessment

4. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የስጋት ታክስ ስሌት ለተዘጋጀለት ታክስ ከፋይ የሚከተሉትን ዝርዝር ነጥቦች ያካተተ የስጋት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ በጽሑፍ መስጠት አለበት፡-
   ሀ) የተሰላውን የታክስ መጠን፤
   ለ) በተሰላው የታክስ መጠን ላይ የሚከፈል ቅጣት ካለ፣
   ሐ) የታክስ ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ጊዜ፣
   መ) ታክሱና ቅጣቱ የሚከፈልበትን ጊዜ፣ ይህ ጊዜ የታክሱ የመክፈያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ሊሆን ይችላል፣
   ሠ) ቅሬታ ማቅረብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ጨምሮ በስጋት ታክስ ስሌቱ ላይ ቅሬታውን የሚያቀርብበትን አኳኋን፣
5. ቢሮው ለታክስ ከፋዩ በሚሰጠው የስጋት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ታክሱ እና ቅጣቱ ወዲያውኑ እንዲከፈሉ ሊያዝ ይችላል።
6. ይህ አንቀጽ በቢሮው የተዘጋጀ የስጋት ታክስ ስሌት የደረሰው ማንኛውም ታክስ ከፋይ የስጋት ታክስ ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታውን አያስቀርም።
7. ታክስ ከፋዩ በአንድ የታክስ ጊዜ መክፈል ያለበትን ታክስ በሙሉ ማሰላት እንዲቻል የስጋት ታክስ ስሌት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 መሠረት ሊሻሻል ይችላል።

was made.

4. The Bureau shall serve a taxpayer assessed under sub-article (1) of this Article with notice, in writing, of the jeopardy assessment specifying the following:
   a) the amount of tax assessed;
   b) the amount assessed as penalty (if any) payable in respect of the tax assessed;
   c) the tax period to which the assessment relates;
   d) the due date for payment of the tax and penalty, which may be a date before the tax would otherwise be due for the tax period;
   e) the manner of objecting to the assessment, including the time limit for lodging an objection to the assessment.
5. The Bureau may specify in a notice of a jeopardy assessment that the tax and penalty due are payable immediately.
6. Nothing in this Article shall relieve a taxpayer from the requirement to file the tax declaration to which the jeopardy assessment that is prepared by the Bureau served under this Article relates.
7. A jeopardy assessment may be the subject of an amended assessment under Article 28 of this Proclamation so that the taxpayer is assessed in respect of the whole of the tax period to which the jeopardy assessment

relates.

8. የስጋት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከደረሰው በኋላ ለዚያ የታክስ ጊዜ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የታክስ ማስታወቂያ ለታክስ ጊዜው እንደቀረበ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ አይቆጠርም፡፡

8. A tax declaration filed by a taxpayer for a tax period after notice of a jeopardy assessment has been served on the taxpayer for the period is not a self-assessment declaration.

## 28. የተሻሻሉ የታክስ ስሌቶች

1. ይህ አንቀጽ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቢሮው፡-
   - ሀ) የገቢ ግብር አዋጅ ሠንጠረዥ “ለ” ወይም “ሐ” ን በተመለከተ የታክስ ከፋዩ ኪሳራ ለታክስ ጊዜው በትክክል የተሰላ መሆኑን፤
   - ለ) በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሠረት በብልጫ የተከፈለ የግብዓት ተጨማሪ እሴት ታክስ መጠንን በተመለከተ ታክስ ከፋዩ በታክስ ጊዜው በብልጫ የከፈለው የግብዓት ተጨማሪ እሴት ታክስ በትክክል የተሰላ መሆኑን፣
   - ሐ) በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ታክስ ከፋዩ ዜሮ መጠንን ጨምሮ ለታክስ ጊዜው መክፈል የሚገባው የታክስ መጠን በትክክል የተሰላ መሆኑን፣ ለማረጋገጥ በሚያገኘው ማስረጃ መሠረት ማንኛውንም የታክስ ስሌት (“የመጀመሪያው የታክስ ስሌት” ተብሎ የሚጠቀስ) በመለወጥ፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 28. Amended Assessments

1. Subject to this Article, the Bureau may amend:
   - a) in the case of a loss under Schedule ‘B’ or ‘C’ of the Income Tax Proclamation, the taxpayer is assessed in respect of the correct amount of the loss for the tax period;
   - b) in the case of an excess amount of input tax under the Value Added Tax Proclamation, the taxpayer is assessed in respect of the correct amount of the excess input tax for the tax period; or
   - c) in any other case, the taxpayer is liable for the correct amount of tax payable (including a nil amount) in respect of the tax period, the “original assessment”) by making such alterations, reductions, or additions, based on such evidence as may be available, to the original assessment of a taxpayer for a tax period.

2. አግባብነት ባለው የታክስ ሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር፣ ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማንኛውንም የታክስ ስሌት፣

   ሀ) በማንኛውም ጊዜ በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ከፋዩ ስም የማጭበርበር ድርጊት ሲፈጸም ወይም በከፍተኛ ሁኔታ ወይም በማወቅ የተፈፀመ የቸልተኝነት ድርጊት ሲኖር፣ ወይም

   ለ) በሌላ በማናቸውም ሁኔታ፡-

   1. ታክስ ከፋዩ በራሱ የሚያሰላው የታክስ ስሌት ሲሆን ታክስ ከፋዩ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያውን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 5 (አምስት) ዓመት ውስጥ፣
   2. ለሌላ ማንኛውም የታክስ ስሌት ቢሮው ለታክስ ከፋዩ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 5 (አምስት) ዓመት ውስጥ፣ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

3. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለታክስ ከፋዩ የሰጠውን የታክስ ስሌት ማሻሻያ ማስታወቂያ ከሚከተሉት ሁኔታዎች ዘግይቶ በተፈጸመው ጊዜ እንደገና ሊያሻሽል ይችላል፡፡

   (ሀ) ለመጀመሪያው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ፣ ወይም

2. Subject to a tax law specifying otherwise, the Bureau may amend a tax assessment under sub-article (1) of this Article:

   a) in the case of fraud, or gross or wilful neglect by, or on behalf of, the taxpayer, at any time; or

   b) in any other case, within 5 years of:

   1. for a self-assessment, from the date that the self-assessment taxpayer filed the self-assessment declaration in the five years;
   2. For any other tax assessment, from the date the Bureau served notice of the assessment on the taxpayer in the five years.

3. When the Bureau has served a taxpayer with notice of an amended assessment made under sub-article (1) of this Article, the Bureau may further amend the original assessment to which the amended assessment relates within the later of:

   a) the period specified in sub-article (2) (b) of this Article applicable to the original assessment; or

(ለ) ቢሮው የተሻሸለውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከሰጠው በኋላ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 (ለ) ተፈጻሚ በሚሆንበት በማናቸውም ሁኔታ ቢሮው የሚያደርገው ተጨማሪ ማሻሻያ መጀመሪያ በተሻሻለው የታክስ ስሌት ላይ በተደረጉት ለውጦች፣ ቅናሾች ወይም ጭማሪዎች ላይ ብቻ የተገደበ ይሆናል፡፡

5. ቢሮው በዚህ አንቀጽ መሠረት የተሻሻለውን የታክስ ስሌት በተመለከተ የሚከተሉትን ነጥቦች ያካተተ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ መስጠት አለበት፡-

ሀ) ማሻሻያ የተደረገበትን የመጀመሪያ የታክስ ስሌት እና ማሻሻያ ማድረግ ያስፈለገበትን ምክንያቶች የያዘ መግለጫ፣

ለ) እንደሁኔታው የተሰላውን የታክስ መጠን፣ወደፊት የሚሸጋገር የኪሣራ ወይም በብልጫ የተከፈለን የግብዓት ታክስ መጠን፣

ሐ) በተሻሻለ የታክስ ስሌት ላይ ሊከፈል የሚገባ የቅጣት መጠን ካለ፣

መ) በተሻሻለው የታክስ ስሌት ላይ ሊከፈል የሚገባ የዘገየ ክፍያ ወለድ መጠን ካለ፣

ሠ) የተሻሻለ የታክስ ስሌት የሚመለከተውን የታክስ ጊዜ፣

ረ) ማስታወቂያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ከ30 (ሰላሳ) ቀናት ባላነሰ

b) One year after the Bureau served notice of the amended assessment on the taxpayer.

4. In any case to which sub-article (3) (b) of this Article applies, the Bureau shall be limited to amending the alterations, reductions, or additions made in the amended assessment to the original assessment.

5. The Bureau shall serve a taxpayer with notice, in writing, of an amended assessment made under this Article specifying the following:

a) the original assessment to which the amended assessment relates and a statement of reasons for making the amended assessment;

b) the amount of tax assessed, or loss or excess input tax carried forward, as the case may be;

c) the amount of penalty assessed (if any) under the amended assessment;

d) the amount of late payment interest (if any) payable in respect of the tax assessed;

e) the tax period to which the amended assessment relates;

f) the due date for payment of any additional tax, and penalty and interest, payable under the amended

ጊዜ ውስጥ በተሻሻለው የታክስ ስሌት መሠረት መከፈል ያለበትን ተጨማሪ ታክስ፣ ቅጣት እና ወለድ የሚከፈልበትን ቀን፣

ሰ) ቅሬታ ማቅረብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ጨምሮ በተሻሻለው የታክስ ስሌት ላይ ቅሬታውን የሚያቀርብበትን አኳኋን፣

6. በተሻሻለው የታክስ ስሌት መሠረት መከፈል ያለበት ተጨማሪ ታክስ ካለ በተጨማሪው ታክስ ላይ ለዘገየ ክፍያ የሚከፈል ቅጣትና ወለድ የሚሰላው በመጀመሪያው የታክስ ስሌት መሠረት ታክሱ መከፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

### 29. ታክስ ከፋዩ ራሱ ያዘጋጀው የታክስ ስሌት እንዲሻሻል ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1. የራሱን የታክስ ስሌት ያዘጋጀ ታክስ ከፋይ ያቀረበውን በራስ የተዘጋጀ የታክስ ማስታወቂያ ቢሮው እንዲያሻሽልለት ለቢሮው ሊያመለክት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ፣

ሀ) ታክስ ከፋዩ ራሱ አዘጋጅቶ ባቀረበው የታክስ ማስታወቂያ ላይ ሊደረጉ ይገባል ብሎ የሚያምንባቸውን ማሻሻያዎችን እና ማሻሻያዎቹን ማድረግ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያቶች መግለጽ፣ እና

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 (2) (ለ) (1) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መቅረብ፣

assessment, being a date that is not less than 30 days from the date of service of the notice;

g) the manner of objecting to the amended assessment, including the time limit for lodging an objection to the assessment.

6. If an amount of additional tax is payable under an amended assessment, any late payment penalty and late payment interest payable in respect of the additional tax shall be computed from the original due date for payment of tax under the original assessment to which the amended assessment relates.

### 29. Application for Making an Amendment to a Self-assessment

1. A taxpayer who has filed a self-assessment declaration may apply to the Bureau for the Bureau to make an amendment to the self-assessment.
2. An application under sub-article (1) of this Article shall:

a) state the amendments that the taxpayer believes are required to be made to correct the self-assessment and the reasons for the amendments; and

b) be filed with the Bureau within the period specified in Article 28 (2) (b) (1) of this Proclamation.

ይኖርበታል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት ማመልከቻው በቀረበለት በ120 (አንድ መቶ ሃያ) ቀናት ውስጥ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በታክስ ከፋዩ ተዘጋጅቶ የቀረበው የታክስ ስሌት እንዲሻሻል መወሰን ወይም ማመልከቻውን ውድቅ ማድርግ አለበት፡፡

4. ቢሮው ታክስ ከፋዩ ራሱ ያቀረበው የታክስ ስሌት እንዲሻሻል የወሰነ እንደሆነ፣
   ሀ) የታክስ ስሌት ማሻሻያው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 (1) መሠረት መከናወን፣ እና
   ለ) የተሻሻለው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 (5) መሠረት ለታክስ ከፋዩ እንዲደርሰው መደረግ አለበት፡፡

5. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርበውን ማመልከቻ ያልተቀበለው እንደሆነ ውሳኔውን ለታክስ ከፋዩ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመሰብሰብና ማስከፈል

### ምዕራፍ አንድ

### ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

**30. ታክስ ለመንግሥት የሚከፈል ዕዳ ስለመሆኑ**

1. በታክስ ሕግ መሠረት በታክስ ከፋዩ ሊከፈል የሚገባውና የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ታክስ

3. When an application has been made under sub-article (1) of this Article, the Bureau shall, in accordance with a Directive issued by the Bureau, make a decision to amend the self-assessment or to refuse the application and such decision shall be made within 120 days of the receipt of the application.

4. If the Bureau makes a decision to amend the self-assessment:
   a) the amended assessment shall be made in accordance with Article 28 (1) of this Proclamation; and
   b) notice of the amended assessment shall be served on the taxpayer in accordance with Article 28 (5) of this Proclamation.

5. If the Bureau makes a decision to refuse an application under sub-article (1) of this Article, the Bureau shall serve the taxpayer with written notice of the decision.

## PART SEVEN

## COLLECTION AND RECOVERY OF TAX AND OTHER AMOUNTS

### CHAPTER ONE

### PAYMENT OF TAX AND OTHER AMOUNTS

**30. Tax as a Debt Due to the Government**

1. Tax that is due and payable by a taxpayer under a tax law is a debt owed to the Government and shall be payable

ለመንግሥት የሚከፈል ዕዳ ስለሆነ ለቢሮው መከፈል አለበት፡፡

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 82 (2) መሠረት በኤሌክትሮኒክስ አከፋፈል ዘዴ ታክስ እንዲከፍል በቢሮው የተጠየቀ ታክስ ከፋይ ቢሮው ሌላ የአከፋፈል ዘዴ እንዲጠቀም በጽሑፍ ካልፈቀደለት በስተቀር ክፍያውን የሚፈጽመው በኤሌክትሮኒክስ አከፋፈል ዘዴ ይሆናል፡፡

3. ታክስ ከፋዩ ታክሱን መክፈል ባለበት ጊዜ ካልከፈለ ቢሮው ያልተከፈለውን ታክስ ለማስከፈል በሚወስደው እርምጃ ምክንያት ለሚያወጣው ማንኛውም ወጪ ኃላፊ ይሆናል፡፡

31. በሁለተኛ ደረጃ የሚመጡ ኃላፊነቶች እና ታክስን ለማስከፈል የሚደረጉ ወጪዎች

1. ቢሮው የሁለተኛ ደረጃ ኃላፊነት ላለበት ወይም ታክስን ለማስከፈል የተደረገን ወጪ መክፈል ላለበት ማንኛውም ሰው መክፈል ያለበትን የገንዘብ መጠን እና ክፍያው የሚፈጸምበትን ቀን የሚገልጽ ማስታወቂያ ይሰጣል፡፡

2. የዚህን አዋጅ ክፍል ሰባት፣ ስምንት፣ ዘጠኝ እና አሥር እንዲሁም አንቀጽ 105ን በሚመለከት፡-

ሀ) "ታክስ" የሚለው ቃል በሁለተኛ ደረጃ የሚመጣ ኃላፊነትንና ታክስን ለማስከፈል የሚደረግ ወጪን ይጨምራል፤

ለ) "ያልተከፈለ ታክስ" የሚለው ሀረግ በዚህ

to the Bureau.

2. A taxpayer required to pay tax electronically by the Bureau under Article 82 (2) of this Proclamation shall do so unless authorised by the Bureau, by notice in writing, to use another method of payment.

3. If a taxpayer fails to pay tax by the due date, the taxpayer shall be liable for any costs incurred by the Bureau in taking action to recover the unpaid tax.

**31. Secondary Liabilities and Tax Recovery Costs**

1. The Bureau may serve a person liable for a secondary liability or tax recovery costs with notice of the amount of the liability payable by the person and the due date for payment.

2. A reference in Parts Seven, Eight, Nine, and Ten, and Article 105 of this Proclamation:

a) to "tax", shall include a secondary liability and tax recovery costs;

b) to "unpaid tax", shall include an

ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተጠቀሰውና በመክፈያ ጊዜው ያልተከፈለን ታክስ ይጨምራል፤ እንዲሁም

ሐ) "ታክስ ከፋይ" የሚለው ሀረግ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተውን ታክስ የመክፈል ኃላፊነት ያለበትን ሰው ይጨምራል፡፡

3. የሁለተኛ ደረጃ ኃላፊነት ባለበት ሰው የተከፈለ ታክስ ይኸው ኃላፊነት ከሚመለከተው የታክስ ከፋዩ የመጀመሪያ የታክስ ኃላፊነት ጋር ይካካሳል፡፡

## 32. የታክስ መክፈያ ጊዜን ስለማራዘም

1. ታክስ ከፋዩ በታክስ ሕግ መሠረት የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ታክስ የመክፈያ ጊዜው እንዲራዘምለት ለቢሮው የጽሑፍ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ ቢሮው በቂ ምክንያት መኖሩን ካረጋገጠ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት፡
   ሀ) ለታክስ ከፋዩ የታክስ መክፈያ ጊዜውን ሊያራዝምለት፣ ወይም
   ለ) ቢሮው በሚወሰነው መሠረት ታክሱን በመከፋፈል በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል ሊያደርገው ይችላል፡፡
3. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለቀረበው ማመልከቻ የሰጠውን ውሳኔ የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ይሰጠዋል፡፡

amount specified in paragraph (a) of this sub-article that is not paid by the due date; and

c) to "taxpayer", shall include a person liable for an amount specified in paragraph (a) of this sub-article.

3. An amount of a secondary liability paid by a person shall be credited against the primary liability of the taxpayer to which the secondary liability relates.

## 32. Extension of Time to Pay Tax

1. A taxpayer may apply, in writing, to the Bureau for an extension of time to pay tax due under a tax law.
2. When an application has been made under sub-article (1) of this Article, the Bureau may, upon satisfaction that there is good cause and in accordance with a Directive issued by the Bureau:
   a) grant the taxpayer an extension of time for payment of the tax; or
   b) require the taxpayer to pay the tax in such instalments as the Bureau may determine.
3. The Bureau shall serve the taxpayer with written notice of the decision on an application under sub-article (1) of this Article.

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ) መሠረት ታክሱን በመከፋፈል በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ የአንድን ጊዜ ክፍያ ካልከፈለ ታክስ ከፋዩ ክፍያውን ባቆመበት ጊዜ ያለውን ቀሪ ክፍያ በሙሉ እንዲከፍል ቢሮው ወዲያውኑ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

5. የታክስ መክፈያ ጊዜው እንዲራዘም ወይም ታክሱን በመከፋፈል በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ በዘገየው ክፍያ ላይ ከመጀመሪያ የታክስ መክፈያ ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ወለድ የመክፈል ግዴታውን አያስቀርም፡፡

**33.በታክስ እና ለሦስተኛ ወገን በሚሰጥ የክፍያ ትዕዛዝ በሚከፈል ገንዘብ ላይ ስለሚኖር የቅድሚያ መብት**

1. ይህ አንቀጽ ለሚከተሉት ክፍያዎች ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡-

ሀ) ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ በሚከፈል ታክስ፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ፣ በተርንኦቨር ታክስ፣ ወይም በኤክሳይዝ ታክስ፣ እና

ለ) ለሦስተኛ ወገን በሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ መሠረት ሊከፈል በሚገባው ገንዘብ፤

2. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ በሚሆንበት ገንዘብ ባለዕዳ የሆነ፣ የያዘ፣ የተረከበ ወይም ቀንሶ የሚያስቀር ሰው ይህንን ገንዘብ የመንግሥት ባለአደራ በመሆን የሚይዝ ስለሆነ ይህ ሰው ሲከስር ወይም ንብረቱ ሲጣራ የመንግሥት ባለአደራ በመሆን የያዘው ገንዘብ፡-

4. When a taxpayer permitted to pay tax by instalments under sub-article (2) (b) of this Article defaults in the payment of an instalment, the Bureau may immediately take action to recover the whole balance of the tax outstanding at the time of default.

5. The grant of an extension of time to pay tax or permission to pay tax due by instalments shall not prevent the liability for late payment interest arising from the original date the tax was due for payment.

**33. Priority of Tax and Garnishee Amounts**

1. This Article applies to the following amounts:

a) withholding tax, value added tax, turn over tax or excise tax; and

b) an amount payable under a garnishee order.

2. A person owing, holding, receiving, or withholding an amount to which this Article applies holds the amount on behalf of the Government and, in the event of the liquidation or bankruptcy of the person, the amount:

ሀ) በንብረት ማጣራቱ ሂደት ወይም በኪሳራው የጠቅላላ ንብረቱ አካል ተደርጎ አይወሰድም፣ እንዲሁም

ለ) ምንም ዓይነት የንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት ለቢሮው መከፈል አለበት፡፡

3. በሌላ ማንኛውም ሕግ በተለየ አኳሃን የተደነገገ ቢሮርም ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ታክስ፡-

ሀ) ከማንኛውም ሰው ለሚፈለግ ማንኛውም ዕዳ ወይም ኃላፊነት ማስፈጸሚያ ሊከበር አይችልም፡፡

ለ) ታክሱ ተይዞ ቀሪ ከሚደረግበት ክፍያ ላይ ከሚፈለጉ ዕዳዎች ሁሉ የመጀመሪያው ይሆናል፡፡ እንዲሁም

ሐ) በማናቸውም ሕግ ወይም የፍርድ ቤት ትእዛዝ መሠረት ከክፍያው ላይ ከሚቀነስ ማንኛውም የገንዘብ ክፍያ ቅድሚያ ይኖረዋል፡፡

## 34. የአከፋፈል ቅደም ተከተል

1. አንድ ታክስ ከፋይ ቅጣትና ክፍያ ለዘገየበት ወለድ የመክፈል ኃላፊነት ሲኖርበትና ታክስ ከፋዩ የፈፀመው ክፍያ መክፈል ከሚገባው ጠቅላላ የታክስ፣ የቅጣትና የወለድ መጠን ያነሰ በሚሆንበት ጊዜ የተከፈለው ገንዘብ የሚሸፍነው ዕዳ ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) በመጀመሪያ ዋናውን የታክስ ዕዳ ለመክፈል፤

ለ) ቀጥሎ ክፍያ ለዘገየበት የሚከፈል ወለድ፣

ሐ) ቀሪው ገንዘብ ለቅጣት መክፈያ ይውላል፡፡

a) shall not form part of the person's estate in liquidation or bankruptcy; and

b) shall be paid to the Bureau before any distribution of property is made.

3. Despite any other law, withholding tax withheld by a person:

a) shall not be subject to attachment in respect of any debt or liability of the person;

b) shall be a first charge on the payment or amount from which the tax is withheld; and

c) shall be withheld prior to any other deduction that the person may be required to make from the payment or amount under an order of any court or any law.

## 34. Order of Payment

1. When a taxpayer is liable for penalty and late payment interest in relation to a tax liability and the taxpayer makes a payment that is less than the total amount of tax, penalty, and interest due, the amount paid shall be applied in the following order:

a) first in payment of the tax liability;

b) then in payment of late payment interest;

c) then the balance remaining is applied in payment of penalty.

2. ማንኛውም ታክስ ከፋይ ክፍያ በሚፈጽምበት ጊዜ ከአንድ በላይ የታክስ ዕዳ የሚፈለግበት ከሆነ ክፍያው የሚሸፍነው ዕዳ ቅደም ተከተል ዕዳው በተፈጠረበት ጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት ይሆናል፡፡

35. ለታክስ አከፋፈል የሚቀርብ ዋስትና

1. ቢሮው የመንግሥትን ገቢ ለመጠበቅ አስፈላጊ መስሎ ሲታየው አስፈላጊ ነው በሚለው መጠንና አኳኋን ታክሱ ከፋዩ ዋስትና እንዲያቀርብ ሊያስገድደው ይችላል፡፡ ታክስ ከፋዩ ዋስትና እንዲያቀርብ የሚጠየቀውም፡-
   ሀ) የመክፈያ ጊዜው ለደረሰ ወይም የመክፈያ ጊዜው ለሚደርስ ታክስ መክፈያ፤ ወይም
   ለ) በታክስ ሕግ መሠረት ተመላሽ ለሚጠይቅ ታክስ ከፋይ ቅድመ-ሁኔታ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጥ ዋስትና ቢሮው የሚጠይቃቸው ተገቢ ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ ዋስትና ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. ታክስ ከፋዩ ዋስትና የማቅረብ ግዴታ የሚኖርበት ቢሮው፡-
   ሀ) የሚፈለገው የዋስትና መጠን፤
   ለ) ዋስትናው የሚቀርብበትን አኳኋን፤ እና
   ሐ) ዋስትናው የሚቀርብበትን ቀን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ የሰጠ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
4. ለዚህ ክፍል ዓላማ ሲባል ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት ያላቀረበው የዋስትና መጠን የታክስ ከፋዩ ያልተከፈለ ታክስ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

2. When a taxpayer has more than one tax liability at the time a payment is made, the payment is applied against the tax liabilities in the order in which the liabilities arose.

35. **Security for Payment of Tax**

1. When it appears to the Bureau necessary to do so for the protection of the revenue, the Bureau may require any taxpayer to give security in such amount and manner as the Bureau considers appropriate:
   a) for the payment of tax that is or may become due by the taxpayer; or
   b) as a condition of the taxpayer claiming a refund of tax under a tax law.
2. Security under this Article may be given by cash or bank guarantee and shall be subject to such conditions as the Bureau may reasonably require.
3. A taxpayer shall be liable to give security only if the Bureau:
   a) the amount of the security required;
   b) the manner in which the security is to be provided; and
   c) the due date for providing the security serves the taxpayer with a notice setting out.
4. An amount of security that a taxpayer fails to provide as required under this Article shall be treated as unpaid tax of the taxpayer for the purposes of this Part.

36. ስለጥበቃ

1. ይህ አንቀጽ በሚከተሉት ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡-
   ሀ) በገቢ ግብር ሕግ መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ታክስ ቀንሶ ለቢሮው የከፈለ ሰው፤
   ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 (1) መሠረት ለቢሮው ታክስ የከፈለ የታክስ እንደራሴ፣
   ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40 መሠረት ለቢሮው ታክስ የከፈለ ተረካቢ፣ወይም
   መ) ለሦስተኛ ወገን በሚሰጥ የክፍያ ትዕዛዝ መሠረት ለቢሮው ገንዘብ የከፈለ ሰው፡፡
2. ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆንበት ሰው ታክስ ከፋዩን በመወከል በታክስ ሕግ መሰረት ለቢሮው የከፈለው ገንዘብ በታክስ ከፋዩ እንዲተካለት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

ምዕራፍ ሁለት

ለዘገየ ክፍያ የሚከፈል ወለድ

37. ለዘገየ ክፍያ የሚከፈል ወለድ

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በታክስ መክፈያ ጊዜው ወይም ከዚያ በፊት ታክሱን ያልከፈለ ታክስ ከፋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው ምጣኔ መሠረት ታክሱ መከፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ እስካላቀበት ቀን ድረስ ባልተከፈለው መጠን ላይ ለዘገየው ክፍያ ወለድ የመክፈልግዴታ አለበት፡፡
2. የዘገየ ክፍያ የወለድ ምጣኔ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ጊዜ

**36. Protection**

1. This Article shall apply to the following persons:

a) a withholding agent who has withheld tax from a payment under the Income Tax Proclamation and paid the tax to the Bureau;

b) a tax representative who has paid an amount to the Bureau pursuant to Article 16 (1) of this Proclamation;

c) a receiver who has paid an amount to the Bureau pursuant to Article 40 of this Proclamation;

d) a person who has paid an amount to the Bureau pursuant to a garnishee order.

2. A person to whom this Article applies shall have the Right to enquire for recovery of the amount paid on behalf a taxpayer to the Bureau in accordance with the Tax Law.

**CHAPTER TWO**

**LATE PAYMENT INTEREST**

**37. Late Payment Interest**

1. Subject to sub-article (8) of this Article, a taxpayer who fails to pay tax on or before the due date for payment shall be liable for late payment interest at the rate specified in sub-article (2) of this Article on the unpaid tax for the period commencing on the date the tax was due and ending on the date the tax was paid.
2. The rate of late payment interest shall be the highest commercial lending interest rate

ከመጀመሩ በፊት ባለው ሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ ምጣኔ ላይ 15% (አሥራ አምስት በመቶ) ተጨምሮበት ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የዘገየ ክፍያ ወለድ የተከፈለበት ታክስ መከፈል የማይኖርበት ታክስ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ለታክሱ ከፋዩ ይመለስለታል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ መሠረት በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 100 መሠረት ታክስን በመክፈያ ጊዜው ባለመክፈል ከሚጣለው ቅጣት በተጨማሪ ይሆናል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ መሠረት በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ በነጠላ ወለድ የሚሰላ ሲሆን የሚታሰበውም በየቀኑ ይሆናል፡፡

6. ቢሮው በዘገየ ክፍያ ላይ ወለድ የመክፈል ግዴታ ላለበት ታክስ ከፋይ መክፈል ያለበትን የወለድ መጠንና የመክፈያ ጊዜውን የሚገልጽ ማስታወቂያ ይሰጠዋል፡፡

7. ታክስ ከፋዩ መክፈል ያለበትን በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ የሚገልፀው ማስታወቂያ ቢሮው የሚሰጠውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ጨምሮ በማንኛውም ማስታወቂያ ውስጥ ሊካተት ይችላል፡፡

8. በሚከተሉት ሁኔታዎች ማስታወቂያው በተሰጠበት እና ክፍያው በተፈፀመበት መካከል ላለው ጊዜ የዘገየ ክፍያ ወለድ አይታሰብም፡፡

that prevailed in Ethiopia during the quarter immediately before the commencement of the period specified in sub-article (1) of this Article increased by 15%.

3. Late payment interest paid by a taxpayer under sub-article (1) of this Article shall be refunded to the taxpayer to the extent that the tax to which the interest relates is found not to have been payable.

4. Late payment interest payable under this Article shall be in addition to any late payment penalty imposed under Article 100 of this Proclamation in respect of a failure to pay tax by the due date.

5. Late payment interest payable under this Article shall be calculated as simple interest and shall be computed on a daily basis.

6. The Bureau may serve a taxpayer liable for late payment interest with a notice of the amount of interest payable by the taxpayer and the due date for payment.

7. A notice of the amount of late payment interest payable by a taxpayer may be included in any other notice, including a notice of a tax assessment, issued by the Bureau to the taxpayer.

8. Late payment interest shall not accrue for the period between the date of notification and the date of payment on the following conditions:

ሀ) ቢሮው በታክስ ሕግ መሠረት ከታክስ ከፋዩ የሚፈለገውን የታክስ ዕዳ የታክስ ስሌት ማስታወቂያን ጨምሮ በማንኛውም የጽሑፍ ማስታወቂያ ያሳወቀው እንደሆነ፤ እና

ለ) ታክስ ከፋዩ ማስታወቂያው እስከተሰጠበት ቀን ድረስ መክፈል የሚጠበቅበትን የዘገየ ክፍያ ወለድ ጨምሮ በማስታወቂያው የተመለከተውን የታክስ ዕዳ በሙሉ በማስታወቂያው በተገለጸው የመክፈያ ቀን የከፈለ ከሆነ፤

9. ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ በሚከፈል ታክስ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ኃላፊነት በሚከፈል ታክስ ላይ የሚታሰብ የዘገየ ክፍያ ወለድ መከፈል ያለበት ይኸው ኃላፊነት ባለበት ሰው ብቻ በመሆኑ ከሌላ ማንኛውም ሰው ሊጠየቅ አይችልም፡፡

10. በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ ጠቅላላ መጠን ከታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳ ሊበልጥ አይችልም፡፡

11. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ “ታክስ” በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድን አይጨምርም፡፡

## ምዕራፍ ሦስት
## ያልተከፈለን ታክስ ስለማስከፈል

### 38. የታክስ ስሌቶችን ስለማስፈጸም

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ታክስ ከፋዩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 55 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ቅሬታ ካለቀረበ ቢሮው ለታክስ ከፋዩ
2. ቢሮው ለታክስ ከፋይ የታክስ ስሌት ወይም ውሳኔ ማስታወቂያ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚሰጥበት ጊዜ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) የተመለከተው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ውሳኔ ቅጂ ማስታወቂያውን ወይም ውሳኔውን በመለየት እና በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የተላለፈውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ውሳኔ ዝርዝር

Court, or in any other proceedings on any ground whatsoever;

b) the production of a notice of a tax assessment or a determination, or a document certified by the Bureau as a copy of a notice of a tax assessment or a determination shall be conclusive evidence of the due making of the assessment or a determination and that the amount and particulars of the assessment or a determination are correct; and

c) in the case of a self-assessment, the production of the original self-assessment declaration or a document certified by the Bureau as a copy of such declaration shall be conclusive evidence of the contents of the declaration.

2. When the Bureau serves a notice of a tax assessment or a determination on a taxpayer electronically, the reference in sub-article (1) (b) of this Article to a copy of the notice of assessment or determination includes a document certified by the Bureau identifying the assessment or determination and specifying the details of the electronic transmission of the assessment or

ጉዳዮች በመግለጽ በቢሮው የተረጋገጠን ሰነድ ይጨምራል፡፡

3. ታክስ ከፋይ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚያቀርብበት ጊዜ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) የተመለከተው የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ቅጂ ማስታወቂያውን በመለየት እና በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የተላለፈውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ዝርዝር ጉዳዮች በመግለጽ በቢሮው የተረጋገጠን ሰነድ ይጨምራል፡፡

4. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "ውሳኔ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 34 ለታክስ ውሳኔ በተሰጠው ትርጉም ሥር በፊደል ተራ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ (ረ)፣ (ሰ) ወይም (ሸ) የተመለከተውን ነው፡፡

## 54. በታክስ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ የቅሬታ ማስታወቂያ

1. በታክስ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ የውሳኔው ማስታወቂያ በደረሰው በ21 (ሃያ አንድ) ቀናት ውስጥ በውሳኔው ላይ የቅሬታ ማስታወቂያ ለቢሮው በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ቅሬታ የቀረበበት የታክስ ውሳኔ በተሻሻለ የታክስ ስሌት ላይ ከሆነ የታክስ ከፋዩ የተሻሻለውን የታክስ ስሌት የመቃወም መብት የመጀመሪያውን የታክስ ስሌት በመለወጥ፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር በተደረገው ማሻሻያ ላይ ብቻ የተገደበ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት

determination.

3. When a taxpayer has filed a self-assessment declaration electronically, the reference in sub-article (1) (c) of this Article to a copy of the declaration includes a document certified by the Bureau identifying the declaration and specifying the details of the electronic transmission of the declaration.

4. In this Article, "determination" means a decision referred to in paragraphs (b), (c), (d), (f), (g) or (h) of the definition of "tax decision" in sub-article (34) of Article 2 of this Proclamation.

## 54. Notice of Objection to a Tax Decision

1. A taxpayer dissatisfied with a tax decision may file a notice of objection to the decision, in writing, with the Bureau within 21 days after service of the notice of the decision.
2. When the tax decision objected to is an amended assessment, a taxpayer's right to object to the amended assessment shall be limited to the alterations, reductions, and additions made in it to the original assessment.
3. A notice of objection shall be treated as validly filed by a taxpayer under sub-

በታክስ ከፋይ የቀረበ የቅሬታ ማስታወቂያ በአግባቡ እንደቀረበ የሚቆጠረው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው፡-

ሀ) የቅሬታ ማስታወቂያው ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔውን የሚቃወምበትን ምክንያቶች፣ ታክስ ከፋዩ ውሳኔውን ለማስተካከል ሊደረጉ ይገባል ብሎ የሚያምንባቸውን ማሻሻያዎች እና እነዚህን ማሻሻያዎች ማድረግ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያቶች በትክክል የሚገልጽ ከሆነ፣

ለ) ቅሬታው ከታክስ ስሌት ጋር የተገናኘ ከሆነ ታክስ ከፋዩ በታክስ ስሌቱ መሠረት መከፈል ያለበትን እና በቅሬታ ማስታወቂያው ተቃውሞ ያላቀረበበትን ታክስ የከፈለ እንደሆነ ነው፡፡ እንዲሁም

ሐ) በታክስ ውሳኔው ላይ ቅሬታ ቢኖረውም ታክሱን ከፍሎ የቅሬታ ማስታወቂያ ማቅረብን የመረጠ ከሆነ የተወሰነበትን ታክስ ከከፈለ ነው፡፡

4. ቢሮው የቅሬታ ማስታወቂያው በአግባቡ አልቀረበም ብሎ ሲያምን ለታክስ ከፋዩ የሚከተሉትን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ወዲያውኑ ይሰጠዋል፡፡

   ሀ) ቅሬታው በአግባቡ አልቀረበም የሚልባቸውን ምክንያቶች፤ እና

   ለ) ከሚከተሉት በዘገየው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ቅሬታውን ካላቀረበ የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ እንደሚያልፍ፣

5. ቅሬታው የሚመለከተው የታክስ ውሳኔ

article (1) of this Article only when the following conditions are satisfied:

a) the notice of objection states precisely the grounds of the taxpayer's objection to the tax decision, the amendments that the taxpayer believes are required to be made to correct the decision, and the reasons for making those amendments;

b) when the objection relates to a tax assessment, the taxpayer has paid any tax due under the tax assessment that is not disputed by the taxpayer in the objection; and

c) if a tax payer prefers to pay the tax assessed on protest, after the tax in dispute is fully paid.

4. When the Bureau considers that a notice of objection filed by a taxpayer has not been validly filed, the Bureau shall immediately serve written notice on the taxpayer stating the following:

   a) the reasons why the objection has not been validly filed; and

   b) that the objection will lapse unless a valid objection is filed by the later of:

5. 21 days from the date of service of

ማስታወቂያ በደረሰው በ21 (ሃያ አንድ) ቀናት ውስጥ፣ ወይም

6. በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት የሚሰጠው ማስታወቂያ በደረሰው በ፲ ቀናት ውስጥ፤

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈ ከሆነ ቢሮው ይህንን የሚገልጽ የጽሁፍ ማስታወቂያ ለሚመለከተው ታክስ ከፋይ ይሰጣል፡፡

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ ከማለፉ በፊት ታክስ ከፋዩ በታክስ ውሳኔ ላይ የቅሬታ ማስታወቂያ የሚያቀርብበት ጊዜ እንዲራዘምለት ለቢሮው የጽሑፍ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡

9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብ፣ ቢሮው፡-

ሀ) ታክስ ከፋዩ በኢትዮጵያ ውስጥ ያልነበረ በመሆኑ፣ በህመም ምክንያት ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (4) በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የቅሬታ ማስታወቂያውን ማቅረብ አለመቻሉ፣ እና

ለ) የቅሬታ ማስታወቂያውን ለማቅረብ በታክስ ከፋዩ በኩል ምክንያታዊ ያልሆነ መዘግየት አለመኖሩን፣ ሲያምንበት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜው ካበቃበት ቀን ጀምሮ ከ10 (ከአሥር) ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡

the notice of the tax decision to which the objection relates; or

6. 10 days from the date of service of the notice under this sub-article.

7. The Bureau shall serve written notice on the taxpayer when an objection shall be treated as lapsed under sub-article (4) of this Article.

8. A taxpayer may apply, in writing and before the end of the objection period in sub-article (1) of this Article, to the Bureau for an extension of time to file a notice of objection.

9. When an application has been made under sub-article (6) of this Article, the Bureau:

a) owing to absence from Ethiopia, sickness, or other reasonable cause, the taxpayer was prevented from lodging the notice of objection within the period specified in sub-article (1) or (4) of this Article; and

b) may allow an extension of time for a maximum of 10 days from the end of the objection period in sub-article (1) of this Article when satisfied.

## 55. በቅሬታ ላይ ውሳኔ ስለመስጠት

1. ቢሮው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 54 መሠረት በአግባቡ የቀረቡ ቅሬታዎች በነጻነት በመመርመር በቅሬታዎቹ ላይ ለሚሰጠው ውሳኔ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ ቋሚ የሥራ ክፍል ያቋቁማል፡፡
2. ቢሮው፣ ቅሬታዎች የሚታዩበትን ሥነ-ሥርዓት እና ለቢሮው የሚቀርቡ የውሳኔ ሃሣቦች የሚመሠረቱባቸውን ጉዳዮች እና የውሳኔ አሰጣጡን ሥርዓት የያዘ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡
3. የሥራ ክፍሉ በታክስ ስሌት ላይ የቀረበውን ቅሬታ ሲመረምር በታክስ ስሌቱ የተመለከተው የታክስ መጠን ሊጨምር ይገባል የሚል እምነት ሲኖረው፣ የሥራ ክፍሉ የታክስ ስሌቱ ለሚመለከተው የታክስ ሠራተኛ ተመልሶ እንደገና እንዲታይ የውሳኔ ሃሳብ ለቢሮው ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
4. ቢሮው በሥራ ክፍሉ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ከመረመረ በኂላ፣ የቀረበውን ቅሬታ በሙሉ ወይም በከፊል በመቀበል ወይም ውድቅ በማድረግ ውሳኔ የሚሰጥ ሲሆን ውሳኔውም በቅሬታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ" ተብሎ ይጠቀሳል፡፡
5. ቢሮው በቅሬታ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ የሚያሳውቀው ሲሆን፣ በታክስ ስሌት ላይ የቀረበ ቅሬታ ከሆነ የታክስ ስሌቱን ማሻሻልን ጨምሮ ውሳኔውን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

## 55. Making Objection Decisions

1. The Bureau shall establish a review department as a permanent office within the Bureau to provide an independent review of objections validly filed under Article 54 of this Proclamation.
2. The Bureau shall issue detail Directive specifying the procedures for reviewing an objection including hearings, and the basis for making recommendations to the Bureau and the decision-making procedure.
3. If, in considering an objection to a tax assessment, the review department is of the view that the amount of tax assessed should be increased, the review department shall recommend to the Bureau that the tax assessment be referred to the tax officer for reconsideration.
4. After having regard to the recommendations of the review department, the Bureau shall make a decision to allow the objection in whole or part, or disallow it, and the Bureau's decision shall be referred to as an "objection decision."
5. The Bureau shall serve notice, in writing, of an objection decision on the taxpayer and take all steps necessary to give effect to the decision, including, in the case of an objection to a tax assessment, the making of an amended assessment.

6. በቅሬታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ ማስታወቂያ የጉዳዩን ዋና ፍሬነገሮች ግኝቶች እና ለውሳኔው መሠረት የሆኑትን ምክንያቶች መግለጫ ማካተት አለበት፡፡

7. ቢሮው ታክስ ከፋዩ ቅሬታ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 180 (አንድ መቶ ሰማንያ) ቀናት ውስጥ በቅሬታው ላይ ውሳኔ ካልሰጠ ታክስ ከፋዩ ይግባኙን 180 (አንድ መቶ ሰማንያ) ቀን በተጠናቀቀ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ማቅረብ ይችላል፡፡

**56. ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ይግባኝ ስለማቅረብ**

1. ይግባኝ ሊቀርብበት በሚችል ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 87 መሠረት የይግባኝ ማስታወቂያውን ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. በታክስ ስሌት ላይ ከቀረበ ቅሬታ ጋር በተገናኘ በታክስ ከፋይ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የሚቀርብ የይግባኝ ማስታወቂያ በአግባቡ ቀርቧል ሊባል የሚችለው በክርክር ላይ ያለ ታክስ 50% (ሃምሳ በመቶ)፣ የተከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) "በክርክር ላይ ያለ ታክስ" ከታክሱ ጋር በተገናኘ ሊከፈል የሚገባውን ቅጣትና የዘገየ ክፍያ ወለድን አይጨምርም፡፡
4. የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የይግባኝ ማስታወቂያ የሚቀርብበት ጊዜ እንዲራዘም ስለሚቀርብ

6. A notice of an objection decision shall contain a statement of findings on the material facts, the reasons for the decision.

7. When the Bureau has not made an objection decision within 180 days from the date that the taxpayer filed notice of the objection, the tax payer may appeal to the Tax Appeal Commission within 30 days after the end of the 180 days period.

**56. Appeal to Tax Appeal Commission**

1. A taxpayer dissatisfied with an appealable decision may file a notice of appeal with the Tax Appeal Commission in accordance with Article 87 of this Proclamation.
2. A notice of appeal to the Tax Appeal Commission in relation to an objection to a tax assessment shall be treated as validly filed by a taxpayer only if the taxpayer has paid to the Bureau 50% of the tax in dispute under the tax assessment.
3. The reference to "tax in dispute" in sub-article (2) of this Article shall not include penalty and late payment interest payable in respect of the disputed tax.
4. The Tax Appeal Commission may issue a Directive providing for applications for an extension of time to file a notice of appeal under sub-article (1) of this Article.

ማመልከቻ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**57. ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ስለማቅረብ**

1. ለኮሚሽኑ በቀረበ የታክስ ይግባኝ ተካፋይ የነበረ ሰው ኮሚሽኑ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ የኮሚሽኑ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 (በሰላሳ) ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማስታወቂያውን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. በኮሚሽኑ በታየ የታክስ ይግባኝ ላይ ተከራካሪ የነበረ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘምለት በጽሑፍ ማመልከቻ ሲጠይቅ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ጊዜውን ሊያራዝመው ይችላል፡፡
3. በታክስ ስሌት ላይ ከቀረበ ቅሬታ ጋር በተገናኘ በታክስ ከፋይ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ የይግባኝ ማስታወቂያ በአግባቡ ቀርቧል ሊባል የሚችለው በክርክር ላይ ያለ ታክስ 75% (ሰባ አምስት በመቶ) የተከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
4. ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚቀርበው በሕግ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሲሆን የይግባኝ ማስታወቂያውም በቀረበው ይግባኝ የሚነሱትን የሕግ ጉዳዮች መግለጽ አለበት፡፡
5. የከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን በመስማት፡-

   ሀ) የኮሚሽኑን ውሳኔ ሊያፀናው፤

   ለ) የኮሚሽኑን ውሳኔ በመሻር፤

1. የኮሚሽኑን ውሳኔ የሚተካ ውሳኔ ሊሰጥ፤ ወይም

**57. Appeal to the High Court**

1. A party to a proceeding before the Commission who is dissatisfied with the decision of the Commission may, within 30 days after being served with notice of the decision, file a notice of appeal to the High Court.
2. The High Court may, on an application in writing by a party to a proceeding before the Tax Appeal Commission, extend the time for lodging a notice of appeal under sub-article (1) of this Article.
3. A notice of appeal to the High Court by a taxpayer in relation to an objection to a tax assessment shall be treated as validly filed only if the taxpayer has paid 75% of the tax in dispute under the assessment.
4. An appeal to the High Court shall be made on a question of law only, and the notice of appeal shall state the question of law that will be raised on the appeal.
5. The High Court shall hear the appeal and may:

   a) decide to affirm the decision of the Commission;

   b) decide to set aside the decision of the Commission:

1. make a decision in substitution of the

2. ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለኮሚሽኑ ወይም ለቢሮው መልሶ ሊልከው፤

ሐ) ይግባኙን ውድቅ ሊያደርገው፤ ወይም

መ) ተገቢ መስሎ የታየውን ሌላ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) "በክርክር ላይ ያለ ታክስ" ማለት የታክስ ይግባኝ ኮሚሽኑ እንዲከፈል ውሳኔ የሰጠበት እና ታክስ ከፋዩ በይግባኝ ማስታወቂያ ቅሬታ ያቀረበበት ታክስ ሲሆን ከታክሱ ጋር በተገናኘ ሊከፈል የሚገባውን ቅጣትና የዘገየ ክፍያ ወለድን አይጨምርም፡፡

**58. ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለሚቀርብ ይግባኝ**

1. ለከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀረበ የታክስ ይግባኝ ተካፋይ የነበረ ሰው ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ የፍርድ ቤቱ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 (በሰላሳ) ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማስታወቂያውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. በከፍተኛ ፍርድ ቤት በታየ የታክስ ይግባኝ ላይ ተከራካሪ የነበረ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘምለት በጽሑፍ ማመልከቻ ሲጠይቅ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጊዜውን ሊያራዝመው ይችላል፡፡

decision of the Commission; or

2. remit the decision to the Commission or Bureau for reconsideration in accordance with the directions of the Court;

c) decide to dismiss the appeal; or

d) make any other decision the court thinks appropriate.

6. The reference to "tax in dispute" in sub-article (3) of this Article means the tax determined by the Tax Appeal Commission to be payable that is disputed by the taxpayer in the notice of appeal, but does not include penalty and late payment interest payable in respect of the disputed tax.

**58. Appeal to the Supreme Court**

1. A party to a proceeding before the High Court who is dissatisfied with the decision of the High Court may, within 30 days after being served with notice of the decision, file a notice of appeal to the Supreme Court.
2. The Supreme Court may, on an application in writing by a party to a proceeding before the High Court, extend the time for lodging a notice of appeal under sub-article (1) of this Article.

**59. የማስረዳት ኃላፊነት**

በዚህ ክፍል መሠረት ከታክስ ውሳኔ ጋር በተገናኘ በሚደረግ ማንኛውም የታክስ ክርክር ሂደት የታክስ ውሳኔ ትክክል አለመሆኑን የማስረዳት ኃላፊነት የታክስ ከፋዩ ነው፡፡

**60. የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም የፍርድ ቤትን ውሳኔ ስለመፈጸም**

1. ቢሮው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በደረሰው በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ መስጠትን ጨምሮ፣ ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 የተመለከተው የታክስ ስሌት ማሻሻያ የጊዜ ገደብ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔን ተግባራዊ ለማድረግ በሚከናወን የታክስ ስሌት ማሻሻያ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## ክፍል አሥር
## መረጃን ስለመሰብሰብና ስለማስፈፀም

**61. የታክስ ክሊራንስ**

1. ማንኛውም ታክስ ከፋይ በፀደቀው ቅጽ መሠረት የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለቢሮው ማመልከት ይችላል፡፡
2. ቢሮው ታክስ ከፋዩ በታክስ ሕግ መሠረት የተጣለበትን ታክስ የመክፈል ግዴታ የፈፀመ መሆኑን ሲያረጋግጥ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ታክሰ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ

**59. Burden of Proof**

In any proceeding under this Part in relation to a tax decision, the burden shall be on the taxpayer to prove that the tax decision is incorrect.

**60. Implementation of Decision of Commission or Court**

1. The Bureau shall, within 30 days after being served with notice of the decision of the Tax Appeal Commission, High Court, or Supreme Court, take such action, including serving the taxpayer with notice of an amended assessment, as is necessary to give effect to the decision.
2. The time limit in Article 28 of this Proclamation for amending a tax assessment shall not apply to an amendment to give effect to a decision of the Tax Appeal Commission or a Court.

## PART TEN
## INFORMATION COLLECTION AND ENFORCEMENT

**61. Tax Clearance**

1. A taxpayer may apply to the Bureau, in the approved form, for a tax clearance certificate.
2. The Bureau shall issue a tax clearance certificate to a taxpayer within 14 days of the taxpayer filing an application under sub-article (1) of this Article if satisfied that the taxpayer has fulfilled its obligations to pay

አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻውን ባቀረበ በ14 ቀናት ውስጥ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ማመልከቻ የሚያቀርበው ታክስ ከፋይ ለቀደመው ዓመት ወይም ለቀደሙት ዓመታት በታክስ ከፋይነት ያልተመዘገበ እንደሆነ ቢሮው ታክስ ከፋዩ የተመዘገበ መሆኑን በመግለጽ ታክስ ከፋዩ ማመልከቻ ባቀረበ በ14 (አስራ አራት) ቀናት ውስጥ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት መስጠት ይኖርበታል፡፡

4. ማንኛውም የፋይናንስ መስሪያ ቤት፣ ማዘጋጃ ቤት፣ የመንግሥት የሥራ ክፍል፣ ወይም የፌደራል ወይም የክልል መንግሥት ቢሮ ወይም ሌላ ማንኛውም የመንግሥት አካል ታክስ ከፋይ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ካላቀረበ በስተቀር ማንኛውንም ፈቃድ መስጠት ወይም ማደስ ወይም በመንግሥት ጨረታ እንዲሳተፍ መፍቀድ አይችልም፡፡

5. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ ላቀረበ ታክስ ከፋይ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ላለመስጠት የወሰነ እንደሆነ ታክስ ከፋዩ ማመልከቻውን ባቀረበ በ14 (አሥራ አራት) ቀናት ውስጥ ማመልከቻን ያልተቀበለበትን ምክንያት የሚገልጽ የውሳኔ ማስታወቂያ ይሰጠዋል፡፡

tax under the tax laws as determined under a Directive issued by the Bureau.

3. If a taxpayer applying under sub-article (1) of this Article was not registered for tax for the preceding year or years, the Bureau shall issue a tax clearance certificate to the taxpayer within 14 days of the taxpayer lodging the application stating that the taxpayer is registered with the Bureau.

4. No Ministry, Municipality, Department or Office of the Federal or a State Government, or other Government body shall issue or renew any licence to a taxpayer, or allow the taxpayer to participate in a public tender, unless the taxpayer produces a tax clearance certificate.

5. If the Bureau refuses to issue a taxpayer with a tax clearance certificate, the Bureau shall provide the taxpayer with notice of the decision within 14 days of the taxpayer lodging an application under sub-article (1) of this Article.

62. የመመስረቻ ጽሑፍን እና የመተዳደሪያ ደንብን ስለማቅረብ

1. ማንኛውም ድርጅት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ የመመስረቻ ጽሑፍ፣ የመተዳደሪያ ደንብ፣ የሽርክና ማህበር ስምምነት ወይም ሌላ የመመስረቻ ወይም የምዝገባ ሰነድ ቅጂ ለቢሮው ማቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሱት ሰነዶች ላይ ማንኛውም ለውጥ ሲደረግ ድርጅቱ ለውጡ በተደረገ በ30 (በሰላሳ) ቀናት ውስጥ ለውጡን በጽሑፍ ለቢሮው ማሳወቅ አለበት፡፡

63. ኦዲተሮች

1. ኦዲተሮች የደንበኞቻቸውን የኦዲት ሪፖርት ለደንበኞቻቸው ካቀረቡበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ 3 (ሦስት) ወር ጊዜ ውስጥ የኦዲት ሪፖርቶቹን ለቢሮው ማቅረብ አለባቸው፡፡
2. ማንኛውም ኦዲተር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ግዴታ ሳይወጣ የቀረ እንደሆነ ቢሮው ኦዲተሩ ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን ለኢትዮጵያ የሂሳብና ኦዲት ቦርድ ወይም ለኢትዮጵያ የተመሠከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች ኢንሲቲትዩት በማሳወቅ ቦርዱ ወይም ኢንስቲትዩቱ የኦዲተሩን ፈቃድ እንዲሰረዝ ይጠይቃል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ "ኦዲተር" ማለት በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ለፐብሊክ

**62. Filing of Memorandum and Articles of Association**

1. A body shall file with the Bureau a copy of the memorandum of association, articles of association, statute, partnership agreement, or other document of formation or registration within 30 days of the date of registration of the body.
2. A body shall notify the Bureau, in writing, of any change made to a document referred to in sub-article (1) of this Article within 30 days of the change being made.

**63. Auditors**

1. Auditors shall file with the Bureau the audit report of their clients within three months from the date of providing the report to their client.
2. If an auditor fails to comply with sub-article (1) of this Article, the Bureau shall notify the Accounting and Auditing Board of Ethiopia or Institute of Certified Public Accountants of Ethiopia of the failure and may request the Board or the Institute to withdraw the auditor's licence.
3. In this Article, "auditor" means a certified auditor and a public auditor as defined under the Financial Reporting

አዲተር እና ለተመሰከረለት አዲተር የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

Proclamation.

**64. በኢትዮጵያ ነዋሪ ካልሆነ ሰው ጋር የሚደረግ የአገልግሎት ውልን ስለማሳወቅ**

1. ምንጩ ኢትዮጵያ የሆነ የአገልግሎት ውል በኢትዮጵያ ነዋሪ ካልሆነ ሰው ጋር የሚገባ ማንኛውም ሰው ውሉን ከፈረመበት ወይም መፈጸም ከጀመረበት ቀድሞ ከመጣው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በፀደቀው ቅጽ መሠረት ለቢሮው ማሳወቅ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ "ምንጩ ኢትዮጵያ የሆነ የአገልግሎት ውል" ማለት የቅጥር ውልን ሳይጨምር፣ የዕቃ አቅርቦትን ቢጨምርም ባይጨምርም በዋነኝነት አገልግሎት በመስጠት ላይ የተመሠረተ ምንጩ ኢትዮጵያ የሆነ ገቢ የሚያስገኝ የአገልግሎት ውል ነው፡፡

**64. Notification of Services Contract with Non-resident**

1. A person who enters into an Ethiopian source services contract with a non-resident shall notify the Bureau, in the approved form, within 30 days of the earlier of the signing of the contract or the commencement of performance under the contract.
2. In this Article, "Ethiopian source services contract" means a contract (other than an employment contract) under which the primary purpose is the performance of services, whether or not goods are also provided, which services give rise to Ethiopian source income.

**65. መረጃ ወይም ማስረጃ ለማግኘት ማስታወቂያ ስለመስጠት**

1. ማንኛውንም የታክስ ሕግ ለማስተዳደር ሲባል ቢሮው ታክስ ከፋይ ቢሆንም ባይሆንም ለማንኛውም ሰው የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት፡-

ሀ) በማስታወቂያው በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የራሱን ወይም የሌላ ማንኛውንም ሰው የታክስ ጉዳይ የሚመለከት በማስታወቂያው የተገለፀውን መረጃ እንዲሰጠው፤

ለ) በማስታወቂያው በተመለከተው ጊዜና ቦታ በመገኘት የራሱን ወይም የሌላ ማንኛውንም ሰው የታክስ ጉዳዮች በተመለከተ

**65. Notice to Obtain Information or Evidence**

1. For the purposes of administering any tax law, the Bureau may, by notice in writing, require any person whether or not liable for tax:

a) to furnish, by the time specified in the notice, such information relating to the person's or any other person's tax affairs as specified in the notice;

b) to present himself at the time and place designated in the notice to give evidence concerning the person's or

በማስታወቂያው የተገለጸውን ማስረጃ እንዲሰጠው፤

ሐ) በማስታወቂያው በተመለከተው ጊዜ ከእርሱ ወይም ከሌላ ማንኛውም ሰው የታክስ ጉዳዮች ጋር የሚገናኙ በእጁ ወይም በእርሱ ቁጥጥር ሥር ያሉ በማስታወቂያው የተገለፁ ሰነዶችን እንዲያቀርብ፣ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት እንዲቀርብ የተጠየቀው ሰነድ ከሆነ፣ የተጠየቀው ሰነድ መለየት በሚያስችል አኳኋን በማስታወቂያው መገለጹ በቂ ይሆናል፡፡

3. ይህ አንቀጽ፡-

ሀ) በኤሌክትሮኒክ መልክ የሚገኙትን ጨምሮ ማንኛውንም መረጃ መስጠትን ወይም ሰነድ ማቅረብን በተመለከተ ልዩ መብት የሚሰጥ ወይም የህዝብ ጥቅምንየሚመለከት ሌላ ሕግ፤ ወይም

ለ) ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታን የሚጥል ውል፤ ቢኖርም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

66. የመግባትና የመበርበር ሥልጣን

1. ማንኛውንም የታክስ ሕግ ለማስተዳደር ሲባል ቢሮው፡-

ሀ) በማንኛውም ጊዜና ያለምንም ማስታወቂያ በሚከተሉት ቦታዎች ላይ የመገኘት ወይም የሚከተሉትን የማግኘት ሙሉ እና ያለተገደበ መብት አለው፤

1. በማንኛውም ግቢ ወይም ቦታ፣ ማንኛውንም ዕቃ ወይም ንብረት፤

2. ማንኛውንም ሰነድ፤

any other person's tax affairs as specified in the notice;

c) to produce, by the time specified in the notice, all documents in the person's custody or under the person's control relating to the person's or any other person's tax affairs as specified in the notice.

2. When a notice under sub-article (1) of this Article requires the production of a document, it shall be sufficient if the document is described in the notice with reasonable certainty.

3. This Article shall have effect despite:

a) any law relating to privilege or the public interest with respect to the giving of information or the production of any documents (including in electronic format); or

b) any contractual duty of confidentiality.

**66. Power to Enter and Search**

1. For the purposes of administering any tax law, the Bureau:

a) shall have, at all times and without notice, full and free access to the following:

1. any premises, place, goods, or property;
2. any document;

3. ማንኛውንም የመረጃ ማከማቻ፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) በተሰጠው መብት መሠረት ያገኘውን በኤሌክትሮኒክ መልክ የተያዘን ጨምሮ የማንኛውንም ሰነድ የተወሰነ ክፍል ወይም ቅጂ ሊወስድ ይችላል፡፡

ሐ) ቢሮው የታክስ ከፋዩን የታክስ ግዴታ ለመወሰን ጠቃሚ ማስረጃ ይሆናል ብሎ የሚያምንበትን ማንኛውንም ሰነድ ሊይዝና በማንኛውም የታክስ ሕግ መሠረት የታክስ ከፋዩን የታክስ ግዴታ ለመወሰን ወይም ለማንኛውም የታክስ ክርክር እስካስፈለገ ጊዜ ድረስ ይዞ ማቆየት ይችላል፡፡

መ) የታተመ መረጃ ወይም በመረጃ ማጠራቀሚያ መሳሪያ የተከማቸ መረጃ ካልተሰጠው የመረጃውን ቅጅ ለመውሰድ አስፈላጊ ለሆነ ጊዜ መሳሪያውን ይዞ ማቆየት ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ሥልጣን ሊሰራበት የሚችለው የቢሮ ሀላፊ ወይም በዚህ ሥልጣን እንዲሠራ በየቢሮ ሀላፊ ግልጽ ውክልና የተሰጠው የታክስ ሠራተኛ ብቻ ነው፡፡

3. ማንኛውም የታክስ ሠራተኛ የቢሮ ሀላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ሥልጣን ሊሰራበት እንደሚችል ፈቃድ የሰጠው መሆኑን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስረጃ በባለቤቱ ወይም

3. any data storage device;

b) may make an extract or copy of any document, including in electronic format, to which access is obtained under paragraph (a) of this sub-article;

c) may seize any document that, in the opinion of the Bureau, affords evidence that may be material in determining the tax liability of a taxpayer and may retain the document for as long as the document may be required for determining a taxpayer's tax liability or for any proceeding under a tax law; and

d) may, if a hard copy or copy on a data storage media of information stored on a data storage device is not provided, seize and retain the device for as long as is necessary to copy the information required.

2. The powers in sub-article (1) of this Article may be exercised only by the head of the Bureau or a tax officer specifically authorised by the Head of the Bureau to exercise such powers.

3. A tax officer shall not enter or remain on any premises or place if, upon request by the owner or lawful occupier, the officer is unable to produce the Head of the Bureau's written authorisation permitting the officer to exercise powers under sub-article (1) of

ሕጋዊ ባለይዞታ በሆነ ሰው ሲጠየቅ ማቅረብ ካልቻለ ወደ ማንኛውም ግቢ ወይም ቦታ መግባት ወይም ገብቶ መቆየት አይችልም፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ የሚሆንበት ቦታ ወይም ግቢ ባለቤት ወይም ሕጋዊ ባለይዞታ ለቢሮው አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶችንና ድጋፍ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ይጨምራል፡-
   ሀ) ምርመራው በሚደረግበት ግቢ ወይም ቦታ የሚገኙ በመረጃ ማከማቻ ወይም በሌላ ማንኛውም መልክ የተያዙ ማናቸውንም ሰነዶች በተመለከተ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በቃል ወይም በጽሑፍ መልስ መስጠት፤ ወይም
   ለ) በዚህ አንቀጽ መሠረት የተፈለገው ዳታ በሚስጠር ቁልፍ የተጠበቀ እንደሆነ የተቆለፈው ዳታ የሚፈታበትን መረጃ መስጠት፤

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሰነድ ወይም የዳታ ማከማቻ መሳሪያ የተያዘበት ሰው ሰነዱን ወይም መሳሪያውን በመመርመር የፈለገውን መረጃ ቅጂ በዳታ ማከማቻ መሳሪያ ውስጥ የተያዙ ሰነዶች የኤሌክተሮኒክ ቅጂን ጨምሮ በመደበኛ የሥራ ሰዓትና ቢሮው በሚወስናቸው ቅድመ ሁኔታዎች መሠረት በራሱ ወጪ መውሰድ ይችላል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ መሠረት ለተወሰደና ለተያዘ ማንኛውም ሰነድ ወይም የዳታ ማከመቻ

this Article.

4. The owner or lawful occupier of the premises or place to which an exercise of power under sub-article (1) of this Article relates shall provide all reasonable facilities and assistance to the Bureau including:
   a) answering questions, either orally or in writing, relating to any document on the premises or at the place, whether on a data storage device or otherwise; or
   b) providing access to decryption information necessary to decrypt data to which access is sought under this Article.

5. A person whose document or data storage device has been seized under sub-article (1) of this Article may examine it and make copies, including electronic copies of documents on a data storage device, at his own expense, during normal office hours and on such terms and conditions as the Bureau may specify.

6. The Head of the Bureau or a tax officer authorised by the Head of the Bureau shall sign for any document or data

መሳሪያ የቢሮ ሀላፊ ወይም በየቢሮ ሀላፊ የተወከለ የታክስ ሠራተኛ በፊርማው ማረጋገጫ መስጠት አለበት፡፡

7. ይህ አንቀጽ፡-

ሀ) የሕግ ሙያን ጨምሮ ልዩ መብት የሚሰጥ ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተገናኘ በኤሌክትሮኒክ መልክ የሚገኙትን ጨምሮ ማንኛውንም ሰነድ ወይም ንብረት ማቅረብን፣ በማንኛውም ግቢ ወይም ቦታ መግባትን የሚመለከት ሌላ ሕግ፤ ወይም

ለ) ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታን የሚጥል ውል፤ ቢኖርም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**67. በታክስ ጉዳዮች የጋራ አስተዳደራዊ የመረዳዳት ስምምነቶችን ሥራ ላይ ስለማዋል**

1. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴሩ በታክስ ጉዳዮች ላይ መንግሥትን በመወከል ከውጭ ሀገር መንግሥት ወይም መንግሥታት ጋር የሚደረጉ የጋራ አስተዳደራዊ የመረዳዳት ስምምነቶችን ሊዋዋል፣ ሊያሻሽል ወይም ሊያቋርጥ ይችላል፡፡
2. በኢትዮጵያ ፀንተው በሚገኙ የጋራ አስተዳደራዊ የመረዳዳት ስምምነቶች እና በታክስ ሕግ መካከል ግጭት ከተፈጠረ የመረዳዳት ስምምነቶቹ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡
3. በኢትዮጵያ ውስጥ ፀንቶ ያለ የታክስ ወይም የጋራ አስተዳደራዊ የመረዳዳት ስምምነት የመረጃ ልውውጥን ወይም በሰጥቶ መቀበል

storage device removed and retained under this Article.

7. This Article shall have effect despite:

a) any law relating to privilege (including legal professional privilege) or the public interest with respect to access to premises or places, or the production of any property or document (including in electronic format); or

b) any contractual duty of confidentiality.

**67. Implementation of Mutual Administrative Assistance Agreements**

1. The Financial and Economic Cooperation Ministry may, on behalf of the Government, enter into, amend, or terminate a mutual administrative assistance agreement with a foreign government or governments.
2. If there is any conflict between the terms of a mutual administrative assistance agreement having legal effect in Ethiopia and a tax law, the mutual administrative assistance agreement prevails.
3. If a tax treaty or mutual administrative assistance agreement having legal effect in Ethiopia provides for exchange of information, or reciprocal assistance in the

መርህ ላይ የተመሠረተ ታክስ የመሰብሰብ ትብብርን ወይም መጥሪያ መስጠትን የሚያስችሉ ድንጋጌዎች የያዙ ከሆነ፣ ቢሮው በስምምነቶቹ መሠረት የኢትዮጵያን ግዴታዎች ለመወጣት በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ በማንኛውም ሕግ የተሰጠውን ሥልጣን መጠቀም የሚኖርበት ሲሆን፤ ለዚህ ዓላማ በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ ሕግ፡-

ሀ) "ታክስ" የመረጃ ልውውጥ ወይም የጋራ መረዳዳት ስምምነት የሚመለከተው የውጭ ሀገር ታክስን፣

ለ) "ያልተከፈለ ታክስ" በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተውንና በመክፈያ ጊዜው ያልተከፈለን ታክስ፤

ሐ) "ታክስ ከፋይ" በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተውን ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበትን ሰው፤ እንዲሁም

መ) "የታክስ ሕግ" በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተው የውጭ ሀገር ታክስ የሚጣልበትን ሕግ፤ ይጨምራል፡፡

4. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ፡-

ሀ) "ዓለም አቀፍ ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ እና በውጭ ሀገር መንግሥት ወይም መንግሥታት መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው፡፡

ለ) "የጋራ አስተዳደራዊ የመረዳዳት ስምምነት" ማለት ከታክስ ጉዳዮች ጋር በተገናኘ የታክስ መረጃ ልውውጥ ስምምነት ወይም የጋራ አስተዳደራዊ

recovery of tax or the service of process, the Bureau shall use the powers available under this Proclamation or any other law to meet Ethiopia's obligations under the treaty or agreement on the basis that a reference in this Proclamation or other law:

a) to "tax", includes a foreign tax to which the exchange of information or reciprocal assistance relates;

b) to "unpaid tax", includes an amount specified in paragraph (a) of this sub-article that has not been paid by the due date;

c) to "taxpayer", includes a person liable for an amount specified in paragraph (a) of this sub-article; and

d) to "tax law", includes the law under which a foreign tax specified in paragraph (a) of this sub-article is imposed.

4. In this Article:

a) "international agreement" means an agreement between the Government of Ethiopia and a foreign government or governments;

b) "mutual administrative assistance agreement" means a tax information exchange agreement or other international agreement for mutual administrative

መረዳዳት እንዲኖር የሚደረግ ሌላ ዓለም አቀፍ ስምምነት ነው፡፡

ሐ) "የታክስ ስምምነት" ማለት ተደራራቢ ታክስን ለማስቀረት እና የታክስ ማጭበርበርን ለመከላከል የሚደረግ ዓለም አቀፍ ስምምነት ነው፡፡

## ክፍል አሥራ አንድ
## የታክስ ሕጎችን አስቀድሞ መተርጎም
## ምዕራፍ አንድ
## በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም

### 68. አስገዳጅ የሆኑ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ትርጉሞች

1. ቢሮው አንድን የታክስ ሕግ አስመልክቶ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 69 መሠረት በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 69 መሠረት የተሰጠ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም እስካልተነሳ ድረስ በቢሮው ላይ አስገዳጅ ይሆናል፡፡
3. በቢሮ የተሰጠ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በታክስ ከፋዮች ላይ አስገዳጅ አይሆንም፡፡

### 69. በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ስለመስጠት

1. ቢሮው የሚሰጠው በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በኦፊሴላዊ ድረ-ገጹ ላይ ማውጣት አለበት፡፡
2. ቢሮው የሚያወጣው በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም

assistance in relation to taxation matters; and

c) "tax treaty" means an international agreement relating to the avoidance of double taxation and the prevention of fiscal evasion.

## PART ELEVEN
## ADVANCE RULINGS
## CHAPTER ONE
## PUBLIC RULINGS

### 68. Binding Public Rulings

1. The Bureau may make a public ruling in accordance with Article 69 of this Proclamation setting out interpretation on the application of a tax law.
2. A public ruling made in accordance with Article 69of this Proclamation shall be binding on the Bureau until withdrawn.
3. A public ruling shall not be binding on a taxpayer.

### 69. Making a Public Ruling

1. The Bureau shall make a public ruling by publishing the public ruling on the official website.
2. A public ruling set by the Bureau shall state that it is a public ruling and shall have a heading specifying

በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ መሆኑን መግለጽ የሚኖርበት ሲሆን በትርጉሙ የተመለከተውን ጉዳይ የሚገልጽ ርዕስና መለያ ቁጥር ሊኖረው ይገባል፡፡

3. በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በዚሁ ትርጉም ላይ ከተመለከተው ቀን ጀምሮ ተፈጻሚነት የሚኖረው ሲሆን በትርጉሙ ላይ ምንም ቀን ካልተመለከተ ትርጉሙ በቢሮው ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ትርጉም በትርጉሙ በተገለፀው ሁኔታ የአንድን ታክስ ሕግ አፈጻፀም በሚመለከት የቢሮ አስተያየት የሚገልጽ ሲሆን ለዚህ አዋጅ ወይም ለሌላ ሕግ አፈጻፀም ሲባል የቢሮው ውሳኔ ተደርጎ አይወሰድም፡፡

### 70. በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉምን ስለማንሳት

1. የፋይናንስ ቢሮ በኦፊሴላዊ ድረ-ገጹ ላይ ማስታወቂያ በማውጣት በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉምን በሙሉ ወይም በከፊል ሊያነሳ ይችላል፡፡ ይህም ሲሆን የትርጉሙ ተፈጻሚነት መቋረጥ፡-

ሀ/ በማስታወቂያ ከተገለፀው ቀን፤ ወይም

ለ/ ማስታወቂያው በፋይናንስ ቢሮ ኦፊሴላዊ

the subject matter of the ruling by which it can be identified and an identification number.

3. A public ruling shall have effect from the date specified in the public ruling or, when no date is specified, from the date the ruling is published on the official website of the Bureau.

4. A public ruling set out the Bureau's opinion on the application of a tax law in the circumstances specified in the ruling and is not a decision of the Bureau for the purposes of this Proclamation or any other law.

### 70. Withdrawal of a Public Ruling

1. The Finance Bureau may withdraw a public ruling, in whole or part, by publishing notice of the withdrawal on the official website of the Bureau and the withdrawal shall have effect from the later of:

a) the date specified in the notice of withdrawal; or

b) the date that the notice of withdrawal of the

ድረ-ገጽ ላይ ከወጣበት ቀን ከሁለቱ በዘገየው ቀን ይጀምራል፡፡

2. በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ ከሚሆን ትርጉም ጋር የሚቃረን ሕግ ከወጣ ወይም ቢሮው የተለየ ትርጉም ከሰጠ ነባሩ ትርጉም ከሕጉ ወይም ከተሰጠው አዲስ ትርጉም ጋር የማይጣጣም እስከሆነ ድረስ እንደተነሳ ይቆጠራል፡፡

3. በሙሉ ወይም በከፊል የተነሳ በሁሉም ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም፡-

ሀ) ከመነሳቱ በፊት ለተጀመሩ ግብይቶች ተፈጻሚ መሆኑ ይቀጥላል፤

ለ) ከተነሳ በኋላ ለተጀመረ ግብይት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም

### 71. አስገዳጅ የሆኑ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ትርጉሞች

1. ማንኛውም ታክስ ከፋይ በፈጸመው ወይም ሊፈጽም ባሰበው ግብይት ላይ የአንድን ታክስ ሕግ ተፈጻሚነት በተመለከተ የፋይናንስ ቢሮ አቋም ምን እንደሆነ የሚገልጽ ትርጉም እንዲሰጠው ለፋይናንስ ቢሮ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ በጽሑፍ ሆኖ፡-

ሀ) ከማመልከቻው ጋር ግንኙነት ያለውን

ruling is published on the official website of the Finance Bureau.

2. When legislation is passed, or the Bureau makes another public ruling that is inconsistent with an existing public ruling, the existing public ruling shall be treated as withdrawn to the extent of the inconsistency from the date of application of the inconsistent legislation or public ruling.

3. A public ruling that has been withdrawn, in whole or part:

a) shall continue to apply to a transaction commenced before the public ruling was withdrawn; and

b) shall not apply to a transaction commenced after the public ruling was withdrawn to the extent that the ruling is withdrawn.

## CHAPTER TWO

## PRIVATE RULINGS

### 71. Binding Private Rulings

1. A taxpayer may apply to the Bureau for a private ruling setting out the Bureau's position regarding the application of a tax law to a transaction entered into, or proposed to be entered into, by the taxpayer.

2. An application under this Article shall be in writing and:

a) include full details of the transaction

ግብይት ዝርዝር ጉዳዮችና ለግብይቱ አግባብነት ያላቸውን ሁሉንም ሰነዶች ማካተት፣

ለ) ትርጉሙ የተጠየቀበትን ጉዳይ በግልጽ ማመልከት፣ እንዲሁም

ሐ) አግባብነት ያለው የታክስ ሕግ ለግብይቱ ያለውን ተፈጻሚነት በተመለከተ የታክስ ከፋዩን አስተያየት ሙሉ መግለጫ መያዝ፣ አለበት፡፡

3. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 72 እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የፋይናንስ ቢሮ በዚህ አንቀጽ መሠረት የቀረበው ማመልከቻ በደረሰው በ60 (ስልሳ) ቀናት ውስጥ ለቀረበለት ጥያቄ ጉዳዩን የሚመለከት ትርጉም መስጠት አለበት፡፡

4. ታክስ ከፋዩ ትርጉሙ ለተጠየቀበት ግብይት አግባብነት ያለውን ትክክለኛ እና የተሟላ ማስረጃ ያቀረበ እና ግብይቱም በማንኛውም ረገድ በቀረበው ማመልከቻ እንደተገለጸው መከናወኑ ከተረጋገጠ በዚህ ላይ ተመስርቶ የተሰጠው ትርጉም በፋይናንስ ቢሮ እና በቢሮው ላይ አስገዳጅ ይሆናል፡፡

5. በፋይናንስ ቢሮ የሚሰጥ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በታክስ ከፋዩ ላይ አስገዳጅ አይሆንም፡፡

6. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ትርጉሙ በተሰጠበት ጊዜ ጸንቶ ካለ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ ከሚሆን ትርጉም ጋር የሚቃረን ከሆነ በሁለቱ ትርጉሞች መካከል ያለውን ልዩነት

to which the application relates together with all documents relevant to the transaction;

b) specify precisely the question on which the ruling is required; and

c) give a full statement setting out the opinion of the taxpayer as to the application of the relevant tax law to the transaction.

3. Subject to Article 72 of this Proclamation, the Bureau shall, within 60 days of receipt of the application under this Article, issue a private ruling on the question to the taxpayer.

4. If the taxpayer has made a full and true disclosure of all aspects of the transaction relevant to the making of a private ruling and the transaction has proceeded in all material respects as described in the taxpayer's application for the private ruling, the private ruling shall be binding on the Finance Bureau and the Bureau.

5. A definition applicable to a taxpayer issued by the Finance Bureau shall not be binding on the taxpayer.

6. When a private ruling is inconsistent to a definition applicable to all taxpayers if the meaning is valid at the time the meaning is given, the definition given to apply to a single taxpayer with respect to the difference between the two meanings shall

በሚመለከት በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን የተሰጠ ትርጉም ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

apply.

**72. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ለመጠየቅ የቀረበን ማመልከቻ ስለአለመቀበል**

1. የፋይናንስ ቢሮ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም እንዲሰጥ በታክስ ከፋዩ የቀረበን ማመልከቻ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ላይቀበለው ይችላል፡-
   ሀ) የፋይናንስ ቢሮ እንደአግባብነቱ ማመልከቻ በቀረበበት ጥያቄ ላይ በሚከተሉት ሁኔታዎች ውሳኔ ሰጥቶበት ከሆነ፡-
      1. የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከተሰጠው፤
      2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 69 መሠረት የተሰጠ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በሥራ ላይ ያለ ከሆነ፤
      3. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 75 መሠረት በፋይናንስ ቢሮ ድረ-ገጽ ወጥቶ በሥራ ላይ ያለ ከሆነ፤
   ለ) ማመልከቻው ታክስ ከፋዩን ከሚመለከት በታክስ ኦዲት ሥር ካለ ጉዳይ ጋር የተገናኘ፣ ታክስ ከፋዩ ተቃውሞ ካቀረበበት ጉዳይ ጋር የተገናኘ ወይም ታክስ ከፋዩ ራሱ ያሰላውን የታክስ መጠን ለማሻሻል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 መሠረት ከቀረበ

**72. Refusing an Application for a Private Ruling**

1. The Finance Bureau may refuse an application by a taxpayer for a private ruling if any of the following applies:
   a) the Finance Bureau, as the case maybe, has already decided the question that is the subject of the application in the following:
      1. a notice of a tax assessment served on the taxpayer;
      2. a public ruling published on the website of the Finance Bureau under Article 69 of this Proclamation that is in force;
      3. a private ruling published the website of the Finance Bureau under Article 75 of this Proclamation that is in force.
   b) the application relates to a question that is the subject of a tax audit in relation to the taxpayer, an objection filed by the taxpayer, or an application by the taxpayer under Article 29of this Proclamation for an amendment to a self-assessment;

ማመልከቻ ጋር የተገናኘ ከሆነ፤

ሐ) ማመልከቻው ፋይዳ የሌለው ወይም ሁከት ለመፍጠር የቀረበ ከሆነ፤

መ) ማመልከቻው የቀረበበት ግብይት ያልተካሄደ ሲሆን ወይም ግብይቱ ሊካሄድ እንደማይችል ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ካለ፤

ሠ) ታክስ ከፋዩ ትርጉሙን ለመስጠት የሚያስችል በቂ መረጃ ለፋይናንስ ቢሮ ያላቀረበ ከሆነ፤

ረ) ማመልከቻውን ለመቀበል የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች እና ለፋይናንስ ቢሮ አግባብነት አላቸው የሚላቸውን ሌሎች ጉዳዮች ግምት ውስጥ በማስገባት በፋይናንስ ቢሮ አስተያየት ማመልከቻውን መቀበል ምክንያታዊ ካልሆነ፤

ሰ) ትርጉሙን መሰጠት የታክስ ማስወገጃ ድንጋጌን ተፈጻሚነት የሚያካትት ሲሆን፤

4. የፋይናንስ ቢሮ በዚህ አንቀጽ መሠረት በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም እንዲሰጥ የቀረበን ማመልከቻ ውድቅ ለማድረግ መወሰኑን ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

**73. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ስለመስጠት**

1. ፋይናንስ ቢሮ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ሲሰጥ ለአመልካቹ ታክስ ከፋይ በጽሑፍ ማሳወቅ ያለበት ሲሆን በዚህ ዓይነት የሚሰጥ ትርጉም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 74 ቀደም ብሎ ካልተነሳ በስተቀር

c) the application is frivolous or vexatious;

d) the transaction to which the application relates has not been carried out and there are reasonable grounds to believe that the transaction will not be carried out;

e) the tax payer has not provided the Bureau with sufficient information to make a private ruling;

f) in the opinion of the Bureau, it would be unreasonable to comply with the application, having regard to the resources needed to comply with the application and any other matters the Bureau considers relevant;

g) the making of the ruling involves the application of a tax avoidance provision.

2. The Finance Bureau shall serve the taxpayer with a written notice of a decision to refuse to make a private ruling under this Article.

**73. Making a Private Ruling**

1. The Finance Bureau shall make a private ruling by serving written notice of the private ruling on the taxpayer and the ruling shall remain in force for the period specified in the ruling or, if earlier, withdrawn under Article 74 of this

በትርጉሙ ለተጠቀሰው ጊዜ የሚያገለግል ይሆናል፡፡

2. ፋይናንስ ቢሮ ወደፊት ሊከሰት የሚችልን ነገር ወይም ሌላ አግባብነት ያለውን ጉዳት ታሳቢ በማድረግ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ሊሰጥ ይችላል፡፡

3. የተሰጠው ትርጉም በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን እና ትርጉሙ የተሰጠበትን ጥያቄ መግለጽ ያለበት ሆኖ የሚከተሉትን ጉዳዮችም መያዝ ይኖርበታል፡-
   ሀ) ታክስ ከፋዩን፤
   ለ) ለትርጉሙ አግባብነት ያለውን የታክስ ሕግ፤
   ሐ) ትርጉሙ ተፈጻሚ የሚሆንበትን የታክስ ዘመን፤
   መ) ትርጉሙ የሚመለከተውን ግብይት፤
   ሠ) ትርጉሙ የተመሠረተባቸውን ታሳቢዎች፤

4. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በቀረበው ማመልከቻ በተመለከተው ጉዳይ ላይ የፋይናንስ ቢሮን አስተያየት የሚገልጽ ሲሆን ለዚህ አዋጅ ወይም ለሌላ ሕግ አፈጻፀም ሲባል የቢሮው ውሳኔ ተደርጎ አይወሰድም፡፡

**74. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉምን ስለማንሳት**

1. ፋይናንስ ቢሮ በቂ ምክንያት ሲኖር በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ለሚመለከተው ታክስ ከፋይ የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት በሙሉ ወይም በከፊል

Proclamation.

2. The Finance Bureau may make a private ruling on the basis of assumptions about a future event or other matter as considered appropriate.

3. A private ruling shall state that it is a private ruling, set out the question ruled on, and identify the following:
   a) the taxpayer;
   b) the tax law relevant to the private ruling;
   c) the tax period to which the ruling applies;
   d) the transaction to which the ruling relates;
   e) any assumptions on which the ruling is based.

4. A private ruling sets out the Finance Bureau’s opinion on the question raised in the ruling application and is not a decision of the Bureau for the purposes of the Proclamation or any other law.

**74. Withdrawal of a Private Ruling**

1. The Finance Bureau may, for reasonable cause, withdraw a private ruling, in whole or part, by written notice served on the taxpayer and the withdrawal shall have effect from the date specified in the notice

ሊያነሳ ይችላል፡፡ ይህም ሲሆን ትርጉሙ በማስታወቂያው ላይ ከተገለጸው ቀን ጀምሮ እንደተነሳ ይቆጠራል፡፡

2. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ ከሚሆን ትርጉም ጋር የሚቃረን ሕግ ከወጣ ወይም ፋይናንስ ቢሮ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን አዲስ ትርጉም ከሰጠ ነባሩ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ከሕጉ ወይም ከተሰጠው አዲስ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ጋር የማይጣጣም እስከሆነ ድረስ እንደተነሳ ይቆጠራል፡፡

3. የተነሳ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም፡-

   ሀ) ከመነሳቱ በፊት ለተጀመሩ የታክስ ከፋዩ ግብይቶች ተፈጻሚ መሆኑ ይቀጥላል፤

   ለ) ከተነሳ በኂላ ለተጀመረ የታክስ ከፋዩ ግብይት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**75. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም መሰጠቱን ስለማሳወቅ**

1. ፋናንስ ቢሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 73 መሠረት የሰጠውን በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በኦፊሴላዊ ድረ-ገጹ ላይ ማውጣት አለበት፡፡ ሆኖም ትርጉሙ የሚመለከተውን ታክስ ከፋይ ማንነት እና በትርጉሙ የተጠቀሰውን ማንኛውንም ሚስጥራዊ የንግድ መረጃ ይፋ ማድረግ የለበትም፡፡

of withdrawal.

2. When legislation is passed, or the Bureau makes a public ruling that is inconsistent with an existing private ruling, the private ruling shall be treated as withdrawn to the extent of the inconsistency from the date of application of the inconsistent legislation or public ruling.

3. private ruling that has been withdrawn:

   a) shall continue to apply to a transaction of the taxpayer commenced before the ruling was withdrawn; and

   b) shall not apply to a transaction of the taxpayer commenced after the ruling was withdrawn to the extent the ruling is withdrawn.

**75. Notification of Private Rulings**

1. The Finance Bureau shall publish a private ruling made under Article 73of this Proclamation on the official website of the Bureau except that the identity of the taxpayer to whom the ruling relates and any confidential commercial information mentioned in the ruling shall not be indicated in the publication.

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ታክስ ከፋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ይፋ በሆነ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ሊጠቀም የሚችል ሲሆን ቢሮው እና ፋይናንስ ቢሮ በትርጉሙ ለተመለከቱት ፍሬ ነገሮች አግባብነት ላለው የታክስ ሕግ ተፈጻሚነት እና ትርጉሙ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ይፋ በተደረገው ትርጉም ይገደዳሉ፡፡

3. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 74 መሠረት ሲነሳ የፋይናንስ ቢሮ የትርጉሙ አስገዳጅነት በአንቀጽ 74 ከተመለከተው ቀን ጀምሮ የሚቋረጥ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ወዲያውኑ በኦፊሴላዊ ድረ-ገጹ ላይ ማውጣት አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የፋይናንስ ቢሮ ሌሎች አስተያየቶች

### 76. የፋይናንስ ቢሮ የሚሰጣቸው ሌሎች አስተያየቶች

በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ከሚሰጡ በፋይናንስ ቢሮ እና በቢሮው ላይ አስገዳጅ ከሆኑና በሁሉም ታክስ ከፋዮች ወይም በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ ከሚሆኑ ትርጉሞች በስተቀር በፋይናንስ ቢሮ የሚቀርቡ የሕትመት ውጤቶች ወይም በሌላ መልኩ በቃልም ሆነ በጽሑፍ የሚሰጡ አስተያየቶች በፋይናንስ ቢሮ ወይም በቢሮው ላይ አስገዳጅነት አይኖራቸውም፡፡

2. Subject to sub-article (3) of this Article, any taxpayer may rely upon a ruling published under sub-article (1) of this Article as a statement binding on the Bureau and the Finance Bureau with respect to the application of the relevant tax law to the facts set out in the ruling and for the tax period covered by the ruling.

3. When a private ruling has been withdrawn in accordance with Article 74 of this Proclamation shall immediately publish a notice of withdrawal on the official website of the Finance Bureau stating that the ruling shall cease to be binding with effect from the date determined under Article 74 of this Proclamation.

## CHAPTER THREE

## OTHER ADVICE OF THE MINISTRY

### 76. Other Advice Provided by the Finance Bureau

No Publications or otherwise (oral or in writing) comments made by the Finance Bureau shall not be binding on the Finance Bureau or the Bureau, except for translations that are binding on the Bureau of Finance and the Bureau issued pursuant to the provisions of this section and applicable to all taxpayers or to a single taxpayer.

## ክፍል አሥራ ሁለት

## ግንኙነቶች፣ ቅጾችና ማስታወቂያዎች

### 77. የሥራ ቋንቋ

አማርኛ የክልሉ መንግስት የስራ ቋንቋ በመሆኑ የክልሉ የሥራ ቋንቋ የታክስ ሕጎች አፊሴላዊ ቋንቋ ነው፡፡ ስለሆነም ቢሮው በአፊሴላዊ ቋንቋዎች ያልቀረበን ግንኙነት ወይም ሰነድ ዕውቅና ላይሰጠው ይችላል፡፡

### 78. ቅጾች እና ማስታወቂያዎች

1. ቅጾች፣ ማስታወቂያዎች፣ የታክስ ማስታወቂያዎች፣ መግለጫዎች፣ ሠንጠረዦች እና ሌሎች በቢሮው የሚፀድቁ ወይም የሚታተሙ ሰነዶች የታክስ ሕጎችን በብቃት ለማስተዳደር ቢሮው በወሰነው ቅጽ የሚዘጋጁ ሲሆን የታክስ ሕግ በሌላ አኳኋን ካልደነገገ በስተቀር እነዚህን ሰነዶች በቢሮው ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ ላይ ማውጣት አስገዳጅ አይደለም፡፡
2. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን ሰነዶች በቢሮው ቢሮዎች ወይም በሌላ ቦታዎች ወይም በፖስታ፣ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ፣ ወይም ቢሮው በሚወሰነው ሌላ ዘዴ ሕዝብ እንዲያገኛቸው ማድረግ አለበት፡፡

### 79. የፀደቀ ቅጽ

1. በታክስ ከፋይ የሚቀርብ ማንኛውም የታክስ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ፣ ማስታወቂያ፣ መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ በፀደቀው ቅጽ መሠረት እንደቀረበ የሚቆጠረው ሰነዱ፡-

ሀ) ለሰነዱ ዓይነት በቢሮው በፀደቀ ቅጽ

## PART TWELVE

## Communications, Forms, and Notices

### 77. Working Languages

Working Languages of the Region shall be the official languages of the tax laws; and the Bureau may refuse to recognise any communication or document that is not conducted in official languages.

### 78. Forms and Notice

1. Forms, notices, tax declarations, statements, tables, and other documents approved or published by the Bureau may be in such form as the Bureau determines for the efficient administration of the tax laws and, except as required under a tax law, publishing of such documents on the official website of the Bureau shall not be required.
2. The Bureau shall make the documents referred to in sub-article (1) of this Article available to the public at offices of the Bureau and at any other locations, or by mail, electronically, or such other means, as the Bureau may determine.

### 79. Approved Form

1. A tax declaration, application, notice, statement, or other document shall be treated as filed by a taxpayer in the approved form when the document:

a) is in the form approved by the

መሠረት የቀረበ፤

ለ) ማንኛውንም ተያያዥ ሰነዶች ጨምሮ ቅጹ የሚጠይቀውን መረጃ የያዘ፤ እና

ሐ) ቅጹ በሚጠይቀው መሠረት የተፈረመ፤ ሲሆን ነው።

2. ታክስ ከፋዩ ለቢሮው ያቀረበው የታክስ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ፣ ማስታወቂያ፣ መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ በፀደቀው ቅጽ መሠረት ያልቀረበ ከሆነ ቢሮው ሰነዱ በፀደቀው ቅጽ መሠረት ያልቀረበ መሆኑን ለዚሁ ሰው ወዲያውኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

3. አንድ ሰነድ በፀደቀው ቅጽ መሠረት ያልቀረበ ቢሆንም ሰነዱ በፀደቀው ቅጽ መሠረት የሚፈለጉትን አብዛኞቹን መረጃዎች በያዘ ቅጽ የቀረበ እንደሆነ ቢሮው ይህንን ሰነድ ሊቀበለው ይችላል።

### 80. ሰነዶች ለቢሮው ስለሚቀርቡበት አኳኋን

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተገለጸው መንገድ እንዲያቀርብ በቢሮው በጽሑፍ ካልተፈቀደለት በስተቀር ማንኛውም ታክስ ከፋይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 82 (2) መሠረት ለቢሮው ማቅረብ የሚጠበቅበትን የታክስ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ፣ ማስታወቂያ፣ መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ማቅረብ አለበት።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ተፈጻሚ የማይሆንበት ታክስ ከፋይ የታክስ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ፣ ማስታወቂያ፣

Bureau for that type of document;

b) contains the information (including any attached documents) as required by the form; and

c) is signed as required by the form.

2. The Bureau shall immediately notify a taxpayer, in writing, when a tax declaration, application, notice, statement, or other document filed by the person is not in the approved form.

3. The Bureau may decide to accept a document that is not filed in the approved form if the document has been filed in a form that contains substantially the information required by the approved form for the document.

### 80. Manner of Filing Documents with the Bureau

1. A taxpayer required by the Bureau under Article 82 (2) of this Proclamation to file a tax declaration, application, notice, statement, or other document with the Bureau electronically shall do so unless authorised by the Bureau by notice in writing to file the document in accordance with sub-article (2) of this Article.

2. When sub-article (1) of this Article does not apply to a taxpayer, the taxpayer shall file a tax declaration, application, notice, statement, or other document with the

መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ በአካል ወይም መደበኛ ፖስታ በመጠቀም ለቢሮው ያቀርባል፡፡

**81. ማስታወቂያዎችን ስለመስጠት**

1. በታክስ ሕግ መሠረት ለአንድ ታክስ ከፋይ የወጣ፣ እንዲደርስ የሚደረግ ወይም የሚሰጥ ማስታወቂያ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰነድ ለታክስ ከፋዩ በሚከተለው አኳኋን በጽሑፍ ሊደርሰው ይገባል፦
   ሀ) ለታክስ ከፋዩ ወይም ለታክስ እንደራሴው ወይም ለታክስ ወኪሉ በአካል በመስጠት ወይም የተላከውን ሰነድ የሚቀበል ሰው ካልተገኘ ማስታወቂያውን ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የታክስ ከፋዩ የንግድ ወይም መኖሪያ ቤት በር ላይ ወይም ሌላ አመቺ ቦታ ላይ በመለጠፍ፤
   ለ) ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የታክስ ከፋዩ መደበኛ ወይም በመጨረሻ የሚታወቀው የንግድ ቦታ ወይም መኖሪያ ቤት በሪኮማንዴ ደብዳቤ በመላክ፤
   ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 82 (3) መሠረት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለታክስ ከፋዩ በማስተላለፍ፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን ዘዴዎች በመጠቀም ማስታወቂያውን ማድረስ ካልተቻለ፣ የህትመት ወጪው በታክስ ከፋዩ የሚሸፈን ሆኖ የፍርድ ቤት ማስታወቂያዎች በሚወጡበት ጋዜጣ ማስታወቂያውን

Bureau under a tax law by personal delivery or normal post.

**81. Service of Notices**

1. A notice or other document issued, served, or given by the Bureau under a tax law to a taxpayer shall be communicated in writing as follows:
   a) by delivering it personally to the taxpayer or the taxpayer's tax representative or licensed tax agent, or, if no person can be found to accept service, by affixing the notice to the door or other available part of the taxpayer's place of business or residence in Ethiopia;
   b) by sending it by registered post to the taxpayer's usual or last known place of business or residence in Ethiopia;
   c) by transmitting it to the taxpayer electronically in accordance with Article 82 (3) of this Proclamation.
2. When none of the methods of service specified in sub-article (1) of this Article are effective, service may be discharged by publication in any newspaper in which court notices may be advertised with the cost of publication charged to the taxpayer.

በማውጣት ማስታወቂያው እንዲደርስ ማድረግ ይቻላል፡፡

3. ማንኛውም ታክስ ከፋይ በታክስ ሕግ መሠረት በደረሰው ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ መሠረት የሚፈለግበትን ተግባር በሙሉ ወይም በከፊል ከፈጸመ በኋላ ማስታወቂያው ወይም ሌላው ሰነድ እንዲደርሰው በተደረገበት መንገድ ሕጋዊነት ላይ ተቃውሞ ሊቀርብ አይችልም፡፡

3. No objection shall be made to the legality of the validity of service of a notice or other document under a tax law shall not be challenged after the notice or document has been wholly or partly complied with.

## 82. የኤሌክትሮኒክ የታክስ ሥርዓትን ተግባራዊ ስለማደረግ

1. በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን የሚደነግግ አንቀጽ ቢኖርም፣ ቢሮው የሚከተሉት ተግባራት በኮምፒዩተር ሥርዓት ወይም በሌላ ተንቀሳቃሽ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ አማካኝነት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ እንዲከናወኑ ሊፈቅድ ይችላል፡-

   ሀ) በታክስ ሕግ መሠረት ለመመዝገብ ወይም የታክስ መለያ ቁጥር ለማግኘት ማመልከቻ ለማቅረብ፤

   ለ) በታክስ ሕግ መሠረት የታክስ ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ ለማቅረብ፤

   ሐ) በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ ወይም ሌላ ክፍያ ለመፈጸም፤

   መ) በታክስ ሕግ መሠረት የታክስ ተመላሽ ክፍያ ለመፈጸም፤

   ሠ) ቢሮው የሚያስተላልፈውን ማንኛውንም ሰነድ ለመላክ፤

   ረ) በታክስ ሕግ መሠረት መከናወን

## 82. Application of Electronic Tax System

1. Despite any other provisions of this Proclamation, the Bureau may authorise the following to be done electronically through a computer system or mobile electronic device:

   a) the lodging of an application for registration or for a TIN under a tax law;

   b) the filing of a tax declaration or other document under a tax law;

   c) the payment of tax or other amounts under a tax law;

   d) the payment of a refund under a tax law;

   e) the service of any documents by the Bureau;

   f) the doing of any other act or

የሚኖርበትን ወይም እዲከናወን የተፈቀደ ሌላ ድርጊት ወይም ነገር ለማከናወን፤

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ማንኛውም ተግባር የኮምፒዩተር ሥርዓትን ወይም ሌላ ተንቀሳቃሽ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያን በመጠቀም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ እንዲፈጽም ታክስ ከፋይን ሊያዝ ይችላል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተከመለከተውን ማንኛውንም ተግባር የኮምፒዩተር ሥርዓትን ወይም ሌላ ተንቀሳቃሽ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያን በመጠቀም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊያከናውን ይችላል፡፡

4. ታክስ ከፋዩ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ግንኙነቶችን ለመቀበል ወይም ለማድረግ የሚያስችለው አቅም እንደሌለው ቢሮው ካመነበት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ( 2) እና ( 3) ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

5. በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የታክስ ማስታወቂያ የሚያቀርብና ታክስ የሚከፍል ማንኛውም ታክስ ከፋይ እነዚህን ተግባራት ለማከናወን በሌላ ዘዴ እንዲጠቀም ቢሮው ካልፈቀደለት በስተቀር በዚሁ ዘዴ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

83. ሰነድ የማቅረቢያ ወይም ታክስ የመክፈያ ጊዜ

ሀ) የታክስ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ፣

thing that is required or permitted to be done under a tax law.

2. Subject to sub-article (4) of this Article, the Bureau may direct that a taxpayer shall do anything referred to in sub-article (1) of this Article electronically through the use of a computer system or mobile electronic device.

3. Subject to sub-article (4) of this Article, the Bureau may do anything referred to in sub-article (1) of this Article electronically through the use of a computer system or mobile electronic device.

4. Sub-articles (2) and (3) shall not apply to a taxpayer if the Bureau is satisfied that the taxpayer does not have the capacity to receive or make communications or payments electronically.

5. A taxpayer who files a tax declaration and pays tax electronically under this Article shall continue to do so unless otherwise authorised by the Bureau.

**83. Due Date for Filing a Document or Payment of Tax**

a) If the due date for filing a tax declaration,

ማስታወቂያ፣ መግለጫ፣ ወይም ሌላ ሰነድ የሚቀርብበት ቀን፤

ለ) የታክስ መክፈያ ቀን፤ ወይም

ሐ)በታክስ ሕግ መሠረት ሌላ ማንኛውም እርምጃ የሚወሰድበት ቀን፤ ቅዳሜ፣ እሁድ ወይም በኢትዮጵያ የህዝብ በዓል ቀን ላይ ከዋለ ሰነዱ የሚቀርብበት ክፍያው የሚፈጸምበት ወይም በታክስ ሕግ መሠረት ሌላ ማንኛውም እርምጃ የሚወሰድበት ቀን የሚቀጥለው የሥራ ቀን ይሆናል፡፡

application, notice, statement, or other document;

b) If the due date for the payment of tax; or

c) taking any other action under a tax law, falls on a Saturday, Sunday, or public holiday in Ethiopia, the due date shall be the following business day.

**84. ማስታወቂያን ተቀባይነት የማያሳጣ ጉድለት**

1. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ የሚሆነው፡-

ሀ) በታክስ ሕግ መሠረት የተዘጋጀ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ ለታክስ ከፋዩ የተሰጠው ከሆነ፣

ለ) የተሰጠው ማስታወቂያ በይዘቱ እና በውጤቱ ማስታወቂያው መሠረት ካደረገው የታክስ ሕግ ዓላማ እና መንፈስ ጋር የሚስማማ ወይም የተጣጣመ ከሆነ፣ እና

ሐ) የታክስ ስሌቱ የሚመለከተው፣ ይመለከተዋል ተብሎ የሚታሰበው ወይም ማስታወቂያው የሚመለከተው ታክስ ከፋይ በማስታወቂያው የተሰየመው የጋራ ዓላማን እና ግንዛቤን መሠረት አድርጎ ከሆነ ነው፡፡

2. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ፡-

ሀ) የታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ማንኛውም ሌላ ሰነድ ለታክስ ከፋዩ በአግባቡ እንዲደርሰው እስከተደረገ ድረስ ለማስታወቂያው መሠረት የሆነው የታክስ ሕግ ማንኛውም ድንጋጌ አልተጠበቀም

**84. Defect Not to Affect Validity of Notices**

1. This Article shall apply when:

a) a notice of a tax assessment or any other document has been served on a taxpayer under a tax law;

b) the notice is, in substance and effect, in conformity with, or is consistent with the intent and meaning of, the tax law under which the notice has been made; and

c) the tax payer assessed, intended to be assessed, or affected by the notice, is designated in the notice according to common intent and understanding.

2. When this Article applies:

a) provided the notice of the tax assessment or other document has been properly served, the notice shall not be affected by reason that any of the provisions of the tax law under which the notice has been made have

በሚል ምክንያት ማስታወቂያውን ተቀባይነት ማሳጣት፤

ለ) የታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ማንኛውም ሌላ ሰነድ ፎርም አልተሟላም በሚል ውድቅ ማድረግ ወይም እንዳልተሰጠ መቁጠር ወይም እንዳልተሰጠ እንዲቆጠር ማድረግ፤ ወይም

ሐ) በታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ማንኛውም ሌላ ሰነድ ላይ በሚታይ ስህተት፣ ግድፈት ወይም ጉድለት ምክንያት ተቀባይነት ማሳጣት፤ አይቻልም።

3. ስህተቱ ወይም ልዩነቱ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የተሰጠውን ታክስ ከፋይ የሚያሳስት እስካልሆነ ድረስ የታክስ ስሌት ማስታወቂያው በሚከተሉት ምክንያቶች ዋጋ ሊያጣ አይችልም።

ሀ) በታክስ ስሌት ማስታወቂያው በተጠቀሰው የታክስ ከፋይ ስም፣ በተገለጸው የገቢ ወይም የገንዘብ መጠን ወይም እንዲከፈል በተጠየቀው የታክስ መጠን ስህተት ምክንያት፤

ለ) በተዘጋጀው የታክስ ስሌት እና ለታክስ ከፋዩ በተሰጠው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ መካከል በሚታይ ልዩነት ምክንያት።

## 85. ስህተቶችን ስለማረም

ቢሮው በታክስ ሕግ መሠረት ለታክስ ከፋዩ የሰጠው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ በታክስ ሕግ ወይም በጉዳዩ ኩነቶች ላይ የትርጉም ጥያቄ የማያስነሳ የጽሁፍ፣ የሂሳብ ስሌት ወይም ሌላ ማንኛውንም ስህተት የያዘ

not been complied with;

b) the notice of the tax assessment or other document shall not be quashed or deemed to be void or voidable for want of form; and

c) the notice of the tax assessment or other document shall not be affected by reason of any mistake, defect, or omission therein.

3. Unless otherwise, the mistake or difference misleads the taxpayer to whom the tax assessment notice is issued, the tax assessment notice shall not voided for the following reasons:

a) a mistake in the tax assessment as to the name of the taxpayer assessed, the description of any income or other amount, or the amount of tax charged; or

b) any variance between the tax assessment and the duly served notice of the tax assessment, provided the mistake or variance is not likely to deceive or mislead the taxpayer assessed.

## 85. Correction of Errors

When a notice of a tax assessment or other document served by the Bureau on a taxpayer under a tax law contains a clerical, arithmetic, or any other error that does not involve a dispute as to the interpretation of the law or facts of the case, the Bureau

በሚሆንበት ጊዜ፣ ቢሮው ስህተቱን ለማረም ሲባል የታክስ ስሌት ማስታወቂያውን ወይም ሌላውን ሰነድ የታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ሰነዱ ለታክስ ከፋዩ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 (አምስት) ዓመታት ውስጥ ማሻሻል ይችላል፡፡

**ክፍል አሥራ ሦስት**

**የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን**

**86. የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ስለማቋቋም**

1. የታክስ ይግባኝ በሚባልባቸው ውሳኔዎች ላይ ይግባኝ የሚሰማ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የኮሚሽኑ አደረጃጀት፣ አስተዳደር፣ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚሽኑ አባላት አሿሿም እና ኮሚሽኑን የሚመለከቱ ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮችን በተመለከተ የመስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይወሰናል፡፡

**87. የይግባኝ ማመልከቻ**

1. ይግባኝ በሚባልበት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የፈለገሰው የውሳኔው ማስታወቂያ በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ኮሚሽኑ የሚያዘጋጀውን ቅጽ በመጠቀም በውሳኔው ላይ የይግባኝ ማመልከቻ ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. የይግባኝ ማመልከቻው ይግባኝ የቀረበበትን ምክንያቶች የሚያመለክት መግለጫ መያዝ ይኖርበታል፡፡
3. ኮሚሽኑ የጽሑፍ ማመልከቻ ሲቀርብለት እና አጥጋቢ ምክንያት መኖሩን ሲያምን

may, for the purposes of correcting the mistake, amend the assessment or other document any time before the earlier of5 years from the date of service of the notice of the tax assessment or other document.

**PART THIRTEEN**

**TAX APPEAL COMMISSION**

**86. Establishment of Tax Appeal Commission**

1. The Tax Appeal Commission is hereby established to hear appeals against appealable decisions.
2. Subject to the provisions of this part, organization of the commission, administration, work procedure, appointment of the commission’s members, and other particulars shall be determined by the Regulation to be issued by Administrative Council .

**87. Notice of Appeal**

1. A person may appeal an appealable decision by filing a notice of appeal against the decision with the Commission in the approved form and within 30 days of service of notice of the decision.
2. A notice of appeal shall include a statement of reasons for the appeal.
3. The Commission may, on an application in writing and if good cause is shown, extend the time for lodging a notice of appeal under

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡

4. ኮሚሽኑ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘም የሚቀርብ ማመልከቻ የሚስተናገድበትን ስነ-ሥርዓት የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

88. ለኮሚሽኑ ሰነዶችን የማቅረብ ሥልጣን

1. ቢሮው የይግባኝ ማስታወቂያው በደረሰው በ30 (በሰላሳ) ቀናት ውስጥ ወይም ኮሚሽኑ በፈቀደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ፡-

ሀ) የይግባኝ ማመልከቻ የቀረበበትን ይግባኝ የሚባልበት ውሳኔ ግልባጭ፣

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) በተጠቀሰው ይግባኝ የሚባልበት ውሳኔ ላይ ያልተጠቀሰ ለውሳኔው ምክንያት የሆነ መግለጫ፣

ሐ) ውሳኔውን በይግባኝ ለማየት ለኮሚሽኑ አስፈላጊ የሆነ ማንኛውንም ሌላ ሰነድ ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት፡፡

2. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) መሠረት የቀረበው የውሳኔ ምክንያቶች መግለጫ አጥጋቢ ሆኖ ካላገኘው በጽሑፍ ማስታወቂያ ቢሮውን በማስታወቂያው በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የውሳኔውን ምክንያቶች የሚያብራራ ተጨማሪ መግለጫ እንዲያቀርብ ሊያዝ ይችላል፡፡

3. ኮሚሽኑ ለይግባኙ አወሳሰን ሌሎች ሰነዶችን ማየት ጠቃሚ ነው ብሎ ሲያምን ቢሮውን

sub article (1) of this Article.

4. The Commission may issue a Directive specifying the procedure for dealing with applications for an extension of time to file a notice of appeal.

**88. Authority to File Documents to the Commission**

1. The Bureau shall, within 30 days of being served with a copy of a notice of appeal within such further time as the Commission may allow:

a) the notice of the appealable decision to which the notice of appeal relates;

b) a statement setting out the reasons for the decision if these are not set out in the notice referred to in paragraph (a) of this sub-article;

c) any other document relevant to the Commission’s review of the decision.

2. If the Commission is not satisfied with a statement filed under sub-article (1) (b) of this Article, the Commission may, by written notice, require the Bureau to file, within the time specified in the notice, a further statement of reasons.

3. If the Commission is of the opinion that other documents may be relevant to an appeal, the

በጽሑፍ ማስታወቂያ በማስታወቂያው በተገለጸው ጊዜ ውስጥ እነዚህን ሰነዶች እንዲያቀርብ ሊያዝ ይችላል፡፡

4. ቢሮው በዚህ አንቀጽ መሠረት ለኮሚሽኑ ያቀረበውን የማናቸውንም መግለጫ እና ሰነድ ቅጅ ለይግባኝ ባዩ መስጠት አለበት፡፡

**89. የኮሚሽኑ ውሳኔ**

1. ኮሚሽኑ የቀረበለትን ይግባኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) በተደነገገው መሠረት በመስማት ውሳኔ ይሰጣል፡፡
2. ኮሚሽኑ የይግባኝ ማመልከቻ ከቀረበለት ቀን ቀጥለው ባሉት ፻፳ (አንድ መቶ ሃያ) ቀናት ውስጥ በቀረበው ይግባኝ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. ኮሚሽኑ የጉዳዩን ውስብስብነት ከግምት በማስገባት እና ለፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለተከራካሪ ወገኖች የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት የይግባኝ መወሰኛ ጊዜውን ከ60 (ስልሳ) ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝመው ይችላል፡፡
4. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ወይም (3) የተመለከተውን የጊዜ ገደብ ሳያከብር መቅረቱ ኮሚሽኑ የሰጠውን ውሳኔ ተቀባይነት ሊያሳጣው አይችልም፡፡
5. የቀረበው ይግባኝ የታክስ ስሌትን የሚመለከት ከሆነ ኮሚሽኑ፡-
   ሀ) በታክስ ስሌቱ የተወሰነውን የገንዘብ መጠን ሊያፀናው፣ ሊቀንሰው፣ ወይም ስሌቱን በሌላ አኳኋን ሊያሻሽለው፣ ወይም
   ለ) በሚሰጠው መመሪያ መሠረት እንደገና

Commission may, by written notice, require the Bureau to file the documents with the Commission within the time specified in the notice.

4. The Bureau shall give the person appealing a copy of any statement or document filed with the Commission under this Article.

**89. Decision of the Commission**

1. The Commission shall hear and determine an appeal and make a decision as set out in sub-article (5) or (6) of this Article.
2. The Commission shall decide an appeal within 120 days after the notice of appeal was filed.
3. The Commission may, by notice in writing to the parties to an appeal, extend the period for deciding the appeal for a period not exceeding 60 days having regard to the complexity of the issues in the case and the interests of justice.
4. A failure by the Commission to comply with sub-article (2) or (3) of this Article shall not affect the validity of a decision made by the Commission on the appeal.
5. If an appeal relates to a tax assessment, the Commission may make a decision to:
   a) affirm, or reduce, or otherwise amend the tax assessment; or
   b) remit the tax assessment to the Bureau for reconsideration in

እንዲመለከተው የታክስ ስሌቱን ለቢሮው ሊመልሰው ይችላል፡፡

6. ኮሚሽኑ በታክስ ስሌት ላይ የቀረበን ይግባኝ በመመርመር የታክስ ስሌቱ ሊጨመር ይገባል የሚል እምነት ሲኖረው፣ ኮሚሽኑ የታክስ ስሌቱን ማስታወቂያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5)(ለ) መሠረት ለቢሮው መልሶ ይልካል፡፡
7. የቀረበው ይግባኝ ይግባኝ የሚባልበትን ሌላ ውሳኔ የሚመለከት ከሆነ ኮሚሽኑ ውሳኔውን ሊያፀናው፣ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው ወይም ኮሚሽኑ በሚሰጠው መመሪያ እንደገና እንዲመለከተው ለቢሮው መልሶ ሊልከው ይችላል፡፡
8. ኮሚሽኑ የውሳኔውን ግልባጭ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 7 (ሰባት) ቀናት ውስጥ ለእያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ይሰጣል፡፡
9. ኮሚሽኑ የሚሰጠው ውሳኔ ውሳኔው የተመሠረተባቸውን ምክንያቶች፣ መሠረታዊ በሆኑ የፍሬነገር ጉዳዮች ምርመራ የተገኘውን ውጤት እና ለውሳኔው መሠረት የሆነውን ማስረጃ ወይም ለውሳኔው መሠረት የሆነውን ሌላ ነገር ማካተት አለበት፡፡
10. ኮሚሽኑ በቀረበለት ይግባኝ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ወይም ኮሚሽኑ በውሳኔ ማስታወቂያው ከተገለጸው ሌላ ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
11. ኮሚሽኑ ይግባኙን ላቀረበው ታክስ ከፋይ

accordance with the directions of the Commission.

6. If, in considering an appeal relating to a tax assessment, the Commission is of the view that the amount of tax assessed should be increased, the Commission shall remit the tax assessment to the Bureau in accordance with sub-article (5) (b) of this Article.
7. If an appeal relates to any other appealable decision, the Commission may make a decision to affirm, vary, set aside the decision, or remit the decision to the Bureau for reconsideration in accordance with the directions of the Commission.
8. The Commission shall serve a copy of the decision on an appeal on each party to the appeal within 7 days of the making of the decision.
9. The Commission's decision shall include the reasons for the decision and the findings on material questions of fact, and reference to the evidence or other material on which those findings were based.
10. The decision of the Commission on an appeal shall come into operation upon the giving of the decision or on such other date as may be specified by the Commission in the notice of the decision.
11. If the decision of the Commission is in

የወሰነለት እንደሆነ፣ ቢሮው ይህንን ውሳኔ ለማስፈጸም የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ መስጠትንም ጨምሮ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 8 መሠረት የውሳኔው ማስታወቂያ በደረሰው 30 (ሰላሳ) ቀናት ጊዜ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ሁሉ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አሥራ አራት

## ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

### 90. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1. ማንኛውም የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ግለሰብ፣ የሽርክና ማህበር ወይም ኩባንያ የታክስ ወኪል ፈቃድ እንዲሰጠው የፀደቀ ቅጽ በመጠቀም ለቢሮው ሊያመለክት ይችላል፡፡
2. ለዚህ ክፍል ዓላማ "የታክስ ወኪልነት አገልግሎት" ማለት፡-

ሀ) ታክስ ከፋዩን በመወከል የታክስ ማስታወቂያ ማዘጋጀት፤

ለ) ታክስ ከፋዩን በመወከል የቅሬታ ማስታወቂያ ማዘጋጀት፤

ሐ) የታክስ ሕጎችን አፈጻጸም በተመለከተ ለታክስ ከፋዮች ምክር መስጠት፤

መ) ከቢሮው ጋር ለሚኖራቸው ጉዳዮች ታክስ ከፋዮችን መወከል፤

ሠ) ታክስ ከፋዮችን በመወከል ከቢሮው ጋር ማንኛውንም ሌላ የሥራ ግንኙነት ማድረግ፤

favour of the taxpayer, the Bureau shall take such steps as are necessary to implement the decision, including serving notice of an amended assessment, within 30 days of receiving notice of the decision under sub-article (8) of this Article.

## PART FOURTEEN

## LICENSING OF TAX AGENTS

### 90. Application for Tax Agent's Licence

1. An individual, partnership, or company wishing to provide tax agent services may apply to the Bureau, in the approved form, for licensing as a tax agent.
2. In this Part, "tax agent services" means:

a) the preparation of tax declarations on behalf of taxpayers;

b) the preparation of notices of objection on behalf of taxpayers;

c) the provision of advice to taxpayers on the application of the tax laws;

d) representing taxpayers in their dealings with the Bureau; or

e) the transaction of any other business on behalf of taxpayers with the Bureau.

## 91. ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

1. ቢሮው በዚህ አዋጅ አንቀጽ አንቀጽ 90 መሠረት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተ ግለሰብ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ ሰው መሆኑን ሲያረጋግጥ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
2. ቢሮው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 90 መሠረት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተ የሽርክና ማህበር፡-

ሀ) በሽርክና ማህበሩ ውስጥ ያለ አባል ወይም ተቀጣሪ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ መሆኑን፣ እና

ለ) እያንዳንዱ የሽርክና ማህበር አባል መልካም ጠባይና ሥነ-ምግባር ያለው መሆኑ ሲያረጋግጥ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

3. ቢሮው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 90 መሠረት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተ ኩባንያ፡-

ሀ) የኩባንያው ተቀጣሪ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ መሆኑን ፣ እና

ለ) የኩባንያው እያንዳንዱ ዳይሬክተር፣ ሥራ አስኪያጅ እና ሌላ ስራ አስፈጻሚ ቢሮ መልካም ጠባይና ሥነ-ምግባር ያለው መሆኑን ሲያረጋግጥ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

## 91. Licensing of Tax Agents

1. The Bureau shall issue a tax agent's licence to an applicant under Article (90) of this Proclamation who is an individual when satisfied that the applicant is a fit and proper person to provide tax agent services.
2. The Bureau shall issue a tax agent's licence to an applicant under Article (90) of this Proclamation that is a partnership when satisfied that:
   a) a partner in, or employee of, the partnership is a fit and proper person to provide tax agent services; and
   b) every partner in the partnership is of good character and integrity.
3. The Bureau shall issue a tax agent's licence to an applicant under Article (90) of this Proclamation that is a company when satisfied that:
   a) an employee of the company is a fit and proper person to provide tax agent services; and
   b) every director, manager, and other executive Bureau of the company is of good character and integrity.

4. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣው ደንብ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት የሚያመለክት ሰው ብቁ እና ተስማሚ መሆኑን ለመወሰን የሚረዱ ጠቋሚ መሥፈርቶችን ይደነግጋል፡፡

5. ባሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 90 ለተጠቀሰው አመልካች ውሳኔውን በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

6. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ለሶስት ዓመታት የሚጸና ሲሆን፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 92 መሠረት ሊታደስ ይችላል፡፡

7. ቢሮው የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የሰጣቸውን ሰዎች ዝርዝር አመቺ ሆኖ ባገኘው መንገድ በየጊዜው ይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡

8. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የሙያ ፈቃድ በመሆኑ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው የንግድ ሥራ ፈቃድ ተሰጥቶት እንደሆነ ሥራውን የሚሠራው በታክስ ወኪልነት ብቻ ይሆናል፡፡

## 92. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ስለማደስ

1. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱ እንዲታደስለት ለቢሮው ማመልከት ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ፡-

ሀ) በጸደቀው ቅጽ መሠረት፣ እና

4. The Regulations will be issued by this proclamation may provide guidelines for determining when a person is fit and proper to provide tax agent services.

5. The Bureau shall provide an applicant under Article (95) of this Proclamation with notice, in writing, of the decision on the application.

6. A licence issued to a tax agent shall remain in force for three years from the date of issue and may be renewed under Article (92) of this Proclamation.

7. The Bureau may, from time to time, publish, in such manner as the Bureau determines, a list of persons licensed as tax agents.

8. A tax agent licence is a professional licence and a tax agent can carry on business as a tax agent only if the tax agent has been issued with a business licence.

## 92. Renewal of Tax Agent's Licence

1. A tax agent may apply to the Bureau for the renewal of the tax agent's licence.

2. An application under sub-article (1) of this Article shall be:

a) in the approved form; and

ለ) የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የአገልግሎት ጊዜ ባበቃ በ21 ቀናት ውስጥ ወይም ቢሮው በሚፈቅደው ከዚህ በዘገየ ጊዜ ውስጥ፣ መቅረብ ይኖርበታል።

3. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 91 የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ እስከቀጠለ ድረስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፈቃዱ እንዲታደስለት ያመለከተን ሰው የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ቢሮው ያድስለታል።

4. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ከታደሰበት ቀን ጀምሮ ለሶስት ዓመታት የሚፀና ሲሆን፣ በዚህ አንቀጽ መሠረት ለተጨማሪ ጊዜያት ሊታደስ ይችላል።

5. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ፈቃዱ እንዲታደስለት ለጠየቀ አመልካች በማመልከቻው ላይ ስለተሰጠው ውሳኔ በጸሁፍ ያሳውቃል።

**93. የታክስ ወኪልነት አገልግሎቶች ላይ ስለሚኖር ገደብ**

1 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ከተሰጠው ሰው በስተቀር ማንም ሰው በክፍያ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት መስጠት አይችልም።

2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ በአንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ (ሀ) ለታክስ ወኪልነት አገልግሎት በተሰጠው ትርጉም ከተካተቱት አገልግሎቶች ውጪ በመደበኛ የሙያ አገልግሎቱ ሂደት የታክስ ወኪልነት አገልግሎት በሚሰጥ የጥብቅና

b) filed with the Bureau within 21 days of the date of expiry of the tax agent’s licence or such later date as the Bureau may allow.

3. The Bureau shall renew the licence of a tax agent who has applied under sub-article 1 of this Article if the tax agent continues to satisfy the conditions for licensing in Article (91).

4. The renewal of a tax agent’s licence shall be valid for three years from the date of renewal and can be further renewed in accordance with this Article.

5. The Bureau shall provide an applicant under sub-article (1) of this Article with notice, in writing, of the decision on the application.

**93. Limitation on Providing Tax Agent Services**

1. Subject to sub-article (2) of this Article, no person, other than a licensed tax agent, shall, for a fee, provide tax agent services.

2. Sub-article (1)of this Article shall not apply to a person who is a licensed advocate acting in the ordinary course of his profession providing tax agent services other than services specified in paragraph (a) of sub article (2) of Article (90) of the definition of “tax agent services.”

ፈቃድ ያለው ሰው ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**94. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ስለመሰረዝ**

1. የታክስ ወኪልነት ሥራውን ለማቋረጥ የፈለገ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሥራውን ከማቋረጡ በፊት በ7 (ሰባት) ቀናት ውስጥ ይህንኑ ለቢሮው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ለዘለቄታው በታክስ ወኪልነት መሥራት ካልፈለገ የታክስ ወኪልነት ፈቃዱ እንዲሰረዝለት ለቢሮው በጽሑፍ ማመልከት ይችላል፡፡
3. ቢሮው ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ መሰረዝ አለበት፣

ሀ) የታክስ ወኪሉ ቢሮውን በሚያሳምን ሁኔታ ይህ ሊሆን የቻለው በእርሱ ፈቃድ ወይም ቸልተኝነት ምክንያት አለመሆኑን ካላረጋገጠ በስተቀር ፈቃድ በተሰጠው የታክስ ወኪል ተዘጋጅቶ የቀረበ የታክስ ማስታወቂያ በማንኛውም መሠረታዊ ጉዳይ ሀሰት ሆኖ ሲገኝ፤

ለ) የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱን ለማግኘት የሚጠየቁየሚያስፈልጉ ብቃት መስፈርችን ይዞ መቀጠል ሳይችል የቀረ እንደሆነ ወይም ቢሮው የታክስ ወኪሉ ሙያዊ የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈጽሟል ብሎ ሲያምን፤

ሐ) የታክስ ወኪሉ የታክስ ወኪልነት ሥራውን መሥራት ሲያቆም፤ እንዲሁም የታክስ ወኪሉ ኩባንያ ወይም የሽርክና ማህበር ሲሆን የኩባንያው ወይም

**94. Cancellation of Tax Agent's Licence**

1. A licensed tax agent shall notify the Bureau, in writing, within 7 days prior to ceasing to carry on business as a tax agent.
2. A licensed tax agent may apply to the Bureau, in writing, for cancellation of the tax agent's licence when the tax agent no longer wishes to be a licensed tax agent.
3. The Bureau shall cancel the licence of a tax agent when any of the following applies:

a) a tax declaration prepared and filed by the tax agent is false in any material particular, unless the tax agent establishes to the satisfaction of the Bureau that this was not due to any wilful or negligent conduct of the tax agent;

b) the tax agent ceases to satisfy the conditions for licensing as a tax agent, or the Bureau is satisfied that the tax agent has committed professional misconduct;

c) the tax agent has ceased to carry on business as a tax agent including, in the case of a company or partnership, when the company or partnership has ceased to exist;

የሽርክና ማህበሩህልውና ሲያከትም፤

መ) የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱ እንዲሠረዝለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ማመልከቻ ሲያቀርብ፤

ሠ) የታክስ ወኪሉ የፈቃድ አገልግሎት ጊዜ ሲያበቃ እና የታክስ ወኪሉ ፈቃዱ እንዲታደስለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 92 መሠረት ማመልከቻ ሳያቀርብ ሲቀር፤

4. ቢሮው የታክስ ወኪሉ ፈቃድ የተሠረዘ መሆኑን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ወኪሉ መስጠት አለበት፡፡

5. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ መሠረዝ የሚፀናው፡-

ሀ) የታክስ ወኪሉ የታክስ ወኪልነት ሥራውን መሥራት ካቆመበት ቀን፤ ወይም

ለ) ፈቃዱ የተሰረዘ መሆኑን የሚገልፀው ማስታወቂያ ለታክስ ወኪሉ ከተሰጠ ከ60 (ስልሳ) ቀናት በኋላ፤ ከሁለቱ ቀድሞ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

6. በሌላ ማንኛውም የታክስ ሕግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገ ቢኖርም፣ ቢሮው የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ሙያዊ የሥነ-ምግባር ጥሰት ፈፅሟል ብሎ ሲያምን ይህንን የሥነ-ምግባር ጥሰት፡-

ሀ) ለኢትዮጵያ የተመሠከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች ኢንስቲትዩት፣ለኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ወይም እንደአግባብነቱ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለተሰጠው ሰው የሂሣብ ባለሙያነት፣

d) the tax agent has applied for cancellation of the tax agent's licence under sub-article (2) of this Article;

e) the licence of the tax agent has expired and the agent has not filed an application for renewal of the licence under Article (92) of this Proclamation.

4. The Bureau shall serve notice, in writing, of a decision to cancel the licence of a tax agent.

5. The cancellation of the licence of a tax agent shall take effect on the earlier of:

a) the date the tax agent ceases to carry on business as a tax agent; or

b) 60 days after the tax agent has been served with notice of the cancellation.

6. Despite anything in any tax law, if the Bureau is of the opinion that a person who is a licensed tax agent has committed professional misconduct, the Bureau shall report the misconduct to:

a) the Institute of Certified Public Accountants, the Accounting and Auditing Board of Ethiopia, or other body having Bureau for the licensing of the person as an

የኦዲተርነት ወይም የሕግ ባለሙያነት ፈቃድ ለሰጠው ሌላ አካል፣እና

ለ) የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለተሰጠው ሰው የንግድ ፈቃድ ለመስጠት ኃላፊነት ላለው ቢሮ፣ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

## ክፍል አሥራ አምስት

## አስተዳደራዊ፣ የወንጀል ቅጣቶች እና ሽልማቶች

### ምዕራፍ አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**95. አስተዳደራዊ ቅጣቶችንና የወንጀል ኃላፊነቶችን የሚመለከቱ ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

1. አንድን ድርጊት መፈጸም ወይም አለመፈጸም አስተዳደራዊ ቅጣት እና የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትል በሚሆንበት ጊዜ ጥፋቱን የፈጸመው ሰው አስተዳደራዊ መቀጫ መቀጣቱ የወንጀል ተጠያቂነቱን አያስቀርም፡፡

2. ማንኛውም ታክስ ከፋይ አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት እና/ወይም የወንጀል ክስ የቀረበበት መሆኑ መክፈል የሚገባውን ታክስ የመክፈል ግዴታውን አያስቀርም፡፡

### ምዕራፍ ሁለት

### አስተዳደራዊ ቅጣቶች

**96. ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች**

1. በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ሌሎች አስተዳደራዊ ቅጣቶች እንደጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሰው በታክስ ከፋይነት መመዝገብ ሲገባው ያልተመዘገበ እንደሆነ መመዝገብ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ

accountant, auditor, or lawyer, as the case may be; and

b) the licensing Bureau responsible for issuing business licences.

## PART FIFTEEN

## ADMINISTRATIVE, CRIMINAL PENALTIES, AND REWARDS

### CHAPTER ONE

### GENERAL PROVISIONS

**95. General Provisions Relating to Administrative and Criminal Liabilities**

1. Here an act or omission entails both administrative and criminal liabilities at the same time, the person committing the offence shall not be relieved from criminal liability by the mere fact that he is held administratively liable.

2. A taxpayer who is assessed for an administrative penalty or prosecuted for a criminal offence shall not be relieved from liability to pay any tax due.

### CHAPTER TWO

### ADMINISTRATIVE PENALTIES

**96. Penalties Relating to Registration and cancellation**

1. Subject to the other administrative penalties imposed by this proclamation, a person who fails to apply for registration as required under this Proclamation shall be liable for a penalty of 25% of the tax payable by the person for the

ለምዝገባ እስካመለከተበት ወይም በቢሮው አነሳሽነት እስከ ተመዘገበበት ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ መክፈል ያለበትን ታክስ 25% (ሃያ አምስት በመቶ) መቀጫ ይከፍላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ታክስ ከፋይ የሚከፍለው ታክስ የሌለ እንደሆነ መመዝገብ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ተመዘገበበት ቀን ድረስ ላለው ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ክፊል ለሆነ ጊዜ ብር 1000 (አንድ ሺ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚጣለው መቀጫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ( 2) ከሚጣለው መቀጫ ያነሰ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ( 2) ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
4. በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ማንኛውም ሰው ያለ በቂ ምክንያት ምዝገባ እንዲሰረዝለት ያላመለከተ እንደሆነ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ማመልከት ከነበረበት ቀን ጀምሮ ምዝገባው እንዲሰረዝ እስካመለከትበት ቀን ወይም በቢሮው አነሳሽነት ምዝገባው እስከተሠረዘበት ቀን ድረስ ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ክፊል ለሆነ ጊዜ ብር 1000 (አንድ ሺህ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

## 97. ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ

period commencing on the date that the person was required to apply for registration and ending on the date that the person files the application for registration or the person is registered on the Bureau’s own motion.

2. Where there is no tax payable by the tax payer mentioned in sub article (1) of this article, the tax payer shall pay a penalty of Birr 1000 for each month or part thereof from the day on which he should have been registered to the day of his actual registration.
3. Where the penalty to be imposed pursuant to sub article 1 of this article is less than the penalty to be imposed pursuant to sub article 2 of this article, the penalty in sub article 2 of this article shall apply.
4. A person who, without reasonable excuse, fails to apply for cancellation of registration as required under this Proclamation shall be liable for a penalty of birr 1,000 for each month or part thereof for the period commencing on the date that the person was required to apply for cancellation of registration and ending on the date that the person files the application for cancellation or the person’s registration is cancelled on the Bureau’s own motion.

## 97. Penalty for Failing to Maintain Documents

1. Subject to sub-article (2) of this Article, a

ሆኖ፣ በታክስ ሕግ መሠረት መያዝ የሚጠበቅበትን ማንኛውንም ሰነድ ያልያዘ ታክስ ከፋይ በታክስ ሕጉ መሠረት ሰነዱ መያዝ በነበረበት የታክስ ዘመን መክፈል ያለበትን ታክስ ፳% (ሃያ በመቶ) ቅጣት ይከፍላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሰነድ መያዝ ሲኖርበት ያልያዘ ታክስ ከፋይ ሰነዱን መያዝ በነበረበት የታክስ ዘመን መክፈል የሚኖርበት ታክስ የሌለ እንደሆነ፡-

ሀ) ለገቢ ግብር ሲሆን ታክስ ከፋዩ የሂሳብ ሰነድ ላልያዘበት ለእያንዳንዱ የታክስ ዘመን ብር 20,00(ሃያ ሺህ ብር) ፣ወይም

ለ) ለሌላ ማንኛውም ታክስ ሲሆን ታክስ ከፋዩ የሂሳብ ሰነድ ላልያዘበት የታክስ ዘመን ብር 2,000 (ሁለት ሺህ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚጣለው መቀጫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ( 2) ከሚጣለው መቀጫ ያነሰ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ( 2) ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1)፣ ( 2) እና ( 3) እንደተጠበቁ ሆነው፣ማንኛውም ታክስ ከፋይ ከሁለት ዓመት በላይ የሂሣብ ሰነድ ካልያዘ ለታክስ ከፋዩ የንግድ ፈቃድየሰጠው አካል ከቢሮው በሚቀርብለት ማስታወቂያ መሠረት የታክስ ከፋዩን የንግድ ፈቃድ ይሰርዛል፡፡

5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17( 2) ለተወሰነው ጊዜ ድረስ ሰነዶችን ይዞ ሳያቆይ የቀረ የደረጃ

taxpayer who fails to maintain any document as required under a tax law shall be liable for a penalty of 20% of the tax payable by the taxpayer under the tax law for the tax period to which the failure relates.

2. If no tax is payable by the taxpayer for the tax period to which the failure referred to in sub-article (1) of this Article relates, the penalty shall be:

a) birr 20,000 for each tax year that the taxpayer fails to maintain documents for the purposes of the income tax; or

b) birr 2,000 for each tax period that the taxpayer fails to maintain documents for the purposes of any other tax.

3. Where the penalty to be imposed pursuant to sub article 1 of this article is less than the penalty to be imposed pursuant to sub article 2 of this article, the penalty in sub article 2 of this article shall apply.

4. Without prejudice to sub-articles (1), (2) and (3) of this Article, the licensing Bureau responsible for issuing business licences, shall on notification by the Bureau, cancel the business licence of a taxpayer who fails to maintain documents for more than 2 years.

5. A Category ‘A’ taxpayer who fails to retain documents for the period specified in Article

‘ሀ’ታክስ ከፋይ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ.ህ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

6. በክልሉ ገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 30 3(4) ለተወሰነው ጊዜ ድረስ ሰነዶችን ይዞ ሳያቆይ የቀረ የደረጃ ‘ለ’ ታክስ ከፋይ ብር ብር 20,000 (ሃያ ሺ.ህ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

98. ከታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር የተገናኘ ቅጣት

1. የታክስ ሕግ በሚደነግገው መሠረት የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን በታክስ ደረሰኝ፣ በታክስ ደቢት ወይም ክሬዲት ማስታወሻ፣ በታክስ ማስታወቂያ፣ ወይም በሌላ በማንኛውም ሰነድ ላይ ሳይገልጽ የቀረ ታክስ ከፋይ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ባልተገለጸበት በእያንዳንዱ ሰነድብር 3,000 (ሶስት ሺ.ህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

2. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 14(6) ተፈጻሚ ከሚሆንበት ሁኔታ በስተቀር፣ ማንኛውም ታክስ ከፋይ፡-

ሀ) የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) የሌላ ሰው ታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የተጠቀመ እንደሆነ፤ ብር 10,000 (አስር ሺ.ህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) (ሀ) ወይም (ለ) በተጠቀሱት ድርጊቶች ምክንያት ታክስ ከፋዩ ወይም ሌላ ሰው ያገኘው የገንዘብ ጥቅም ከብር 10,000 (አስር ሺ.ህ ብር) የሚበልጥ ከሆነ የሚከፍለው የገንዘብ መቀጫ መጠን ካገኘው ጥቅም ጋር እኩል ይሆናል፡፡

17(2) shall be liable for a penalty of birr 50,000.

6. A Category ‘B’ taxpayer who fails to retain documents for the period specified in Article 30 3(4) of the Income Tax Proclamation of the Region shall be liable for a penalty of birr 20,000.

**98. Penalty in Relation to TINs**

1. A taxpayer who fails to state their TIN on a tax invoice, tax debit or credit note, tax declaration, or any other document as required under a tax law shall be liable for a penalty of birr 3,000 for each failure.

2. Except when Article 14(6) of this Proclamation applies, a taxpayer shall be liable for a penalty of birr 10,000 if the taxpayer:

   a) provides their TIN for use by another person; or

   b) uses the TIN of another person.

3. If the pecuniary advantage obtained by the taxpayer or another person as result of conduct referred to in sub-article (2) (a) or (b) of this Article exceeds birr 10,000, the penalty shall be equal to the pecuniary advantage obtained by the taxpayer.

**99. የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ ስለሚያስከትለው ቅጣት**

1. በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የታክስ ማስታወቂያ ግዴታውን ያልተወጣ ታክስ ከፋይ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ የታክስ ጊዜ ወይም ከፊል ለሆነው ጊዜ ያልተከፈለውን ታክስ 5% (አምስት በመቶ) 25% (ሃያ አምስት በመቶ) እስኪሞላ ድረስ መቀጫ ይከፍላል፡፡
2. ለመጀመሪያው የሂሣብ ጊዜ ወይም ከፊል ለሆነው ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሠረት የሚከፍለው መቀጫ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) አይበልጥም፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ያልተከፈለ ታክስ ነው የሚባለው በታክስ ማስታወቂያ ላይ መታየት በነበረበት እና ታክሱ መከፈል ባለበት ቀን በተከፈለው ታክስ መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡
4. በማናቸውም ሁኔታ የሚጣለው መቀጫ ቀጥለው ከተመለከቱት ከዝቅተኛው ያነሰ አይሆንም፡-
   ሀ) ብር 10,000 (አሥር ሺህ ብር)፣
   ለ) በታክስ ማስታወቂያ ላይ መመልከት ከነበረበት የታክስ መጠን 100% (መቶ በመቶ)
5. በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ በታክስ ጊዜው ሊከፍል የሚገባው ታክስ የሌለ እንደሆነ፣ የታክስ ማስታወቂያ ሳያቀርብ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ የታክስ ጊዜ ብር

**99. Late Filing Penalty**

1. A person who fails to file a tax declaration by the due date shall be liable for a late filing penalty of 5 % of the unpaid tax for each tax period or part thereof to which the failure relates, provided that the penalty to be so imposed shall not exceed 25% of the unpaid tax.
2. The penalty to which a tax payer is liable for non-filing of tax declaration for the first tax period or part thereof under sub article 1 of this article shall not exceed 50,000 birr.
3. For the purpose of this article, unpaid tax means the difference between the amount of tax that should have been entered in the tax declaration and the tax paid on the due date.
4. The penalty to be imposed shall under no circumstance be less than the lowest of the following:
   a) birr 10,000
   b) 100% of the amount tax that should have been entered in the tax declaration.
5. Notwithstanding the provisions of this article, where the taxpayer has no tax to pay for a tax period, he shall be liable for a penalty of birr 10,000 for each tax period

10,000(አሥር ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

to which the non-filing of tax declaration relates.

**100. ታክስን ዘግይቶ መክፈል የሚያስከትለው ቅጣት**

1. ማንኛውም ታክስ ከፋይ በታክስ መክፈያ ጊዜው ውስጥ ታክስ ሳይከፍል ከቀረ ለዘገየበት ጊዜ፡-
   ሀ) የታክስ መክፍያ ጊዜው ከላፈ ከአንድ ወር በኂላ ባልተከፈለው ታክስ ላይ 5% (አምስት በመቶ) ፤እና
   ለ) ከዚያ በኂላ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ሙሉ ወይም ከፊል ወር ባልተከፈለው ታክስ ላይተጨማሪ 2% (ሁለት በመቶ) መቀጫ ይከፈላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚጣለው የመቀጫመጠን መቀጫው ከዋናው የታክስ ዕዳ መብለጥ የለበትም፡፡
3. መክፈል በማይገባው ታክስ ላይ ሳይከፈል በዘገየበት የተጣለ መቀጫ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 50 (4) መሠረት ለታክስ ከፋዩ ይመለሳል፡፡
4. ይህ አንቀጽ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 101 በሚመለከተው ያልተከፈለ ታክስ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**100. Late Payment Penalty**

1. A taxpayer who fails to pay tax by the due date shall be liable for the following late payment penalties:
   a) 5% of the unpaid tax that remains unpaid at the expiration of 1 month or part thereof after the due date; and
   b) an additional 2% of the amount of the unpaid tax for each month or part of a month thereafter to the extent that the tax remains unpaid.
2. The amount of penalty assessed under this Article shall not exceed the amount of the tax liability to which it relates.
3. Late payment penalty paid by a taxpayer shall be refunded to the taxpayer in accordance with Article 50 (4) of this Proclamation to the extent that the tax to which the penalty relates is found not to have been payable.
4. This Article shall not apply when Article 101 of this Proclamation applies in relation to the unpaid tax.

**101. ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ከሚከፈል ታክስ ጋር በተገናኘ የሚጣል ቅጣት**

1. በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ታክስ ቀንሶ ለቢሮው ማስተላለፍ ያለበት ማንኛውም ሰው ሳይቀንስ የቀረው ወይም ቀንሶ ለቢሮው

**101. Withholding Tax Penalties**

1. A person who fails to withhold tax or, having withheld tax fails to pay the tax to the Bureau, as required under the Income Tax Proclamation shall be liable for a

ያላስተላለፈውን ታክስ 10% (አሥር በመቶ) መቀጫ ይከፍላል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ለድርጅት ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ፣ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ መሠረት ከሚጣለው ቅጣት በተጨማሪ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ፣ ዋና የሂሳብ ሹም ወይም ታክስ ተቀንሶ መያዝ እናዳለበትና የተያዘውም ታክስ መከፈል እንዳለበት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ማንኛውም ሌላ የድርጅቱ ሠራተኛ እያንዳንዳቸው ብር 2,000 (ሁለት ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላሉ፡፡

3. የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 88 ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ አቅራቢውና ገዥው እያንዳንዳቸው ብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላሉ፡፡

4. በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 88 መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈልን ታክስ ለማስቀረት በማሰብ በዚህ አንቀጽ መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ታክስ ቀንሶ የመክፈል ግዴታ ላለበት ሰው ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ለማቅረብ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው ብር 10,000 (አሥር ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

### 102. የታክስ ደረሰኝ አለመስጠት

ደረሰኝ መስጠት ሲገባው ያልሰጠ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ለገዥ ባልሰጠው በእያንዳንዱ ደረሰኝ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) መቀጫ ይቀጣል፡፡

### 103. ታክስን አሳንሶ ማሳወቅ የሚያስከትለው ቅጣት

1. በታክስ ማስታወቂያ የተገለጸው የታክስ መጠን

penalty of 10% of the tax to be withheld or actually withheld but not transferred to the Bureau.

2. When sub-article (1) of this Article applies to a body and in addition to the penalty imposed under that sub-article, the manager of the body, chief accountant, or any other officer of the body responsible for ensuring the withholding and payment of withholding tax shall be liable for a penalty of birr 2,000 each.

3. When Article 88 of the Income Tax Proclamation applies, both the supplier and purchaser shall be liable for a penalty of birr 20,000 each.

4. A person, who, with the intention of avoiding withholding tax under Article 88 of the Income Tax Proclamation, refused to supply goods or services to a person who is obliged to withhold tax under that Article shall be liable for a penalty of birr 10,000.

### 102. Failure to Issue Tax Invoice

Where a taxpayer being required to issue tax invoice fails to do so, shall be liable for a penalty of birr 50,000 for each transaction to which the failure to issue tax invoice relates.

### 103. Tax Understatement Penalty

1. A taxpayer who has declared tax liability is

ታክስ ከፋዩ ሊከፍል ከሚገባው ትክክለኛ የታክስ መጠንያነሰ እንደሆነ (ልዩነቱ "የታክስ ጉድለት "ተብሎ የሚገለጽ) የታክስ ጉድለቱን መጠን 10% (አሥር በመቶ) መቀጫ ይከፍላል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በታክስ ከፋዩ ላይ ለሁለተኛ ጊዜ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የቅጣቱ መጠን ወደ 30% (ሰላሳ በመቶ) ከፍ ይላል።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በታክስ ከፋዩ ላይ ለሶስተኛ ጊዜ እና ከዚያ በላይ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የመቀጫው መጠን ወደ 40% (አርባ በመቶ) ከፍ ይላል።
4. የታክስ ጉድለቱ የተፈጠረው ታክስ ከፋዩ የራሱን ታክስ አስልቶ የታክስ ማስታወቂያ ከማቅረቡ በፊት ቢሮው ማብራሪያ ባልሰጠበት አከራካሪ በሆነ የታክስ ሕግ ድንጋጌ ላይ በያዘው ምክንያታዊ አቋም ላይ የተመሠረተ ሆኖ ከተገኘ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚጣል መቀጫተፈጻሚ አይሆንም።

**104. ታክስን በመሸሽ የሚጣል መቀጫ**

ቢሮው የታክስ ከፋይን የታክስ ስሌት ሲሠራ ከታክስ መሸሽን የሚከላከል ድንጋጌ ተፈጻሚ ካደረገ ታክስ ከፋዩ ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚ ባይደረግ ኖሮ ከታክስ በመሸሽ ሊያስቀር ይችል የነበረውን የታክስ መጠን እጥፍ መቀጫ ይከፍላል።

**105. የኤሌክትሮኒክስ የታክስ ሥርዓትን አለመከተል የሚያስከትለው መቀጫ**

1. በታክስ ሕግ መሠረት ቢሮው የታክስ

less than the taxpayer's correct tax liability (the difference being referred to as the "tax shortfall") shall be liable for a penalty of 10% of the tax shortfall.

2. The penalty under sub-article (1) of this Article shall be increased to 30% for the second application of the Article to the taxpayer.
3. The penalty under sub-article (1) of this Article shall be increased to 40% for the third or subsequent application of the Article to the taxpayer.
4. No penalty shall be imposed under this Article if the tax shortfall arose as a result of a self-assessment taxpayer taking a reasonably arguable position on the application of a tax law on which the Bureau has not issued ruling prior to the taxpayer filing their self-assessment declaration.

**104. Tax Avoidance Penalty**

If the Bureau has applied tax avoidance provision in assessing a taxpayer, the taxpayer shall be liable for a tax avoidance penalty equal to double the amount of the tax that would have been avoided but for the application of the anti-tax avoidance provision.

**105. Penalty for Failing to Comply with Electronic Tax System**

1. When a taxpayer required by the Bureau

ማስታወቂያውን ወይም የታክስ ክፍያውን በኤሌክትሮኒክስ የታክስ ሥርዓት መሠረት እንዲፈጽም የጠየቀው ታክስ ከፋይ በዚሁ ሥርዓት መሠረት ሳይፈጽም ቢቀር ቢሮው ታክስ ከፋዩ ሥርዓቱን ያልከተተለበትን ምክንያት እንዲገለጽ በጽሑፍ መጠየቅ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ የታክስ ማስታወቂያውን ወይም የታክስ ክፍያውን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ላለ መፈጸሙ ማስታወቂያው ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት 14 ቀናት ውስጥ ቢሮውን የሚያሳምን በቂ ምክንያት ማቅረብ ካልቻለ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

106. በታክስ ወኪል ላይ ስለሚጣል መቀጫ

የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው፡-

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 መሠረት ለደንበኛው የምስክር ወረቀት ወይም መግለጫ ካልሰጠ፣ ወይም
2) ለደንበኞች የተሰጡ የምስክር ወረቀቶችንና መግለጫዎችን በአንቀጽ 22 (4) ለተወሰነው ጊዜ ካልያዘ፣ ወይም
3) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 94 (1) መሠረት የታክስ ወኪልነት ሥራውን ማቆሙን ለቢሮው ካላሳወቀ፤ ብር 10,000 (አስር ሺህ) ቅጣት ከፍላል፡፡

107. ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ጋር ተያይዞ የሚጣል መቀጫ

1. ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው፡-

under a tax law to file a tax declaration or pay tax electronically fails to do so, the Bureau shall serve the taxpayer with notice in writing seeking reasons for the failure.

2. A taxpayer who fails to provide adequate reasons to the satisfaction of the Bureau for the failure to file a tax declaration or pay tax electronically within 14 days of the date of service of the notice under sub-article (1) of this Article shall be liable for a penalty equal to birr 50,000.

**106. Tax Agent Penalties**

A licensed tax agent shall be:

1) to provide a certificate or statement to their client as required under Article 22 of this Proclamation;
2) to keep certificates and statements provided to clients for the period specified in Article 22 (4) of this Proclamation;
3) if not notify as the tax agent fails to the Bureau as required under Article 94 (1) of this Proclamation, it shall be liable for a penalty of birr 10,000.

**107. Penalties Relating to Sales Register Machines**

1. Any person who has the obligation to use sales register machine shall be liable for a penalty of :

| | |
|---|---|
| ሀ) ዕውቅና ያልተሰጠው ወይም በቢሮው ዘንድ ያልተመዘገበ መሣሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጥ ሶፍትዌር ሲጠቀም ከተደረሰበት ለተጠቀመበት ለእያንዳንዱ መሣሪያ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡ | a) Birr 50,000 if found using sales register machine or point of sales machine software not accredited or registered by the Bureau. |
| ለ) መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ወይም በሌላ በቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ በሌላ ማናቸውም ዓይነት ደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡ | b) Birr 50,000 for carrying out transactions without receipt or invoice or for using any other receipt not generated by a sales register machine except at the time the machine is under repair or for any other justifiable reason. |
| ሐ) በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም የፊስካል ማስታወሻ እንዲቀየር ያደረገ ወይም ጉዳት ለማድረስ ወይም ማስታወሻውን ለመቀየር ሙከራ ያደረገ ከሆነ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡ | c) Birr 100,000 if caused damage to or change of fiscal memory or attempts to cause damage to or change of fiscal memory. |
| መ) የታክስ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ሥርዓት ኦዲት እንዳያደርግ መሰናክል የፈጠረ ወይም በመሣሪያው ላይ በዓመት አንድ ጊዜ በአገልግሎት ማዕከል የቴክኒክ ምርመራ ያላደረገ ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡ | d) Birr 25,000 for obstructing inspection of the audit system of a sales register machine by officer or for failure to have annual machine inspections performed by a service center; |
| ሠ) በንግድ ሥራው ለሚጠቀምበት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከአገልግሎት ማዕከል ጋር ውል ካልፈጸመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን ከተርሚናል ጋር ሳያያይዝ ከተጠቀመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው የምርመራ | e) Birr 25,000 for not having a valid service contract with an authorized service centre for a sales register machine in use, or for using the sales register machine without connecting to the terminal, or for not keeping the |

መዝገብ ከመሣሪያው ጎን እንዲቀመጥ ካላደረገ ወይም በሽያጭ መመዝገቢያ የተመዘገቡ ዕቃዎች ተመላሽ መደረጋቸው ወይም ደንበኛው የተመላሽ ጥያቄ ማቅረቡ በተመላሽ መዝገብ ላይ በትክክል መመዝገቡ ሳይረጋገጥ የተመላሽ ደረሰኝ ከሰጠ ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

ረ) የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው በስርቆት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ አገልግሎት መስጠት ሲያቋርጥ በሦስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ብልሽት ባጋጠመው በሁለት ሰዓት ውስጥ ለአገልግሎት ማዕከሉ እና ለቢሮው ካላሳወቀ ብር 10,000 (አሥር ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

ሰ) የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚቀመጥበትን የንግድ ቦታ ትክክለኛ አድራሻ ለቢሮው ያላስታወቀ እንደሆነ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

ሸ) የአድራሻ ወይም የስም ለውጥ ሲያደርግ ወይም የንግድ ሥራውን የሚያቋርጥ ሲሆን ከሦስት ቀናት አስቀድሞ ለአገልግሎት ማዕከሉ እና ለቢሮው ያላሳወቀ እንደሆነ ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

ቀ) የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ጥቅም

inspection booklet besides the sales register machine, or for issuing refund receipts without properly recording the return of goods or customers' request for refund in the refund book.

f) Birr 10,000 for failure to inform the Bureau and the machine service center within three days of the termination of a sales register machine use due to theft or irreparable damage, or within two hours for failure to report machine malfunction due to any other causes.

g) Birr 50,000 for failure to notify to the Bureau the correct place of business the sales register machine is in use;

h) Birr 25,000 for failure to notify the Bureau change of name or address or for failure to notify the Bureau and Service Center three days in advance in cases of termination of business;

i) The place where the machine is

ላይ በሚውልበት የንግድ ሥራ ቦታው፡-

1. የተጠቃሚውን ስም፣ የንግድ ስም፣ የንግዱ ሥራ የሚካሄድበትን አድራሻ፣ የታክስ ከፋዩን መለያ ቁጥር፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን የዕውቅና እና መጠቀሚያ ፈቃድ ቁጥር፤
2. "የሽያጭ ሠራተኞች መሣሪያው የተበላሸ ከሆነ በቢሮው ፈቃድ የታተመ ተከታታይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ ለደንበኞች የመስጠት ግዴታ አለባቸው" የሚል ማስታወቂያ፤ እና
3. "ደረሰኝ የማይሰጥ ከሆነ አይክፈሉ" የሚል ጽሑፍ ያለበት ማስታወቂያ፣ በግልጽና በሚታይ ቦታ ለጥፎ ካልተገኘ ብር 10,000 (አሥር ሺህ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

በ) ሥራ ላይ የዋለውን የሽያጭ ነቁጣ ሶፍትዌር የቢሮው ዕውቅና ባልተሰጠው ሰው እንዲቀየር ወይም እንዲሻሻል ካደረገ ብር 30,000 (ሰላሣ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

2. ማንኛውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት ዕውቅና እና ፈቃድ የተሰጠው ሰው፡-

ሀ) የንግድ ሥራውን የአድራሻ ለውጥ ለቢሮው ካላሳወቀ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

ለ) በቢሮው ዕውቅና ያልተሰጠውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ለገበያ ካዋለ ብር

installed:-

1. name of the machine user, trade name, location of trade, taxpayers' identification number, accreditation and permit numbers for the sales register machine;
2. text stating that "in case of machine failure sales personnel must issue manual receipts authorized by the Bureau"; and
3. A fine of Birr 10,000 (ten thousand Birr) shall be imposed if a notice with the inscription "Do not pay if receipt is not issued," if it is not found to be posted in a clear and conspicuous place.

j) A fine of Birr 30,000 shall be levied if the sales software used in operation causes it to be altered or modified by a person who is not accredited by the Bureau.

2. Any person who is accredited and permitted for the supply of sales register machine or software shall be liable for a penalty of:

a) Birr 100,000 for failure to notify change of business address to the Bureau;

b) Birr 500,000 for selling a sales register machine not accredited by the Bureau;

500,000 (አምስት መቶ ሺህ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡

ሐ) ለእያንዳንዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ምዝገባ ከቢሮው የመሣሪያ መለያ ቁጥር ካልወሰደ ወይም የወሰደውን የመሣሪያ መለያ ቁጥር ለእይታ በሚያመች ቦታ በመሣሪያው ላይ ካልለጠፈ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

c) Birr 50,000 for failure to get a machine registration code for each sales register machine from the Bureau or for not affixing the machine code stickers on a visible part of the machine;

መ) በሥራ ላይ ባሉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ላይ የሚያደርገውን ማናቸውንም ለውጥ ለቢሮው በቅድሚያ ካላሳወቀ ወይም ስለመሣሪያው የአጠቃቀም መመሪያ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካስገባ ወይም ትክክለኛውን መረጃ ከቀነሰ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

d) Birr 100,000 for failure to notify to the Bureau in advance any change made to the sales register machine in use or for inserting or adding incorrect information or for omitting the correct information from the manual that guides the use of sales register machine;

ሠ) የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በመሠረቃቸው ወይም ሊጠገኑ በማይቻልበት ሁኔታ በአደጋ ምክንያት ብልሽት የደረሰባቸው መሆኑን አስታውቀው እንዲተኩላቸው ለሚጠይቁ አገልግሎት ማዕከላት በሦስት ቀናት ውስጥ ለማቅረብ አለመቻሉን ለቢሮው አስቀድሞ ካላሳወቀ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

e) Birr 50,000 for failure to notify the Bureau in advance or for not being able to replace, within three days of the request made by a service center, sales register machine lost due to theft or sustained irreparable damage;

ረ) ውል ስለተዋዋላቸው አገልግሎት ማዕከላት መረጃ ካልያዘ ወይም ውላቸውን ስላቋረጡ ወይም አዲስ ስለተዋዋላቸው የአገልግሎት ማዕከላት

f) Birr 50,000 for failure to keep information about service centers with which it has signed agreements or for failure to notify the Bureau about contracts terminated or newly entered agreements with service

ለቢሮው ካላስታወቀ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

3. ማንኛውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል፦

ሀ) የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የፊስካል ማስታወሻ በተተካ በሁለት ቀናት ውስጥ ለቢሮው ካላስታወቀ ብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

ለ) ውል የገባባቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በዓመት አንድ ጊዜ የቴክኒክ ምርመራ ካላደረገ ብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

ሐ) አቅራቢው ዕውቅና ሳይሰጠው እና በቢሮው ሳይመዘገብ በሥራ ላሠማራው ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡

**108. ልዩ ልዩ ቅጣቶች**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 መሠረት ማንኛውንም ለውጥ ያላሳወቀ ታክስ ከፋይ ብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 82 መሠረት የመመስረቻ ጽሑፉን፣ መተዳደሪያ ደንቡን፣ የሽርክና ስምምነቱን ወይም ሌላ የመመስረቻ ወይም የምዝገባ ሰነድ ወይም በእነዚህ ሰነዶች ላይ የተደረገውን ማንኛውም ማሻሻያ ሳያቀርብ የቀረ ድርጅት ሰነዱ ሳይቀርብ ለቀረበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ ብር 10,000 (አሥር ሺህ ብር) መቀጫ

centers.

3. Any sales register machine service centre shall be liable for a penalty of:
   a) Birr 20,000 for failure to report to the Bureau within two days of change of the fiscal memory of a sales register machine;
   b) Birr 20,000 for failure to perform annual technical inspections on sales register machines that are under contract;
   c) Birr 50,000 for deploying every person not certified by the supplier and not registered by the Bureau.

**108. Miscellaneous Penalties**

1. A taxpayer who fails to notify any change as required under Article 10 of this Proclamation shall be liable for a penalty of birr 20,000.
2. A body that fails to file a copy of its memorandum of association, articles of association, statute, partnership agreement, or other document of formation or registration, or any amendment to such document, as required under Article 82 of this Proclamation shall be liable for a penalty of birr 10,000 for each month or part thereof that the document remains unfiled.

ይከፍላል፡፡

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 83 በተደነገገው መሠረት የኦዲት ሪፖርቱን ለቢሮው ያላቀረበ ማንኛውም ኦዲተር ሰነዱ ሳይቀርብ ለቀረበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ክፊል ለሆነው ጊዜ ብር 10,000 (አሥር ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የሚጣለው ቅጣት የኦዲተሩን ፈቃድ አስመልክቶ በኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ከሚወስደው እርምጃ በተጨማሪ ይሆናል፡፡
5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 84 መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ካልሆነ ሰው ጋር የተደረገን ውል ለቢሮው ያላሳወቀ ሰው ይህንኑ ሳያሳውቅ ለቀረበት ለእያንዳንዱ ቀን ብር 1,000(አንድ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡
6. በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 79 መሠረት ግንኙነት ካለው ሰዎች ጋር የሚያደርጋቸውን ግብይቶች ዝርዝር ጉዳይ ለቢሮው ያልገለጸ ሰው ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል፡፡
7. ማናቸውም መረጃ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ባለስልጣኑ የሚጠይቀውን መረጃ ለቢሮው ያልሰጠ እንደሆነ እንደሁኔታው መረጃውን ያልሰጠው ሰው ወይም መረጃ የተጠየቀው መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ብር 5,000 (አምስት ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላሉ፡፡

3. A public auditor who fails to file an audit report with the Bureau as required under Article 63 of this Proclamation shall be liable for a penalty of birr 10,000 for each month or part of a month that the document remains unfiled.
4. The penalty provided for under sub-article (3) of this Article shall be in addition to any action taken by the Accounting and Auditing Board of Ethiopia in relation to the public auditor's licence.
5. A person who fails to notify the Bureau as required under Article 64 of this Proclamation shall be liable for a penalty of birr 1,000 for each day of default.
6. A taxpayer who fails to provide details of transactions with related persons as required under Article 79 of the Income Tax Proclamation shall be liable for a penalty of birr 100,000.
7. Any person having the obligation to supply information fails to give any information requested by the Bureau, that person or the head of the organization ,as appropriate, from which the information is sought shall be liable for a penalty of birr 5000.

**109. ስለአስተዳደራዊ መቀጫ አወሳሰን**

1. ቢሮው አስተዳዳራዊ መቀጫ ለወሰነበት ሰው የመቀጫ ውሳኔ ማስታወቂያ መስጠት አለበት፡፡
2. አንድ ድርጊት ወይም አለማድረግ የሚያስከትለው አስተዳደራዊ መቀጫ በአንድ ታክስ ብቻ ያልተወሰነ ሲሆን እንያንዳንዱ ቅጣት ለየብቻው ከተወሰነ በኋላ ሁሉም መቀጫዎች ተጠቃለው ይጣላሉ፡፡
3. አስተዳደራዊ መቀጫ የተወሰነበት ሰው መቀጫው እንዲነሳለት ለቢሮው በጽሑፍ ማመልከት የሚችል ሲሆን መቀጫው እንዲነሳለት የጠየቀበትን ምክንያት በማመልከቻው መግለጽ አለበት፡፡
4. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ( 3) መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት ወይም በራሱ አነሳሽነት በአንድ ሰው ላይ የተጣለን መቀጫ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በሙሉ ወይም በከፊል ሊያነሳ ይችላል፡፡
5. ቢሮው እንዲነሳ ውሳኔ የሰጠበትን የእያንዳንዱን አስተዳደራዊ መቀጫ መዝገብ መያዝ እና በየሩብ ዓመቱ ለፋይናንስ ቢሮ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የታክስ ወንጀሎች

**110. የታክስ ወንጀል ጉዳዮች የሚታዩበት ሥነ-ሥርዓት**

በታክስ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች የኢትዮጵያን የወንጀል ህግ በመተላለፍ የሚፈጸሙ በመሆናቸው ክሱ የሚመሠረተው፣ የሚታየው

**109. Assessment of Administrative Penalties**

1. The Bureau shall serve a person liable for an administrative penalty with notice of the penalty assessed.
2. When the same act or omission may involve administrative penalties in relation to more than one tax, the penalties shall be aggregated after being assessed separately for each tax.
3. A person liable for an administrative penalty may apply in writing to the Bureau, for waiver of the penalty payable and such application shall include the reasons for the requested remission.
4. The Bureau may, upon application under sub-article (3) of this Article or on its own motion waive, in whole or in part, an administrative penalty imposed on a person in accordance with a Directive issued by the Bureau.
5. The Bureau shall maintain a public record of each administrative penalty waived and report it to the Bureau on a quarterly basis.

## CHAPTER THREE

## TAX OFFENCES

**110. Procedure in Tax Offence Cases**

A tax offence is a violation of the criminal law of Ethiopia and shall be charged, prosecuted, and appealed in accordance with Criminal

እና ይግባኝም የሚቀርበው በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡

111. ከታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር የተገናኙ ወንጀሎች

1. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) ከአንድ በላይ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የወሰደ ወይም ለመውሰድ የሞከረ እንደሆነ፤

ለ) የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት የሰጠ፣ ወይም

ሐ) የሌላን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የተጠቀመ እንደሆነ፣ ብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) የገንዘብ ቅጣት እና ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) ታክስ ከፋዩ ለወሰደው ወይም ለመውሰድ ለሞከረው ለእያንዳንዱ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር በተናጠል ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ ጥቅም ላይ የዋለው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14(6) በተገለጹት ሁኔታዎች የሆነ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) እና (ሐ) ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

112. የሀሰት ወይም አሳሳች መግለጫዎች እና የተጭበረበሩ ሰነዶች

1. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) ለቢሮው ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ

Procedure Code of Ethiopia.

**111. Offences Relating to TINs**

1. A person who:

a) obtains, or attempts to obtain, more than one TIN;

b) allows their TIN to be used by another person; or

c) uses the TIN of another person, shall be punishable with a fine of birr 20,000 and simple imprisonment for a term of one to three years.

2. Sub-article (1) (a) of this Article applies separately to each TIN obtained or attempted to be obtained.

3. Sub-article (1) (b) and (c) of this Article shall not apply when a TIN is used in the circumstances specified in Article 14 (6) of this Proclamation.

**112. False or Misleading Statements, and Fraudulent Documents**

1. A person who:

a) makes a false or misleading statement to the Bureau; or

የሰጠ፤ ወይም

ለ) ለቢሮው የተጭበረበሩ ሰነዶችን ያቀረበ እንደሆነ፣ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከአምስት ዓመት እስከ ስምንት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

2. አንድ ሰው ለቢሮው ሊያስተላልፈው እንደሚችል እያወቀ ወይም ማወቅ የሚያስችለው በቂ ምክንያት እያለው ለሌላ ሰው የሰጠው ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለቢሮው እንደተሰጠ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ ይቆጠራል፡፡

3. ማንኛውም ሰው ታክስን ለማጭበርበር በማሰብ በሕይወት በሌለ ሰው ወይም አድራሻው በማይታወቅ ሰው ወይም ውክልና ለመስጠት ወይም የንግድ ሥራ ለመሥራት የሕግ ችሎታ በሌለው ሰው ወይም ከንግድ ሥራው ውጤት ተጠቃሚ ባልሆነ ሰው ወይም በሌላ የፈጠራ ሰው ስም የንግድ ፈቃድ አውጥቶ በውክልና የንግድ ሥራ የሚሠራ እንደሆነ ከንግድ ሥራው ለሚጠየቀው ታክስ ኃላፊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖበዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በወንጀል ይቀጣል፡፡

**113. የተጭበረበሩ ወይም ሕገ-ወጥ የሆኑ ደረሰኞች**

1. ማንኛውም ሰው፡-

b) provides the Bureau with fraudulent documents, shall be punishable with a fine of birr 50,000 to 100,000 and rigorous imprisonment for a term of three to fifteen years.

2. The reference in sub-article (1) of this Article to a statement made to the Bureau by a person shall include a statement made by the person to another person with the knowledge or reasonable expectation that the person will pass on the statement to the Bureau.

3. Whosoever, with the intention to evade tax, engages in business in an agents capacity by obtaining a trade license in the name of a person who is not alive or whose address is not known or who does not have the legal capacity to give power of attorney or who does not benefit from the business or who does not exist, shall apart from being responsible for the tax liability of the business, be punishable under sub article 1 of this article.

**113. Fraudulent or Unlawful Invoices**

1. A person who:

a) prepares, produces, sells, or

ሀ) የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ያዘጋጀ፣ ያተመ፣ የሸጠ ወይም ያሰራጨ፤ ወይም

ለ) የታክስ ዕዳውን ለመቀነስ ወይም ተመላሽ ለመጠየቅ የተጭበረበሩ ደረሰኞችን የተጠቀመ እንደሆነ፤ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ.ህ ብር) የገንዘብ ቅጣት እና ከሰባት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱትን የተጭበረበሩ ደረሰኞች በመጠቀም የተገኘው የገንዘብ ጥቅም ከብር 100,000 (ከመቶ ሺ.ህ ብር) የሚበልጥ እንደሆነ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚጣለው ቅጣት ከገንዘቡ ጥቅም ጋር እኩል በሆነ የገንዘብ ቅጣት እና ከአስር ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡

3. ሀሰተኛ ደረሰኞችን ለመስራት፣ ለማዘጋጀት ወይም ለማተም የሚያገለግል ማሽን፣ መሳሪያ፣ ወይም ሶፍትዌር የያዘ፣ የሸጠ፣ ያከራየ፣ ወይም በሌላ መንገድ ያቀረበ ማንኛውም ሰው ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺ.ህ ብር) የገንዘብ ቅጣት እና ከአስር ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ( 3) መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ መገኘት ማሽኑን፣ መሳሪያውን፣ሶፍትዌሩን ወይም የወንጀሉን ፍሬ መውረስን ያስከትላል፡፡

distributes fraudulent invoices; or

b) uses fraudulent invoices to reduce his tax liability or claim a refund, shall be punishable with a fine of birr 100,000 and rigorous imprisonment for a term of seven to ten years.

2. If the pecuniary benefit obtained by a person from a fraudulent invoice under sub-article (1) of this Article is greater than birr 100,000, the sanction under sub-article (1) shall be equal to the pecuniary benefit derived and imprisonment for a term of ten to fifteen years.

3. A person who possesses, sells, leases, or otherwise supplies a machine, equipment, or software that is used in making, preparing, or printing fraudulent invoices shall be punishable with a fine of birr 200,000 and rigorous imprisonment for a term of ten to fifteen years.

4. Conviction for an offence under sub-article (3) of this Article shall not prejudice the confiscation of the machine, equipment, or software, and of the proceeds of the crime.

5. ሀሰተኛ ደረሰኞችን የያዘ፣ ያሰቀመጠ፣ ለሽያጭ ያመቻቸ፣ ወይም ሀሰተኛ ደረሰኞች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደረገ ሰው ከሶስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደረስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

5. A person who possesses, keeps, facilitates, or arranges the sale, or commissions the use of fraudulent invoices shall be guilty of an offence punishable by rigorous imprisonment for a term of three to five years.

**114. ከደረሰኝ ጋር የተገናኙ ጠቅላላ ወንጀሎች**

**114. General Offences Relating to Invoices**

1. ማንኛውም ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ያለደረሰኝ ግብይት ያከናወነ እንደሆነ ከብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ) እስከ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጫእና ከሶስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፡፡
2. በአንድ ግብይት በተሰጡ ተመሳሳይ የደረሰኝ ኮፒዎች ላይ የተለያዩ ዋጋዎችን በመመዝገብ የሽያጭ ዋጋን ያሳነሰ ማንኛውም ሰው ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) እና ከአምስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
3. የሽያጩ ትክክለኛ ዋጋ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) የሚበልጥ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚጣለው ቅጣት በደረሰኞቹ ላይ ከተመለከቱት ከፍተኛው የገንዘብ መጠን እና ከሰባት ዓመት እስከ አስር ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
4. ግብይት ሳይፈጸም ደረሰኝ የሰጠ ወይም የተቀበለ ሰው ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) እስከ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሰባት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ

1. Any taxpayer with an obligation to issue a tax invoice, carrying out transaction without tax invoice shall be punishable with a fine of birr 25,000 to 50,000 and with rigorous imprisonment for a term of three to five years.
2. A person who understates a sales price by entering different amounts of the price in identical copies of the invoice for a single transaction shall be punishable with a fine of birr 100,000 and rigorous imprisonment for a term of five to seven years.
3. If the actual price of the sale is greater than birr 100,000, the sanction under sub-article (2) of this Article shall be a fine equal to the highest of the prices specified on the invoices and rigorous imprisonment for term of seven to ten years.
4. A person who provides or accepts an invoice for which there is no transaction shall be punishable with a fine of birr 100,000 to 200,000 and rigorous imprisonment for a term of seven to ten

ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከተው ደረሰኝ ከብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) የሚበልጥ የገንዘብ መጠን የያዘ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚጣለው ቅጣት በደረሰኙ ከተገለጸው የገንዘብ መጠን ጋር እኩል በሆነ የገንዘብ ቅጣት እና ከአስር ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚደረስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
6. ቢሮው ሳይፈቅድለት የታክስ ደረሰኝ ያተመ ሰው ከብር 3,000 (ሦስት መቶ ሺህ ብር) እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሁለት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ጥፋተኛ የተባለ ሰው ወንጀሉን ለሁለተኛ ጊዜ የፈጸመ እንደሆነ የህትመት መሣሪያው እና የማተሚያ ድርጅቱ ይወረሳል፣ የንግድ ፈቃዱም ይሰረዛል፡፡

**115. ሕገ-ወጥ የሆነ ተመላሽን ወይም ከተገቢው በላይ ማካካሻን መጠየቅ**

1. ቢሮውን ለማጭበርበር በማሰብ ተመላሽ ወይም ማካካሻ የጠየቀ ሰው ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) እና ከአምስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት

years.

5. If the invoice to which sub-article (4) of this Article applies is for an amount in excess of birr 200,000, the sanction under sub-article (1) of this Article shall be a fine equal to the amount stated on the invoice and to rigorous imprisonment for a term of ten to fifteen years.
6. Whosoever without authorization from the Bureau prints tax invoices shall be punishable with a fine of birr 300,000 to birr 500,000 and with rigorous imprisonment of two to five years.
7. A person found guilty and convicted under sub-article (6) of this Article for the second time, shall forfeit his printing machine and/or his business and his business license shall be cancelled.

**115. Claiming Unlawful Refunds or Excess Credits**

1. A taxpayer who claims a refund or tax credit with intent to defraud the Bureau using a falsified receipt or by employing any other similar method, shall be punishable with a fine of birr 50,000 and with rigorous imprisonment for a term of five to seven years.
2. Conviction for an offence under sub-article

የሚጣለው ቅጣት፣ ታክስ ከፋዩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 49 መሠረት ተመላሽ የተደረገለትን ታክስ መልሶ ከመክፈል ግዴታ ነጻ ሊያደርገው አይችልም፡፡

**116. ከቴምብር ቀረጥ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች**

1. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በምስክርነት ካልሆነ በስተቀር የቴምብር ቀረጥ ሊከፈልበት ሲገባ የቴምብር ቀረጥ ያልተከፈለበትን ሰነድ ሥራ ላይ ያዋለ ወይም የፈረመ፣ ወይም

ለ) የቴምብር ቀረጥ ላለመክፈል ወይም አነስተኛ የቴምብር ቀረጥ ለመክፈል በማሰብ የአንድን ሰነድ ትክክለኛ ባህሪይ ያልገለጸ ወይም የደበቀ እንደሆነ፣ ከብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) እስከ ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሶስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

2. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) ቴምብሮችን ወይም ቴምብር የተመታባቸውን ሰነዶች ለመሸጥ የተፈቀደለት ሆኖ የቴምብር ቀረጥ አዋጁን ወይም ደንቡን የተላለፈ እንደሆነ፣ ወይም

ለ) ቴምብሮችን ወይም ቴምብር የተመታባቸውን ሰነዶች ሳይፈቀድለት የሸጠ ወይም ለሽያጭ ያቀረበ እንደሆነ፣ ከብር 5,000 (አምስት ሺህ ብር) እስከ ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ ብር)

(1) of this Article shall not relieve the taxpayer from the obligation to repay the refund under Article 49.

**116. Stamp Duty Offences**

1. A person who:

a) executes or signs (other than as a witness) a document subject to stamp duty on which no stamp duty is paid; or

b) disguises or hides the true nature of a document with the intention of not paying stamp duty or paying a lower amount of stamp duty, shall be punishable with a fine of birr 25,000 to birr 50,000 and rigorous imprisonment for a term of three to five years.

2. A person who:

a) being authorised to sell stamps or stamped papers violates the Stamp Duty Proclamation or Regulations; or

b) sells or offers for sale stamps or stamped papers without authorisation, shall be punishable with a fine of birr 5,000 to birr 25,000 and rigorous imprisonment for a term of three

በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሶስት ዓመት እስከ አምስት ዓመታት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

to five years.

**117. ታክስን ለማስከፈል ከሚወሰድ እርምጃ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች**

1. ማንኛውም የታክስ ከፋይ ንብረት ተረካቢ በታክስ ሕጎች በተደነገገው መሠረት የተጣለበትን ግዴታ ሳይፈፅም የቀረ እንደሆነ በብር 5,000 (አምስት ሺህ ብር) የገንዘብ ቅጣት እና በአንድ ዓመት ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 41 መሠረት የንብረት መያዝ ትዕዛዝ የደረሰው ሰው፡-
   ሀ) ትዕዛዙ የተላለፈበትን ንብረት የሸጠ፣ የለወጠ፣ ወይም በሌላ መንገድ ያስተላለፈ እንደሆነ፤
   ለ) ትዕዛዙ የተላለፈበትን ንብረት የደበቀ፣ የሰበረ፣ ያበላሸ ወይም የጎዳ እንደሆነ፤ ወይም
   ሐ) ትዕዛዙ የተላለፈበትን ንብረት የሚመለከት ማናቸውንም ሰነድ ያወደመ፣ የደበቀ፣ ያስወገደ፣ የጎዳ፣ የለወጠ፣ የሰረዘ፣ የደለዘ ወይም ያጠፋ እንደሆነ፤ ከሁለት ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለሶስተኛ ወገን በሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ መሠረት የተጠየቀውን ገንዘብ ለቢሮው ያልከፈለ ማንኛውም ሰው ከሁለት ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል

**117. Offences Relating to Recovery of Tax**

1. A receiver entrusted with the property of a taxpayer failing to discharge his obligation under any tax law shall be punishable with a fine of birr 5,000 and with simple imprisonment of one year.
2. A person who, after receipt of a seizure order under Article 41:
   a) sells, exchanges, or otherwise disposes of the property that is the subject of the order;
   b) hides, breaks, spoils, or damages the property that is the subject of the order; or
   c) destroys, hides, removes, damages, changes, cancels, or deletes any documents relating to the property the subject of the order, shall be punishable with simple imprisonment of two to three years.
3. Subject to sub-article (4) of this Article, a person who fails to pay the amount specified in a garnishee order to the Bureau shall be punishable with simple imprisonment of two to three years.

እስራት ይቀጣል፡፡

4. ለሶስተኛ ወገን የሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ የደረሰው ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 43 (5) መሠረት ትዕዛዙን መፈጸም እንደማይችል ለቢሮው ካሳወቀ፣ ቢሮው የሰጠውን ትዕዛዝ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 43(6) መሠረት መሻሩን ወይም ማሻሻሉን ወይም ትዕዛዙ የደረሰው ሰው ያቀረበውን ማስታወቂያ ውድቅ ማድረጉን እስካላስታወቀው ድረስ ለሶስተኛ ወገን የሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ የተሰጠው ሰው ትዕዛዙን እንደፈጸመ ይቆጠራል፡፡
5. ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱ በደረሰው ለሶስተኛ ወገን የሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ የተጠየቀውን ገንዘብ የመክፈል ግዴታውን አያስቀርም፡፡
6. ከሃገር የመውጣት ክልከላ ትዕዛዝን በመጣስ ከኢትዮጵያ የወጣ ወይም ለመውጣት የሞከረ ማንኛውም ሰው ከሁለት ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡
7. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 42 መሠረት የተላለፈን ትዕዛዝ ያላከበረ ማንኛውም የፋይናንስ ተቋም በዚህ ምክንያት ባለስልጣኑ ሳይሰበሰበው በቀረው የገንዘብ ልክ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 የተመለከተው ወንጀል የተፈጸመው የፋይናንስ ተቋሙ ሥራ አስኪያጅ እያወቀ ወይም በቸልተኝነቱ

4. A person who notifies the Bureau under Article 43 (5) of this Proclamation is treated as being in compliance with a garnishee order served on the person until the Bureau serves the person with a notice under Article 43 (6) of this Proclamation cancelling or amending the garnishee order or a person to whom a payment order is given to a third party shall be deemed to have executed the order unless the person to whom the order is received has notified that he has rejected the notice.
5. The conviction of a person for an offence under sub-article (3) of this Article shall not relieve the person of liability to pay the amount required to be paid under the garnishee order.
6. A person who departs or attempts to depart from Ethiopia in contravention of a departure prohibition order shall be punishable with simple imprisonment of two to three years.
7. A financial institution that fails to comply with order issued under Article 42 of this Proclamation shall be punishable by a fine equal to the tax that the Bureau failed to collect as result of the failure.
8. If an offence under sub-article (7) of this Article was committed with the knowledge or as a result of negligence of the manager of the financial institution, the manager

ምክንያት የሆነ እንደሆነ ሥራ አስኪያጁ ከሁለት ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

9. ከቢሮው ፈቃድ ሳያገኝ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 45 መሠረት የእሽግ ትዕዛዝ የተላለፈበትን የንግድ ሥፍራ ወይም ቦታ እሽግ የከፈተ ወይም ያስወገደ ሰው ከሁለት ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

**118. ታክስን ስለመሰወር**

1. ማንኛውም ሰው ታክስን ለመሰወር በማሰብ ገቢውን የደበቀ፣ የታክስ ማስታወቂያውን ያላቀረበ ወይም ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ.ህ ብር) እስከ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺ.ህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሶስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
2. ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ታክስን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው ታክስን ለመሰወር በማሰብ ቀንሶ የያዘውን ታክስ ለቢሮው ያላስተላለፈ ከሆነ ከሶስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

**119. የታክስ ሕጎችን አስተዳደር ስለማደናቀፍ**

1. በታክስ ሕጉ መሠረት ግዴታውን እየተወጣ ያለን የታክስ ሠራተኛ ያደናቀፈ ወይም ለማደናቀፍ የሞከረ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

shall be punishable by simple imprisonment of two to three years.

9. A person who, without the permission of the Bureau, opens or removes the seal of premises that are the subject of a closure order under Article 45 shall be punishable with simple imprisonment of two to three years.

**118. Tax Evasion**

1. Whosoever, with the intention to evade tax, conceals his income or fails to file a tax declaration or pay tax by the due date shall be punishable with a fine of birr 100,000 to 200,000 and rigorous imprisonment for a term of three to five years.
2. A withholding agent who withholds tax from a payment but fails to pay the withheld tax to the Bureau by the due date with the intention to evade tax shall be punishable by rigorous imprisonment for a term of three to five years.

**119. Obstruction of Administration of Tax Laws**

1. A person who obstructs or attempts to obstruct a tax officer in the performance of duties under a tax law shall be punishable with simple imprisonment for a term of one to three years.

2. የታክስ ሕግ አስተዳደርን ያደናቀፈ ወይም ለማደናቀፍ የሞከረ ማንኛውም ሰው ከብር 10,000 (አሥር ሺህ ብር) በማያንስ የገንዘብ ቅጣት እና ከሶስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ የሚከተሉት እና ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶች የማደናቀፍ ተግባራት ተደርገው ይወሰዳሉ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 85 መሠረት በሚሰጥ ማስታወቂያ መሠረት አለመፈጸምን ጨምሮ፣ ሰነዶችን ለመመርመር ከቢሮው የሚቀርብ ጥያቄን አለመቀበል ወይም ሪፖርቶችን ወይም የታክስ ከፋዩን የታክስ ጉዳዮች የሚመለከት መረጃን ለማቅረብ ፈቃደኛ አለመሆን፣

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 85 መሠረት ቀርቦ ማስረጃ እንዲሰጥ በተሰጠው ማስታወቂያ መሠረት አለመፈጸም፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 66 መሠረት የቢሮ ሀላፊ የወከለውን የታክስ ሠራተኛ ማንኛውንም መረጃ ወይም ማስረጃ ለማግኘት ያላቸውን መብት እንዳይጠቀሙ መከልከል፣

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 66 (4) መሠረት አስፈላጊውን እርዳታ ለመስጠት ወይም መገልገያ ለማቅረብ ፈቃደኛ አለመሆን፣

ሠ) በቢሮው ቢሮ ውስጥ ሁከት መፍጠር ወይም የታክስ ሠራተኞች የቅጥር ግዴታቸውን እንዳይወጡ ማደናቀፍ፡፡

2. A person who obstructs or attempts to obstruct the administration of a tax law shall be punishable with a fine of not less than birr 10,000 and rigorous imprisonment for a term of three to five years.
3. In this Article, the following and other similar actions constitute obstruction:

a) refusing to comply with a request of the Bureau for inspection of documents, or the provision of reports or information relating to the tax affairs of a taxpayer, including a refusal to comply with a notice served on the person under Article 85 of this Proclamation;

b) non-compliance with a notice served on the person under Article 85 of this Proclamation requiring the person to attend and give evidence;

c) preventing the officer authorised by Head of the Bureau from exercising the right of access under Article 66 of this Proclamation;

d) refusing to provide reasonable assistance or facilities as required under Article 66 (4);

e) provoking a disturbance in an office of the Bureau or impeding an employee of the Bureau from performing their duties of employment.

**120. ስልጣን ሳይኖር ታክስ መሰብሰብ**

በማንኛውም የታክስ ሕግ ታክስ እንዲሰበስብ ሥልጣን ያልተሰጠው ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ታክስ የሰበሰበ ወይም ለመሰብሰብ የሞከረ እንደሆነ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) እስከ ብር 75,000 (ሰባ አምስት ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከአምስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

**121. በታክስ ወንጀል መርዳት ወይም ማበረታታት**

አንድ ሰው በታክስ ህግ መሠረት የተደነገገን የታክስ ወንጀል "ዋና ወንጀል" አድራጊ ተብሎ የሚታወቅ ሌላ ሰው እንዲፈጽም የረዳ፣ ያበረታታ፣ ያገዘ፣ ያነሳሳ ወይም የተመሳጠረ እንደሆነ በዋናው ወንጀል አድራጊ ላይ የተጣለውን ቅጣት ይቀጣል፡፡

**122. ከታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ጋር የተያያዙ ወንጀሎች**

1. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን አባልነቱ ኃላፊነቱን በመፈጸም ላይ ያለን ሰው የሰደበ፣

ለ) ፈቃድ ሳይኖረው የኮሚሽኑን የሥራ ሂደት ያቋረጠ፤

ሐ) የኮሚሽኑን የሥራ ሂደት ለማወክ በማሰብ በኮሚሽኑ ግቢ ውስጥ ወይም ኮሚሽኑ ባለበት አካባቢ ረብሻ የፈጠረ ወይም በረብሻው የተሳተፈ፤ ወይም

**120. Unauthorised Tax Collection**

A person not authorised to collect tax under the tax laws who collects or attempts to collect tax, shall be punishable with fine of birr 50,000 to 75,000 and rigorous imprisonment for a term of five to seven years.

**121. Aiding or Abetting a Tax Offence**

A person who aids, abets, assists, incites, or conspires with another person to commit an offence under a tax law referred to as the “principal offence” shall be punishable by the same sanction as imposed for the principal offence.

**122. Offences Relating to the Tax Appeal Commission**

1. A person who:

a) insults a member of the Commission in the exercise of his powers or functions as a member;

b) interrupts a proceeding of the Commission without authorisation;

c) creates a disturbance, or takes part in creating a disturbance, in or near a place where the Commission is sitting with the intent of disrupting the proceedings of the Commission; or

መ) በማናቸውም ሁኔታ የኮሚሽኑን ሥራ ያሰናከለ እንደሆነ፤ ከብር 500 (አምስት መቶ ብር) እስከ ብር 3,000 (ሦስት ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ወይም ከስድስት ወር እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

2. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በኮሚሽኑ ፊት እንዲቀርብ ወይም ለኮሚሽኑ ሰነድ እንዲያቀርብ ወይም መረጃ እንዲሰጥ መጥሪያ ሲደርሰው ያለበቂ ምክንያት በመጥሪያው መሠረት ያልፈጸመ፤

ለ) በኮሚሽኑ ፊት ያለምንም በቂ ምክንያት ቃለ-መሃላ ለመፈጸም ፈቃደኛ ያልሆነ፤

ሐ) ኮሚሽኑ በሚያየው ጉዳይ ለቀረበለት ጥያቄ ያለ በቂ ምክንያት መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ፣ ከብር 300(ሦስት መቶ ብር) እስከ ብር 3,000 (ሦስት ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከስድስት ወር እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

3. ማንኛውም ሰው ለኮሚሽኑ እያወቀ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች ማስረጃ የሰጠ እንደሆነ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) በማያንስ ገንዘብ ቅጣት እና ከሶስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

**123. በታክስ ወኪሎች ስለሚፈፀም ወንጀል**

ማንኛውም ሰው የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ሳይሰጠው የዚህን አዋጅ አንቀጽ 93 በመተላለፍ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ

d) obstructs the function of the commission by whatever means, shall be punishable with a fine of birr 500 to 3,000 or simple imprisonment for a term of six months to two years.

2. A person who:

a) without reasonable excuse, refuses or fails to comply with a summons to appear before the Commission, or to produce any document or provide any information to the Commission;

b) without reasonable excuse, refuses to take an oath before the Commission;

b) without reasonable excuse, refuses or fails to answer any question asked of the person during a proceeding before the Commission; shall be punishable with a fine of birr 300 to 3,000 and simple imprisonment for a term of six months to two years.

3. Whosoever, knowingly gives false or misleading evidence to the Commission, shall be punishable with a fine of birr 50,000 and with rigorous imprisonment of three to five years.

**123. Offences by Tax Agents**

Whosoever, without having a license to act as a tax agent, provides tax agent's services in contravention of Article 93 of this

ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

124. ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪዎች ጋር በተገናኘ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

1. ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው፡-

ሀ) በቢሮው ዕውቅና ያልተሰጠው ወይም ያልተመዘገበ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከተጠቀመ ከሶስት ዓመት በማያንስ እና ከሰባት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

ለ) መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ወይም በሌላ በቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ፣ ከሁለት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

ሐ) በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው የፊስካል ማስታወሻ ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም የፊስካል ማስታወሻ እንዲቀየር ያደረገ ወይም ጉዳት ለማድረስ ወይም ማስታወሻውን ለመቀየር ሙከራ ያደረገ ከሆነ፣ ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

2. ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት ዕውቅና እና ፈቃድ የተሰጠው ሰው፡-

ሀ) በቢሮው ዕውቅና ያልተሰጠውን

Proclamation shall be punishable by simple imprisonment for a term of one to three years.

**124. Offences Relating to Sales Register Machines**

1. Any person who has the obligation to use sales register machine commits an offence;

a) if found using a sales register machine not accredited or registered by the Bureau, shall be punished with rigorous imprisonment for a term of not less than three year and not more than seven years;

b) if he, except at the time the sales register machine is under repair, or other justifiable reason , carried out transactions without receipt or invoice or used any other receipt not generated by a sales register machine shall be punished with rigorous imprisonment for a term of not less than two year and not more than five years;

c) if caused damage or change to the fiscal memory of a sales register machine or attempts to cause damage or change to the fiscal memory shall be punished with rigorous imprisonment for a term of not less than three years and not more than five years;

2. Any person who is accredited and registered to supply sales register machines commits an offence:

a) if sold a software or a sales register

መሣሪያ ወይም ሶፍትዌር ለገበያ ካዋለ፣ ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

ለ) በሥራ ላይ ባሉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ላይ የሚደረገውን ማናቸውንም ለውጥ ለቢሮው በቅድሚያ ካላስታወቀ ወይም በመሣሪያው የአጠቃቀም መመሪያ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካስገባ ወይም ትክክለኛውን መረጃ ከቀነሰ፣ ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

3. ማንኛውም ሰው የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት ፈቃድ ሳይኖረው ማንኛውንም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም ሶፍትዌር ለገበያ ያዋለ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

4. ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል አቅራቢው ዕውቅና ያልሰጠውን እና በቢሮው ያልተመዘገበ ሠራተኛ በሥራ ላይ አሰማርቶ ከተገኘ በብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) የገንዘብ ቅጣት ወይም ከአንድ ዓመትበማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

5. ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ያለአገልግሎት ማዕከሉ እና ቢሮው ዕውቅና ከፈታታ ወይም

machine not accredited by the Bureau shall be punished with rigorous imprisonment for a term of not less than three years and not more than five years;

b) if failed to notify the Bureau in advance any change made to the sales register machine in use, or if inserted incorrect information to or omitted the correct information from the manual that guides the use of sales register machine shall be punished with rigorous imprisonment for a term of not less than three years and not more than five years.

3. Who so ever without having a license to supply sales register machine or software, distributes sales register machine or software, shall be punishable with rigorous imprisonment of five to seven years.

4. Any sales register machine service centre deploying a service personnel that is not certified by the supplier and/or not registered by the Bureau, shall be punished with a fine of birr 50,000 or imprisonment for a term of not exceeding one year.

5. Any personnel of a sales register machine service centre commits an offence if, without the knowledge of the service centre and the Bureau, dismantle or assemble a sales register machine, or if deliberately removed

ከገጣጠመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ሳይበላሽ ሆን ብሎ እሽጉን ካነሳ ወይም አካሉን ከቀየረ ወይም እነዚህን የመሳሰሉ አድርጎቶች ከፈጸመ ከብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ ቅጣት እና ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

6. የታክስ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አጠቃቀም ደንብ እና መመሪያዎችን በመተላለፍ፡-

   ሀ) የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የፈታ ወይም የገጣጠመ ወይም የአገልግሎት ማዕከል ሠራተኛ በሌለበት ሥራ ላይ እንዲውል የፈቀደ ወይም የመሣሪያውን መለያ ቁጥር የቀያየረ እንደሆነ፣ ወይም

   ለ) በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ተጠቃሚው ወይም በአገልግሎት ማዕከሉ ወይም በሠራተኛው ወይም በአቅራቢው የተፈጸመን ማናቸውንም ሕገ ወጥ ድርጊት እያወቀ ወይም በቸልተኝነት በ24 (ሃያ አራት) ሰዓት ውስጥ ለቢሮው ሪፖርት ያላደረገ እንደሆነ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 5,000 (አምስት ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ ቅጣት እና ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

## 125. በድርጅቶች የሚፈፀሙ ወንጀሎች

1. የታክስ ሕግን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመው

the seals on a sales register machine or changed parts of a sales register machine not reported to have any break down, or if committed any similar act and shall, upon conviction, be punished with a fine of not more than Birr 10,000 and imprisonment for a term of not less than one year and not more than three years.

6. Any tax officer who, in violation of the rules and procedures of the use of sales register machines:

   a) dismantles or assembles a sales register machine or approves its utilization without the presence of a service personnel or changes the machine registration code; or

   b) knowingly or negligently fails to report to the Bureau, within 24 hours, offences committed by the user, service centre or its personnel or supplier of a sales register machine; commits an offence and shall, upon conviction, be punished with a fine of not more than Birr 5,000 and imprisonment for a term of not less than one year and not more than three years.

## 125. Offences by Bodies

1. When the person committing an offence under a tax law is a body, every person who

ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ በተፈፀመበት ወቅት ሥራ አስኪያጅ የሆነ ማንኛውም ሰው ወንጀሉን እንደፈፀመ ይቆጠራል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፡-

ሀ) ወንጀሉ የተፈጸመው ሥራ አስኪያጁ ሳይፈቅድ ወይም ሳያውቅ ከሆነ፣ እና

ለ) በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ያለና ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው የጥፋቱን መፈፀም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብለው የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን ለማድረግ ተገቢውን ትጋት እና የአሠራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ወስዶ የተገኘ እንደሆነ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

126. የታክስ ወንጀል የፈጸሙ ሰዎችን ስም ይፋ ስለማድረግ

1. ቢሮው በታክስ ወንጀል ጥፋተኛ የተባሉትን ሰዎች ስም ዝርዝር በቢሮው ድረ-ገጽ እንዲሁም በሌሎች የመገናኛ ብዙሃን በየጊዜው ይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ይፋ የሚደረገው ዝርዝር የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡

ሀ) ጥፋተኛ የተባለውን ሰው ስም፣ ምስል እና አድራሻ፣

ለ) ቢሮው አግባብ ናቸው የሚላቸውን የወንጀሉን ዝርዝር ጉዳዮች፤

ሐ) ወንጀሉ የተፈፀመበትን የታክስ ጊዜ

is a manager of the body at the time the offence was committed shall be treated as having committed the same offence.

2. Sub-article (1) of this Article shall not apply to a person where :

a) the offence was committed without the person's consent or knowledge; and

b) he has exercised due diligence and caution that a prudent person in his position is expected to take under similar circumstance and the precautions that are assumed to be taken by a person who is in the same situation and sees things carefully to prevent the commission of the crime

**126. Publication of Names**

1. The Bureau may from time to time publish a list of the names of persons convicted by final decisions of court of law of an offence under a tax law on its website and through other mass media.

2. A list published in accordance with sub-article (1) of this Article shall specify the following:

a) the name, picture, and address of the convicted person;

b) particulars of the offence as the Bureau considers appropriate;

c) the tax period or periods during which

ወይም ጊዜያት፤

መ) ጥፋተኛ የተባለው ሰው በፈጸመው ወንጀል ምክንያት ያልከፈለውን የታክስ መጠን፤

ሠ) ጥፋተኛ በተባለው ሰው ላይ የተጣለ የገንዘብ ቅጣት ካለ የቅጣቱን መጠን፣

## ምዕራፍ አራት
## ሽልማቶች

### 127. የታክስ ስወራን በሚመለከት ለተሰጠ ተጨባጭ መረጃ የሚሰጥ ሽልማት

1. ማንኛውም ሰው በመደበቅ፣ አሳንሶ በማሳወቅ፣ በማጭበርበር ወይም በሌላ ተገቢ ባልሆነ መንገድ የሚፈፀምን የታክስ ስወራ አስመልክቶ ሊረጋገጥ የሚችል ተጨባጭና የማያሻማ መረጃ ለቢሮው የሰጠ እንደሆነ፣ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የተሰወረውን ታክስ መጠን እስከ 20% (ሃያ በመቶ) በሽልማት መልክ ታክሱ በሚሰበሰብበት ጊዜ ለዚህ ሰው ይሰጣል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፡-
   ሀ) በታክስ ስወራው ተግባር ላይ ለተሳተፈ፤ ወይም
   ለ) የታክስ ስወራውን ማሳወቅ የመደበኛ ሥራው አካል ለሆነ ሰው፤ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ የተጠቀሰውን ሽልማት በተመለከተ ቢሮው ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡

### 128. ለላቀ የሥራ ክንውን የሚሰጥ ሽልማት

1. ቢሮው የላቀ የሥራ ክንውን ላስመዘገበ

the offence was committed;

d) the amount of tax not paid by the convicted person as a result of commission of the offence;

e) The amount, if any, of penalty assessed to the convicted person.

## CHAPTER FOUR
## REWARDS

### 127. Reward for Verifiable Information of Tax Evasion

1. If a person provides verifiable and objective information of tax evasion, through concealment, under-reporting, fraud, or other improper means, the Bureau shall, in accordance with the directive to be issued by it, grant the person a reward of up to 20% of the amount of the tax evaded at the time the tax is collected by the Bureau.
2. A person shall not be entitled to a reward under sub-article (1) of this Article if:
   a) the person participated in the tax evasion; or
   b) the reporting of the tax evasion was part of the person’s duties
3. The Bureau shall provide details of a reward under this Article by Directive.

### 128. Reward for Outstanding Performance

1. The Bureau shall reward a tax officer for

የታክስ ሠራተኛ እንዲሁም የታክስ ግዴታውን በአርዓያነት ለተወጣ ታክስ ከፋይ ሽልማት ይሰጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ የተጠቀሰውን ሽልማት በተመለከተ ቢሮው ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

## ክፍል አሥራ ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 129. ደንቦችንና መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን

1. የመስተዳደር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ ትክክለኛ አፈጻፀም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ቢሮው ለዚህ አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለሚወጣው ደንብ ትክክለኛ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 130. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በተፈጸመ ድርጊት ወይም አለማድረግ ወይም በተላለፈ የታክስ ውሳኔ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፡-

ሀ) ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ሊከፈል ሲገባ ባልተከፈለ ታክስ ላይ የሚጣል አስተዳደራዊ መቀጫ በቀድሞ ደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ገቢዎች ባለስልጣን በሥራ ላይ በነበሩት የታክስ ሕጎች መሠረት ፍጻሜ ያገኛል፡፡

ለ) ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት

outstanding performance and a taxpayer for exemplary discharge of his tax obligations.

2. The Bureau shall provide details of a reward under this Article by Directive.

## PART SIXTEEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 129. Power to Issue Regulations and Directives

1. The Administrative Council may issue Regulations necessary for the proper implementation of this Proclamation.
2. The Bureau may issue Directives necessary for the proper implementation of this Proclamation and Regulations issued under sub-article (1) of this Article.

### 130. Transitional Provisions

1. This Proclamation shall apply to an act or omission occurring caused a tax decision made before its entry in to force.
2. Notwithstanding sub article (1) of this proclamation:-

a) Administrative penalties applicable to non-payment of taxes due before this proclamation becomes effective shall be assessed in accordance with the tax laws of former South Nations Nationalities and Peoples' Revenue Authority in force prior to this proclamation.

b) Any case that has been pending in the

በቀድሞ ደቡብ ብሄረች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ገቢዎች ባለስልጣን ግብር ይግባኝ ጉባኤ በመታየት ላይ የነበሩ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ መሰረት በአዲስ መልክ በሚቋቋመው የግብር ይግባኝ ጉባኤ በቀድሞ ደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ገቢዎች ባለስልጣን በስራ ላይ በነበሩት የታክስ ሕጎች መሰረት ታይቶ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል፡፡

ሐ) በቢሮው የአቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል እና የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት በአዲስ መልክ እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡

መ) ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በቀድሞ ደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል መንግስት ታክስ አስተዳደር ህግ ድንጋጌ መሰረት ማመልከቻና ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈባቸው ግብር ከፋዮች በዚህ አዋጅ መሰረት ማመልከቻና ይግባኝ እንደአዲስ ማቅረብ አይችሉም፡፡

3. ይህ አዋጅ በፀናበት ዕለት የተመሠከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች ኢንሲቲትዩት ያልተቋቋመ እንደሆነ ኢንስቲትዩቱ እስኪቋቋም ድረስ በዚህ አዋጅ ኢንሲቲትዩቱን የሚጠቅስ ማንኛውም አንቀጽ ለዚህ አዋጅ ዓላማ የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድን የሚመለከት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

4. ለዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 አፈጻጸም ሲባል፣ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች

former South Nations Nationalities and Peoples’ Revenue Authority tax appeal commission when this proclamation becomes effective shall be adjudicated in accordance with the tax laws of former South Nations Nationalities and Peoples’ Revenue Authority that is in force prior to this proclamation.

c) The Bureau's Complaints Inquiry Department and Tax Appeals Commission shall be reorganized in accordance with the provisions of this Proclamation.

d) According to the provisions of the Tax Administration law of the Former South Nations, Nationalities and Peoples' Region State before this proclamation is ratified, taxpayers whose application and appeals have expired cannot submit new applications and appeals according to this proclamtion.

3. For the purposes of this Proclamation, if the Institute of Certified Public Accountants is not established at the commencement of this Proclamation, any reference in this Proclamation to the Institute shall be treated as a reference to the Accounting and Auditing Board of Ethiopia until the Institute is established.

4. The obligatory use of sales register machines shall continue to apply for the

ስለመጠቀም ግጼታ በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ሌላ ደንብ እስኪተካ ድረስ ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

131. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ድንጋጌዎች

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 130 ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ይህን አዋጅ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም ድንጋጌ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

132. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

ይህ አዋጅ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ማዕከላዊ ነጋሪት ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ወልቂጤ**

**የካቲት 20 ቀን 2016 ዓ.ም**

**እንዳሻው ጣሰው**

**የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት**

**ፕሬዝዳንት**

purposes of Article 20 of this Proclamation until replaced by other Regulations issued by the Administrative Council .

**131. Inapplicable Provisions**

Subject to the provisions of Article 130 of this proclamation, any law that is inconsistent with this proclamation shall not be applicable in respect of matters provided for in this proclamation.

**132. Effective Date**

This Proclamation shall enter in to force on the date of its Publication in the Central Ethiopia Region State Negarit Gazeta.

**Done at Wolqite, 28 February 2024.**

**Endashaw Tasew**

**Presidenete of the Central Ethiopia Region State**